# የፌደራል የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ስልጠና ማዕከል

**ለቅድመ ስራ ሰልጣኞች የተዘጋጀ**
**የስልጠና ማኑዋል**

## *የታክስ ሕግና የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት*

በፌደራል የፍትህ አካላት ባለሙያወች ስልጠና ማእከል የተዘጋጀ

# ማውጫ

ገፅ


**የሞጁሉ መግቢያ---------------------------------------------------------------**

**ክፍል አንድ፡- የታክስ ሥልጣን ክፍፍል በኢፌድሪ ሕገ መንግሥት--------------------7**

መግቢያ --------------------------------------------------------------------------------------7

1.1. ታክስ በአጠቃላይ---------------------------------------------------------------------9

1.1.1. ምንነት--------------------------------------------------------------------------9

1.1.2. አላማ---------------------------------------------------------------------------10

1.1.3. መዋቅር-----------------------------------------------------------------------11

1.2. የታክስ ሥልጣን ክፍፍል በፌዴራል ሥርዓት-----------------------------------13

1.2.1. የታክስ ሥልጣን ምንነት----------------------------------------------------13

1.2.2. የታክስ ሥልጣን ገፅታዎች--------------------------------------------------15

1.2.3. መርሆች----------------------------------------------------------------------16

1.2.4. ዘዴዎች (Methods) ---------------------------------------------------------18

የመወያያ ጥያቄዎች-----------------------------------------------------22

1.3. የታክስ ሥልጣን ክፍፍል በኢፌድሪ ሕገ መንግሥት-------------------------------22

1.3.1. የፌዴራልና የክልል መንግስታት ብቸኛ የታክስ ሥልጣን---------------23

1.3.2. የጋራ የታክስ ሥልጣን (Concurrent Taxes)----------------------------28

የመወያያ ጥያቄዎች-------------------------------------------------------34

1.4. ተለይተው ያልተሰጡ የታክስ ሥልጣኖች (Residual Taxes)---------------------35

የመወያያ ጥያቄዎች------------------------------------------------------------37

1.5. የታክስ ሥልጣን ገደቦች---------------------------------------------------------------38

1.5.1. አድሏዊ በሆኑ የፌዴራል ታክስ ሕጎች ላይ የተጣለ ገደብ -----------------38

1.5.2. ክልል ዘለል በሆኑ የክልል መንግስት የታክስ

ሕግ ላይ የተጣለ ገደብ ---------------------------------------------------40

1.5.3. አንዱ የመንግሥት እርከን

በሌላው መንግስት ንብረት ላይ ታክስ አለመጣል----------------------------41

የመወያያ ጥያቄዎች-------------------------------------------------------------43

**ክፍል ሁለት፡- የታክስ መዋቅር በኢፌድሪ መንግሥት**--------------------------44
*መግቢያ* ------------------------------------------------------------------------------------44
2.1. የታክስ መዋቅር በቅድመ ኢፌድሪ ባጭሩ---------------------------------------------46
2.2. በኢፌድሪ፤- ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶች----------------------------------47
2.2.1. ቀጥተኛ ታክሶች፡-የገቢ ታክስ-----------------------------------------------------48
2.2.1.1. ምንነት---------------------------------------------------------------------48
2.2.1.2. ተፈጻሚነት ወሰን---------------------------------------------------------50
የመወያያ ጥያቄዎች-----------------------------------------------------52
2.2.1.3. የገቢ ምንጭ-----------------------------------------------------------------52
2.2.1.4. የገቢ ታክስ ሥረዓት-------------------------------------------------------53
2.2.1.5. የገቢ ታክስ አይነቶች------------------------------------------------------54
2.2.1.5.1. ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ታክስ (ሠንጠረዥ "ሀ") -------54
የመወያያ ጥያቄ--------------------------------------------57
2.2.1.5.2. የቤት ኪራይ ገቢ ታክስ (ሠንጠረዥ "ለ")--------------57
2.2.1.5.3. የንግድ ሥራ ትርፍ ታክስ (ሠንጠረዥ "ሐ")-----------60
የመወያያ ጥያቄዎች---------------------------------------68
2.2.1.5.4. ሌሎች ገቢዎች ታክስ (ሠንጠረዥ "መ")----------------68
የመወያያ ጥያቄዎች-------------------------------------71
2.2.1.6. የፍትሐብሔር ሐላፊነት የሚያስከትሉ
የገቢ ግብር ግዴታዎች--------------------------------------------72
የመወያያ ጥያቄዎች----------------------------------------------74
2.2.2. ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶች ---------------------------------------------------------74
2.2.2.1. ተጨማሪ እሴት ታክስ------------------------------------------------74
የመወያያ ጥያቄዎች---------------------------------------------87
2.2.2.2. ተርን ኦቨር ታክስ-----------------------------------------------------87
የመወያያ ጥያቄዎች-----------------------------------------------93
2.2.2.3. ኤክሳይስ ታክስ-------------------------------------------------------93

2.2.3. የቴምብር ቀረጥ------------------------------------------------------------------96
የመወያያ ጥያቄዎች--------------------------------------------------------------101
2.2.4. የታክስ ወንጀሎች----------------------------------------------------------102
የመወያያ ጥያቄዎች--------------------------------------------------------------104
2.2.5. የታክስ ይርጋ--------------------------------------------------------------104
የመወያያ ጥያቄ-----------------------------------------------------------------106

**ክፍል ሶስት፡- የታክስ ይግባኝ ሥረዓት እና አሰባሰብ አፈፃፀም**-------------------------107
መግቢያ------------------------------------------------------------------------------107
3.1. ይግባኝ ሥርዓት---------------------------------------------------------------108
3.1.1. አቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ--------------------------------------------------108
3.1.2. ግብር ይግባኝ ጉባኤ----------------------------------------------------109
3.1.3. የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት -------------------------------------------------111
የመወያያ ጥያቄዎች--------------------------------------------------------113
3.2. አሰባሰብ አፈፃፀም-------------------------------------------------------------116
የመወያያ ጥያቄዎች-----------------------------------------------------------------122

**ዋቢ ጽሑፎች**---------------------------------------------------------------------124

## የሞጁሉ መግቢያ

መንግሥት የዜጎችን የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ችግሮችን በአግባቡ የመፍታት ከፍተኛ ኃላፊነት አለበት፡፡ የዜጎችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ለመፍታት መንግስት የራሱ ገቢ (revenue) ሊኖረው ይገባል፡፡ መንግሥት ለዚህ አላማ የተለያዩ የገቢ ምንጮች ያሉት ወይም የሚፈጥር ነው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ አንዱና በዚህ ክፍለ ትምህርት የምንመለከተው ግብርን ወይም ታክስን ይሆናል፡፡ ታክስ የመንግሥት ዋነኛው የፋይናስ ምንጭ በመሆኑ ታክስ በሁሉም ሐገሮች የልማትና የእድገት ጀርባ አጥንት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ስለዚህ ማንኛውንም መንግስት የልማት አላማውን ሆነ ሌላ ማንኛውንም አላማ ለማሳካት የሚያስፈልገውን ወጪ ለመሸፈን ታክስ ይጥላል፣ ይሰበስባል፡፡

ስለታክስና ኢፌድሪ ሕገመንግስት ሰልጣኞች የተወሰነ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ለማስቻል ሞጁሉ ሶስት ክፍሎች እንዲኖሩት ተደርጎ ተዘጋጅቷል፡፡ በዚሁ መሰረት አንደኛው ክፍል በኢፌድሪ ሕገመንግሥት የተደነገገውን የታክስ ሥልጣን ክፍፍል የሚመለከት ነው፡፡

ሁለተኛው ክፍል የኢፌድሪ መንግስት ታክስ መዋቅር (Tax structure) የሚመለከት ነው፡፡ ይህም ክፍል የሞጁሉ ሰፊ ቦታ የሚይዝ ነው፡፡ ሶስተኛው እና የመጨረሻው ክፍል የታክስ ይግባኝ ሥርዓት እና አሰባሰብ አፈፃፀም የሚቀርብበት ይሆናል፡፡

በኢፌድሪ ህገመንግስቱን መሰረት በማድረግ የወጡ በርካታ የታክስ አዋጆችና ደንቦች አሉ፡፡ ይህ ሞጁል የተዘጋጀው በዋነኝነት እነዚህን አዋጆችና ደንቦች መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ሰልጣኞችም እነዚህን አዋጆችና ደንቦች ከየሥልጠና ማዕከሉ ያገኛሉ የሚል እምነት አለን፡፡

ይሔን ክፍለ ትምህርት ሲያጠናቅቁ ሰልጣኞች፡-

- በፌዴራል ሥርዓት የታክስ ሥልጣን እንዴት በሁለቱ የመንግስት እርከኖች መካከል መከፋፈል እንዳለበት ይገነዘባሉ፡፡

- በኢፌድሪ ሕገመንግስት የፌዴራልና የክልል መንግሥታት ታክስ የመጣልና የመሰብሰብ ሥልጣንን ገደብ ያውቃሉ፡፡
- የኢፌድሪ መንግሥት የታክስ መዋቅር አንድ በአንድ ለይተው ያውቃሉ፡፡
- ስለታክስና ስለቀረጥ አወሳሰን፣ አከፋፈል እና አሰባሰብ ይተነትናሉ፡፡
- የታክስ ከፋዮች ግዴታዎች እና መብቶች ያብራራሉ፡፡
- የታክስና የቀረጥ መክፈል ግዴታ አለመወጣት የሚያስከትለውን ሐላፊነት ያውቃሉ፡፡
- የታክስ ግዴታ በይርጋ የሚታገድበትን ሁኔታ ይረዳሉ፡፡
- ስለ ታክስ ይግባኝ ሥርዓት እና አሰባሰብ አፈፃፀም በቂ ግንዛቤ ይጨብጣሉ፡፡

# ክፍል አንድ

# የታክስ ሥልጣን ክፍፍል በኢፌድሪ ሕገመንግሥት

## መግቢያ

የማንኛውም ፌዴራል ሥርዓት መሰረታዊ ባህሪ የሥልጣን ክፍፍል ነው፡፡ በፌዴራል ሥርዓት የመንግሥት ሥልጣን (የሕግ አውጭ፣ ሕግ አስፈፃሚና ሕግ ተረጓሚ) በሁለቱ የመንግስት እርከኖች (Levels of government) ማለትም በፌዴራል መንግሥትና በክልል መንግሥታት መካከል የተከፋፈለ ነው፡፡ የስልጣን ክፍፍሉም በፌዴራሉ ሕገመንግሥት የሚዳነገግ በመሆኑ የሁለቱም የመንግሥት እርከኖች የስልጣን ምንጭ ይሔው ሕገመንግሥት ነው፡፡

ሁለቱም የመንግሥት እርከኖች እያንዳንዳቸው በህገመንግሥቱ ተለይቶ የተሰጣቸው ሥልጣንና ተግባር አሏቸው፡፡ ይህ በመሆኑ የፌዴራል መንግስት ወይም የክልል መንግስታት አንዱ የሌላው ተቀጽላ አይደለም፡፡ ይህ እውን ይሆን ዘንዳ ሁለቱም የመንግሥት እርከኖች በሕገ-መንግሥቱ የተሰጣቸውን ሥልጣንና ተግባር ለማከናወን የሚያስችላቸው የየራሳቸው የገቢ ምንጭ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

ከዚህ የተነሳ በማንኛውም የፌዴራል ሥርዓት ከመንግሥት ሥልጣን ክፍፍል ጋር መታየት ያለበት ቁልፍ ጉዳይ የገቢ ክፍፍል ነው፡፡ በዚሁ መሰረት በፌዴራል ሥርዓት የመንግሥት ሥልጣን በፌዴራል መንግሥት እና በክልል መንግሥታት መካከል እንደሚከፋፈል ሁሉ የገቢ ምንጮችም በሁለቱ የመንግስት እርከኖች መካከል መከፋፈል ይኖርባቸዋል፡፡ ይህን Basu የተባሉ ፀሐፊ፡-

> *Just as the legislative and executive powers have to be divided as between the federal and state governments so also the necessary financial powers must be divided under any federal constitution* በማለት ገልጸታል፡፡

በፌዴራል ህገመንግስት ክፍፍሉ የግድ ከሚላቸው የፋይናስ ሥልጣኖች ውስጥ አንዱ የታክስ ሥልጣን ነው፡፡ የኢፌድሪ ሕገመንግሥትም እንደ ማንኛውም ፌዴራላዊ ህገመንግሥት

የመንግሥትን ሥልጣን በሁለቱ የመንግሥት እርከኖች መካካል ከመከፋፈሉ በላይ የታክስ ሥልጣንንም በፌዴራል መንግሥትና በክልል መንግሥታት መካከል ከፋፍሏል፡፡

እንደማንኛውም ፌዴራላዊ ህገመንግስት የኢፌድሪ ህገመንግስት የታክስ ሥልጣን ክፍፍል ጋር መነሳት ያለባቸው ጥያቄዎች፡- የፌዴራል መንግስት በምን አይነት ታክሶች ላይ ታክስ የመጣልና የመሰብሰብ ሥልጣን ሊሰጠው ይገባል? የክልል መንግስታትም በምን አይነት ታክሶች ላይ ታክስ የመጣልና የመሰብሰብ ሥልጣን ሊሰጣቸው ይገባል? የሚሉት ናቸው፡፡ በሌላ አገላለጽ የታክስ ሥልጣን እንዴት በፌዴራልና በክልል መንግሥታት መካከል መከፋፈል አለበት? ክፍፍሉ በምን መርህ ላይ ተመስርቶ መከናወን አለበት? የሚሉት ናቸው፡፡ ለእነዚህ እና ሌሎች ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ስለታክስና የታክስ ሥልጣን ምንነትና ገጽታዎች እንዲሁም ስለታክስ ሥልጣን ክፍፍል መሠረታዊ መርሆችና ዘዴዎችን በመጀመሪያ መታወቅ ይኖርባቸዋል፡፡

ይህ ክፍል አምስት ንዑስ ክፍሎች አሉት፡፡ የመጀመሪያው ንዑስ ክፍል ስለታክስ አንዳንድ አጠቃላይ ሐሳቦች የሚቀርቡበት ነው፡፡ በሁለተኛው ንዑስ ክፍል በፌዴራል ሥረአት የታክስ ሥልጣን ክፍፍል መሰረታዊ መርሆች እና ዘዴዎች፣ በንዑስ ክፍል ሶስት የታክስ ሥልጣን ክፍፍል በኢፌድሪ ሕገመንግስት፣ በንዑስ ክፍል አራት ደግሞ በሕገመንግስቱ ተለይተው ያልተሰጡ የታክስ ሥልጣኖችን የሚቀርቡበት ይሆናል፡፡ የታክስ ሥልጣን የመጨረሻው ንዑስ ክፍል የታክስ ሥልጣን ገደቦችን የሚመለከት ነው፡፡

ይህን ክፍል ሲያጠናቅቁ ሰልጣኞች፡-

- ታክስና የታክስ ሥልጣን ምንነትና ገፅታዎች ያውቃሉ፡፡
- ስለፌዴራል ሥርዓት የታክስ ሥልጣን ክፍፍል መሰረታዊ መርሆችና ዘዴዎች በቂ ግንዛቤ ይኖራቸዋል፡፡
- በኢፌድሪ ሕገመንግስት የፌዴራልና የክልል መንግሥታት የታክስ መጣል ሥልጣን ይዘረዝራሉ፡፡
- በኢፌድሪ ሕገመንግስት የፌዴራልና የክልል መንግሥታት የታክስ የመሰብሰብ ሥልጣን ይተነትናሉ፡፡

- በሕገመንግስቱ የተደነገገውን የታክስ ሥልጣን ክፍፍል ይገመግማሉ፣ ይመዝናሉ፡፡ ከሌሎች ሐገሮች ጋር ያነፃፀራሉ፡፡
- ስለታክስ አጣጣል የተደነገጉ ሕገመንግስታዊ የታክስ ሥልጣን ገደቦችን ይረዳሉ፡፡

## 1.1. ታክስ በአጠቃላይ

### 1.1.1. ምንነት

ብዙ ፀሐፊዎች ታክስን በተለያየ መንገድ ገልፀውታል፡፡ ለምሳሌ እንደ Seligman፡ "A tax is a compulsory contribution from the person to the government to defray expenses incurred in the common interest of all with out reference to special benefit conferred" በማለት ይገልጸዋል፡፡

ትርጉሙም በጭሩ፡-ታክስ ማለት መንግስት ለጠቅላላው ህብረተሰብ ጥቅም የሚያደርጋቸውን ወጪዎች ለመሸፈን እንዲችል ማንኛውም ታክስ ከፋይ በተለይ በግል የልዩ ጥቅም ጥያቄ ሳያነሳ መክፈል ያለበት በሕግ የተጣለ የግዴታ ክፍያ ነው፡፡ ከዚህ ትርጉም መረዳት እንደሚቻለው፡-

- ታክስ በሕግ የተጣለ ግዴታ ነው፡፡ ይህ በመሆኑ ታክስ መክፈል በገዛ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ሳይሆን አስገዳጅነት ባህሪ ያለው ነው፡፡ ታክስ እንዲከፈል ግዴታ አለመወጣት የወንጀል ተጠያቂነት ያስከትላል፡፡
- ታክስ የሚጣለው በመንግስት ነው፡፡ ማንም ሰው ታክስ የመጣል መብት የለውም፡፡ የመንግስት ብቻ ነው ታክስ የመጣልና መሰብሰብ ህጋዊ መብት ያለው፡፡
- ታክስ የሚከፈለው በታክስ ከፋይ ነው፡፡ ታክስ ከፋዩ የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ሊሆን ይችላል፡፡
- ታክስ የሚጣለውና የሚሰበሰበው ለጠቅላላው ሕብረተሰብ ጥቅም ነው፡፡ ስለዚህ መንግስት በሚያወጣው ወጪ ተጠቃሚ የሚሆነው ታክስ ከፋዩ ብቻ ሳይሆን ታክስ ከፋይ ያልሆነውም ሊሆን ይችላል፡፡
- ታክስ ከፋዩም ለከፈለው ታክስ ከመንግስት በቀጥታ በግሉ ልዩ ጥቅም የመጠየቅ መብት የለውም፡፡ ማለትም በሚከፈለው ታክስ እና መንግስት በሚሰጠው አገልግሎት መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት የለም፡፡ ስለዚህ አንድ ሰው ታክስ የሚከፍለው ከመንግስት ቀጥተኛ

እና እኩል የሆነ ጥቅም ስለሚያገኝ ሳይሆን መንግስት ለሚያከናውናቸው ተግባሮች እገዛ የማድረግ ግዴታ ጭምር ስላለበት ነው፡፡

### 1.1.2. አላማ

መንግስት ታክስን የሚጥለውና የሚሰበስበው የተለያዩ አላማዎች ለማስፈፀም ነው፡፡ ጥቂቶቹም፡-

- **ገቢን ለመፍጠር፡** መንግስት ለጠቅላላው ሕብረተሰብ ጥቅም የሚያደርጋቸውን ወጪዎች ለመሸፈን የሚያስችለው ገቢ ያስፈልገዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ አንዱ የገቢ ምንጭ ታክስ ነው፡፡ የታክስ ዋና አላማም የመንግስት ገቢን መፍጠር ነው፡፡
- **የገቢ እና የሐብት ልዩነትን መቀነስ**፡- በሐብታምና በደሀ መካካል ያለውን ልዩነትን ለማጥበብ ብዙ መንግስታት እየጨመረ የሚሔደው የታክስ ሥርዓት (Progressive taxation system) ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡ በዚህ አይነቱ የታክስ ሥርዓት ውስጥ ከፍተኛ ገቢ የሚያገኙ ሰዎች ከፍ ያለ ታክስ እንዲከፍሉ ይደረጋሉ፡፡ መካካለኛ ገቢ የሚያገኙት ደግሞ ዝቅ ያለ ታክስ ይከፍላሉ፡፡ ዝቅተኛ ገቢ የሚያገኙ ሰዎች ደግሞ ከታክስ መክፈል ነፃ ሊደረጉ ይችላሉ፡፡ ከፍተኛ ገቢና መካካለኛ ገቢ ከሚያገኙ ሰዎች የተሰበሰበውን ታክስ መንግስት ዝቅተኛ ገቢ የሚያገኙ ሰዎች ወይም ምንም ገቢ የሌላቸው ወይም ሥራ አጦችን ለመደጎም ያውለዋል፡፡
- **ኢኮኖሚን ለማረጋጋት**፡- መንግስት ታክስን ኢኮኖሚን ለማረጋጋት አላማ ሊጠቀምበት ይችላል፡፡ መንግስት ታክስን በመጠቀም የዋጋ ግሽበት እና የኢኮኖሚ መቀዝቀዝን ለመቆጣጠር ሊጠቀምበት ይችላል፡፡ ይሔንንም እውን የሚያደርገው እንደ ሁኔታው የታክስ ማስከፈያ መጠን (tax rate)በመጨመር ወይም በመቀነስ ወይም አዲስ ታክስ በመጣል ወይም የተወሰኑ ታክሶችን በማንሳት ሊሆን ይችላል፡፡
- **ጎጂ ወይም መሰረታዊ ያልሆኑ ምርቶችና ፍጆታ መቀነስ፡** በሕብረተሰቡ ጤና ላይ ችግር የሚያስከትሉ ምርቶች ወይም መሰረታዊ ያልሆኑ ምርቶቾ ፍጆታ ለመቀነስ መንግስት ታክስን አንዱ መሳሪያ አድርጎ ሊጠቀም ይችላል፡፡ ይሔንንም ብዙን ጊዜ ተግባራዊ የሚያደርገው በተመረጡ ምርቶች ላይ ከፍተኛ ታክስ በመጫን ነው፡፡ ለዚህ አላማ የሚጣለው የታክስ አይነተ አክሳይስ ታክስ የሚባለው ነው፡፡ በሕብረተሰቡ ጤና ላይ ችግር የሚያስከትሉ ምርቶች ወይም መሰረታዊ ያልሆኑ ምርቶቾ ላይ ከፍተኛ ታክስ

መጣል ዋጋቸው እንዲጨምር ስለሚያደረግ አብዛኛው ሰው እነዚህን ምርቶች ከመግዛት ሊቆጠብ ይቻላል የሚል እምነት አለ፡፡

- **ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት፡** መንግስት ኢንቨስትመትን ለማበረታታት የተለያዩ እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል፡፡ አንዱ ከታክስ ጋር በተያያዘ የሚወስደው እርምጃ ነው፡፡ መንግስት ልዩ ትኩረት የሚገባቸውን የሥራ መስኮችን ለማበረታታት በመስኮቹ ላይ የሚጣለውን ታክስ ሊቀነስ ወይም ለተወሰነ ጊዜ ከታክስ ነፃ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡
- **የሐገር ውስጥ ፋብሪካዎች እና ምርቶች ጥበቃ ለማድረግ፡-** መንግስት የተለያዩ የሀገር ውስጥ ፋብሪካዎች ወይም ምርቶች ጥበቃ ለማድረግ ታክስ ሊጥል ይችላል፡፡ ለዚህ አላማ ተገቢውን የታሪፍ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡
- **ውጪ ንግድ ለማበረታታት፡-** መንግስት ውጪ ንግድን ለማበረታታት ወደ ውጪ የሚላኩ እቃዎችን ወይም ምርቶች ከታክስ ነፃ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡ ይህ ደግሞ ምርቶች በውጭ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡

### 1.1.3. መዋቅር

የታክስ መዋቅር ማለት በአንድ ሀገር ውስጥ የሚጣሉ እና የሚሰበሰቡ የታክስ ዓይነቶች ማለት ነው፡፡ በሀገሮች መካከል ባለው የኢኮኖሚ፤ ፖለቲካ እና ማህበራዊ ልዩነቶች የተነሳ ሀገሮች የተለያዩ የታክስ መዋቅር አሏቸው፡፡ ይህ ማለት ግን ምንም ዓይነት ተመሳሳይነት የላቸውም ማለት አይደለም፡፡ ለምሳሌ የገቢ ታክስ፤ ኤክሳይዝ ታክስ፤ተጨማሪ እሴት ታክስ እና የጉምሩክ ቀረጥ በብዙ ሀገሮች የሚጣሉ እና የሚሰበሰቡ የታክስ አይነቶች ናቸው፡፡

ብዙ ፀሐፊዎች የታክስ አይነቶችን በተለያየ መደብ ይከፋፍላሉ፡፡ በተለይ ታክሶችን ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ብሎ መከፋፈል የተለመደ ነው፡፡ ታክሶችን ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ብሎ ለመከፋፈል እንደ መሰረት ሆኖ የሚያገለግለው ታክሱን የመክፈል የመጀመሪያው ሸክም እና የመጨረሻው ሸክም ማን ላይ ያርፋል ለሚለው ጥያቄ የሚሰጠው መልስ ነው፡፡

ይሔንኑ በመተራስ ዳልተን የተባለ ጸሐፊ ቀጥተኛ ታክሶችን "…..are those which are paid entirely by those persons on whom they are imposed. Direct taxes are those taxes which can not be shifted to others" በማለት ባአጭሩ ይገልጻቸዋል፡፡ ከዚህ ትርጉም ቀጥተኛ

ታክሶችን በተመለከተ ታክስ የመክፈል የመጀመሪያው ሆነ የመጨረሻው ሸክም የሚያርፈው በአንድ ሰው ላይ መሆኑን መረዳት ይቻላል። በሌላ አባባል ታክሱ የመክፈል ሸክም ወደ ሌሎች ሰዎች አይሻገርም ወይም በሌሎች ሰዎች ላይ አያርፍም ማለት ነው። ታክሱ የሚከፈለው በቀጥታ ታክስ በተጣለበት ሰው ነው። ከቀጥተኛ ተክሶች ውስጥ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ላይ የሚጣል ታክስ፣ የንግድ ሥራ ትርፍ ግብር፣ ከቤት ኪራይ በሚገኝ ገቢ ላይ የሚጣል ታክስ፣ በወለድ ላይ የሚከፈል ገቢ ታክስ፣ የንብረት ታክስ፣ የእርሻ ገቢ ታክስ፣ የውርስ ታክስ፤ የስጦታ ታክስን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል።

በሌላ በኩል ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶችን በተመለከተ ታክሶቹን የመክፈል የመጀመሪያው እና የመጨረሻው ሸክም የሚያርፈው በአንድ ሰው ላይ ሳይሆን በተለያዩ ሰዎች ላይ ነው። በዚህ መሰረት ታክሱን የመክፈል የመጀመሪያው ሸክም የሚወድቀው አግባብ ባለው ህግ ውስጥ ታክስ ከፋይ ተብሎ በተጠቀሰው ታክስ ከፋይ ላይ ሲሆን የመጨረሻው ሸክም የሚወድቀው ደግሞ በሸማቹ ላይ ነው። ይህም ማለት አግባብ ባለው ህግ ውስጥ ታክስ ከፋይ ተብሎ የተጠቀሰው ሰው የከፈለውን ታክስ በዋጋ መልክ የታክስ ሸክሙን ወደ ሸማቹ እንዲሻገር ያደርጋል ማለት ነው። ቀጥተኛ ካልሆኑ ታክሶች ውስጥ የሽያጭ ታክስ፣ ተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ተርን ኦቨር ታክስ፣ኤክሳይዝ ታክስ፣ የጉምሩክ ቀረጥን በምሳሌነት መጥቀስ ይችላል።

ሌሎች ፀሐፊዎች የታክስ አይነቶችን የገቢ ታክስ፣ የንብረት ታክስ እና የcommodity ታክስ ብለው ይከፋፍላሉ። ይሔም ክፍፍል የታክስ መሰረትን መሰረት ያደረገ ነው። የታክስ መሰረት (tax base) ማለት ታክሱ የሚጣልበት ነገር ማለት ነው። ማንኛውም ታክስ የታክስ መሰረት አለው። የታክስ መሰረት ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ፤ የንግድ ሥራ ትርፍ ገቢ፤ አንድ ሰው እቃ ወይም አገልግሎት ለመግዛት የሚያወጣው ገንዘብ፤ በውርስ የተገኘ ሀብት መጠን ወ.ዘ.ተ ሊሆን ይችላል።

በሌላ በኩል የንብረት እና የcommodityታክሶች የምንላቸው ደግሞ ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶችን ተብለው ከላይ የተጠቀሱ የታክስ አይነቶችን የሚመለከቱ ናቸው። ሐገሮች እንደ ሐገራቸው ሁኔታ የታክስ አይነቶችን በተለያዩ መንገድ ሊከፋፍሉ ይችላሉ።

## 1.2. የታክስ ሥልጣን ክፍፍል በፌዴራል ሥረዓት

### 1.2.1. የታክስ ሥልጣን ምንነት

የታክስ ሥልጣን በተለያዩ መንገዶች ሊገለጽ ይችላል፡፡ ለምሳሌ Coke የተባለ ፀሓፊ የታክስ ሥልጣንን፡-

> *"It is an inherent sovereign power of a state to collect contribution of money or other property from its citizens and the inhabitants of its territory for defraying its general expenditure"* በማለት ይገልጸዋል፡፡

ከዚህ ትርጉም መረዳት እንደሚቻለው የታክስ ሥልጣን አንድ ሉአላዊ መንግሥት በመንግሥትነቱ የሚኖረው ሥልጣን ነው፡፡ ይህ በመሆኑ ሁሉም ሉአላዊ መንግሥታት የታክስ ሥልጣን አሏቸው ለማለት ይቻላል፡፡ ሕገመንግሥታዊ ድንጋጌዎች በታክስ ሥልጣን ላይ የተለያዩ ገደቦችን ሊጥሉ ቢችሉም ሕገመንግሥቱ ከሚጥላቸው ገደቦች ውጪ የአንድ ሉአላዊ መንግሥት የታክስ ሥልጣን ገደብ የለሽ ነው ለማለት ይቻላል፡፡
ሆኖም ግን የአንድ ሉአላዊ መንግሥት የታክስ ሥልጣን ወሰን ከሉአላዊ መንግሥት ግዛት ክልል የሚያልፍ አይደለም፡፡ ስለዚህ በመርህ ደረጃ የአንድ ሉአላዊ መንግሥት የታክስ ሥልጣኑን ተግባራዊ ሊያደርግ የሚችለው በግዛቱ ክልል ውስጥ በሚገኙ ሰዎች፣ ንብረቶችና የንግድ እንቅስቃሴዎች ላይ ብቻ ነው፡፡

የታክስ ሥልጣንም መንግሥት በሕብረተሰቡ ውስጥ የተለያዩ ተግባሮችን ለማከናወን የሚያስፈልገውን ወጪዎችን ለመሸፈን የሚያስችለውን ገቢ ለመፍጠር የሚያገለግል ነው፡፡ ታክስ የሚጣለውም በሕግ ብቻ ነው፡፡ ሕጎችን በማውጣት መንግሥት ወጪውን ለመሸፈን የወጪ ሸክሙን መሸከም ባለባቸው መካከል እንዴት መከፋፈልና መሰብሰብ እንዳለበት ይወሰናል፡፡ ይህ በመሆኑ የታክስ ሥልጣን ሕግ ማውጣት ባህሪ ያለው ነው፡፡ ስለዚህ በአንድ ሀገር ታክስ የሚጣለው ሕግ ለማውጣት ሥልጣን ባለው የመንግሥት አካል ነው፡፡ ለምሳሌ ፓርላሜንተሪ የመንግሥት መዋቅር ባላቸው ሀገሮች ታክስ የመጣል ሥልጣን ለፓርላማው የተሠጠ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ አንድ ፀሀፊ፡-

> *A tax must not only be imposed by a Government; but also the legislative department of government. No tax can be imposed by the executive department of a government or by the courts* በማለት

የታክስ ሥልጣን የሕግ አውጪው የመንግሥት አካል ብቻ መሆኑን በአጭሩ አስቀምጦታል፡፡

በኢፌድሪ ህገመንግስት የፌዴራል መንግሥት ህግ አውጪው አካል የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፤ የክልሎች ዳግም የክልል ም/ቤቶች በመሆኑ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለፌዴራል መንግሥት በተመለከተው ገቢ ምንጭ ክልል፤ የክልል ም/ቤቶች ዳግም ለክልሎች በተመለከተው ገቢ ምንጭ ክልል ታክስ የመጣል ሥልጣን አሏቸው፡፡ (አንቀጽ 55(11)) ህግ አስፈፃሚው እና ህግ ተርጓሚው አካል ግን ታክስ የመጣል ሥልጣን የላቸውም፡፡

## 1.2.2. የታክስ ሥልጣን ገፅታዎች

የታክስ ሥልጣን ሶስት ገፅታዎች አሉት፡፡ አንደኛው የሕግ ማውጣት ነው፡፡ ይህ የታክስ ሥልጣን ገጽታ መሰረታዊ ሕጎችን በመደንገግ ታክስን መጣል የሚመለከት ነው፡፡ ይህ የታክስ ሥልጣን ገጽታ የበለጠ ለመረዳት ከታክስ ጋር በተያያዘ መጣል (levy) የሚለው ቃል ትርገሙን ማየት ጠቀሜታ አለው፡፡ ብላክስ ሎው ዲኪሺነሪ መጣል (levy) የሚለውን ቃል፡-

> "… the legislative function and declaration of the subject and rate or amount of taxation… Exercise of legislative function … determining that a tax shall be imposed and fixing amount, purpose and subject of taxation.." በማለት ይፈተዋል፡፡

ታክስ መጣል ህግ ማውጣት ተግባር መሆኑንና ይህም ተግባር ታክስ እንዲጣል መወሰን፤ የታክሱን አላማ እንዲሁም ታክስ የሚጣልበትን ነገር እና ማስከፈያውን መጠን... መወሰንን የሚመለከት መሆኑን ከዚህ ትርጉም መረዳት ይቻላል፡፡

ሁለተኛው ገፅታ ታክስ መሰብሰብ ነው፡፡  ይህ የታክስ ሥልጣን ገፅታ የተጣሉትን ታክሶች የታክስ ህጉን በማስፈጸም የመሰብሰብ ሥልጣንን የሚመለከት ነው፡፡ ሶስተኛው ገፅታ መጠቀም ነው፡፡ ይህ የታክስ ሥልጣን ገፅታ የተሰበሰበው የታክስ ገቢ መጠቀምን ወይም ከታክሱ ከሚገኘው ገቢ ተጠቃሚ የመሆን መብትን የሚመለከት ነው፡፡

በብዙ ሐገሮች የታክስ ሥልጣን ይዘት እነዚህን ሶስት ገጽታዎች የያዘ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ሕግ አውጪው አካል ታክስን በተመለከተ ሰፊ ሥልጣን (discretion) ያለው መሆኑን መረዳት ይችላል፡፡ ሕግ አውጪው ከታክስ ጋር ተያያዥነት ባላቸው የተለያዩ ወሳኝ ጉዳዮች ላይ የመወሰን ሥልጣን አለው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ አንዱ አንድ የተወሰነ የታክስ መጣል አለበት ወይስ የለበትም በሚለው ላይ ውሳኔ መስጠት ነው፡፡ ሕግ አውጪው ሥልጣን በዚህ ላይ ብቻ የተገደበ ሳይሆን የሚጣለው የታክስ አይነት ማስከፈያው መጠን፤ አተማመን ዘዴን፤ መክፈያ ጊዜ፤ አሰባሰብ መንገድና አፈፃፀሙ ምን ወይም እንዴት መሆን አለበት እስከ መወሰን የሚሔድ ነው፡፡

1.2.3. **መርሆች**

በፌዴራል ሥረዓት የታክስ ሥልጣን ክፍፍል በምን መርህ ላይ መመስረት አለበት ለሚለው ጥያቄ ወጥ የሆነ መልስ የለም፡፡ የታክስ ሥልጣን ክፍፍሉም እንደ ሐገሩ ተጨባጭ ሁኔታ ይለያያል፡፡ ሆኖም ግን ያሉት ልዩነቶች እንደተጠበቁ ሆነው በአብዛኞዎቹ የፊዚካል ፌዴራሊዝም ፀሐፊዎች ዘንድ በተወሰኑ መርሆች ላይ ከሞላ ጉደል መግባባት አለ ለማለት ይቻላል፡፡ እነዚህ መግባባት የተደረሰባቸው መርሆች በይበልጥ አሰተዳደራዊ አመቺነት እና ቅልጥፍናን መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ ከእነዚህ መርሆች ውስጥ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

**ኢኮኖሚን ለማረጋጋት የሚረዱ ታክሶች፡-** በፌዴራል ሥርዓት የሐገሪቱን አጠቃላይ ኢኮኖሚ የመቆጣጠር ሥልጣን የፌዴራል መንግስት ነው፡፡ ይህ ስልጣን የፌዴራል መንግስት የተሰጠ በመሆኑ ኢኮኖሚን ለማረጋጋት ሚና ያላቸው ታክሶች ለማከላዊ መንግስት መሆን አለባቸው፡፡ (Taxes suitable for economic stabilization should be central) ይሄም ማእከላዊ መንግስት ወይም ፌዴራል መንግስት በሕገ መንግስቱ ከሚኖረው ሐላፊነትና ተግባር ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በዚህ መርህ መሰረት የኩባንያ እና ተጨማሪ እሴት ታክሶችን የመጣል ሥልጣን ለፌዴራል መንግስት፤ የግል ገቢ ታክስ እና የችርቻሮ የሽያጭ ታክስ ደግሞ ለክልሎች መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

**ገቢን ለማመጣጠን አመቺ የሆኑ ታክሶች፡-** መንግስት በሐገሪቱ ዜጎች መካከል ፍታሐዊ የሆነ የገቢ ክፍፍል እንዲኖር የማደረግ ሐላፊነት አለበት፡፡ በፌዴራል ሥርዓት ደግሞ ይህ ሐላፊነት

በተለይ የፌዴራል መንግስቱ ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ መርህ መሰረት ገቢን ለማመጣጠን የሚረዱ ታክሶችን የመጣል ሥልጣን ለፌዴራሉ መንግስት መስጠት እንዳለባቸው ነው፡፡ (Taxes suitable for income redistribution should be central)

**መሰረታቸው ቋሚ የሆኑ ታክሶች፡-** መሰረታቸው ቋሚ የሆኑ ታክሶች ለክልል መንግስት መተው አለባቸው፡፡ (Tax bases with low mobility should be regional) ለዚህ ደግሞ የመሬት ታክስን መጥቀስ ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል የታክስ መሰረታቸው ክልል ዘለል የሆኑ የታክስ መሰረቶች ለፌዴራል መንግስት መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡

**የታክስ መሰረታቸው ሥርጭት በሁሉም ቦታ እኩል ያልሆኑ ታክሶች፡** የታክስ መሰረታቸው ሥርጭት በሁሉም ቦታ እኩል ያልሆኑ ታክሶች ለፌዴራል መንግስት መስጠት አለባቸው፡፡ (Tax bases distributed very unequally between jurisdictions should be centralized) ይህ መርህ ይበልጥ የሚመለከተው የተፈጥሮ ሀብትን ነው፡፡ የተፈጥሮ ሀብት በሁሉም ክልሎች በእኩል መጠን አይገኝም፡፡ ይህ ደግሞ በክልል መንግስታት መካከል ከፍተኛ የኢኮኖሚ ልዩነት እንዲኖር ያዳርጋል፡፡ ከፍታዊነት አንጻር ሲታይ ከተፈጥሮ ሀብት ከሚገኘው ጥቅም ተጠቃሚ መሆን ያለበት የተፈጥሮ ሀብቱ የሚገኝበት ክልል ብቻ ሳይሆን ሁሉም የፌደሬሽኑ አባላት መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ ያለው አማራጭ የተፈጥሮ ሀብትን በተመለከተ የታክስ ሥልጣኑ ለክልል መንግስት ሳይሆን ለፌዴራል መንግስት መስጠት ነው፡፡ የፌዴራል መንግስትም ከተፈጥሮ ሐብቱ የሚሰበሰበውን የታክስ ገቢ ሁሉም ክልል ተጠቃሚ እንዲሆን የማድረግ ሐላፊነት አለበት፡፡

በሌላ በኩል የተፈጥሮ ሐብቱ በሚገኝበት አካባቢ ያሉ ነዋሪዎች የተፈጥሮ ሐብቱን በተመለከተ የይገባናል ስሜት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ የተፈጥሮ ሐብት የይገባናል ጥያቄ ፖለቲካዊ ይዘትም ሊኖረው ይችላል፡፡ ይሄን ተንተርሶ የሚነሳው ጥያቄ የፌዴራል ሥርዓቱን ሕልውና ሊፈታተን ይችላል፡፡ ከዚህ የተነሳ የተለያዩ ፌደሬሽኖች ከተፈጥሮ ሐብት የሚያገኘውን የታክስ ገቢ ክፍፍል በተመለከተ የተለያዩ አማራጮች ወስዳዋል፡፡ ለምሳሌ በቀድሟ ሩሲያ ፌደሬሽን ከተፈጥሮ ሐብት የሚገኘውን የታክስ ገቢ የተፈጥሮ ሐብቱ ለሚገኝበት ክልል በማካፈል ችግሩን ለመፍታት ተሞክሯል፡፡

በአጭሩ ከተፈጥሮ ሐብት በሚገኘው ገቢ ላይ የትኛው የመንግስት እርከን ታክስ ሥልጣን ሊኖረው ይገባል የሚለው ጥያቄ አስተዳደራዊ አመቺነት እና ቅልጥፍናን ብቻ መሰረት አድርጎ የሚወሰን አይደለም፡፡ የተፈጥሮ ሐብትን በተመለከተ የታክስ ሥልጣን ክፍፍሉ ለሐገሪቱ ኢኮኖሚ የሚኖረውን ጠቀሜታ፣ በፌዴራል ሥረዓቱ ሕልውና ላይ ያለውን ተጽእኖ እና የተፈጥሮ ሐብቱ ባለበት አካባቢ የሚኖሩ ነዋሪዎችን ስሜትና ፍላጎት ከግምት ውስጥ ማስገባትን የሚጠይቅ ነው፡፡

**የአገልግሎት ታክሶችን እና ክፍያዎችን፡-** የአገልግሎት ታክሶች እና ክፍያዎች የመጣልና የመሰበሰብ ሥልጣን ለሁለቱም የመንግስት እርከኖች ሊሰጥ ይችላል፡፡ (Benefit taxes and charges might be appropriately used at all levels).

በአጠቃላይ በፌዴራል ሥረዓት የታክስ ሥልጣን ክፍፍል እንደ ሁኔታው አስተዳደራዊ አመቺነት፣ ቅልጥፍናን፣ የታክስ ክልላዊ ወይም ብሔራዊ ባህሪ፣ የታክሱ ምንጭ ባለቤትነት እና ሌሎች ነጥቦችን ከግምት ውስጥ ማስገባትን የሚጠይቅ ነው ለማለት ይቻላል፡፡

### 1.2.4. ዘዴዎች ( Methods )

በንድፈ ሐሳብ ደረጃ ሶስት አይነት ሕገመንግሥታዊ የታክስ ሥልጣን ክፍፍል ዘዴዎች አሉ፡፡ አንደኛው ሁሉንም የታክስ ሥልጣን ለፌዴራል መንግሥት መስጠት ነው፡፡ ሕግመንግሥቱ ሁሉንም የታክስ ሥልጣን ለፌዴራል መንግሥት የሚሰጥ ከሆነ የክልል መንግሥታት ሙሉ በሙሉ በፌዴራል መንግሥት ላይ ጥገኛ ይሆናሉ፡፡ ይህ አማራጭ በፌዴራል ሥረዓት ሥልጣንና ኃላፊነት ያልተማከለ መሆን አለበት የሚለው መርህ የሚጋፋ በመሆኑ ብዙም ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ሁለተኛው የአንደኛው ዘዴ ተቃራኒ ሲሆን ይህም ሁሉንም የታክስ ሥልጣን ለክልል መንግሥታት የሚሰጥ ነው፡፡ በዚህ ዘዴ መሰረት ሕገመንግሥቱ ሁሉንም የታክስ ሥልጣን ለክልል መንግሥታት የሚሰጥ ከሆነ ክልሎች የገቢያቸውን የተወሰነ መጠን ወደ ፌዴራል መንግሥት ወደ ላይ እንዲያዞሩ(upward revenue sharing) የሚጠይቅ ነው፡፡ ይህ አማራጭ

ዘዴ የፌዴራል መንግሥቱ በታክስ ፖሊሲ ማከናወን የሚገባውን ተግባሮች ማለትም የገቢ ክፍፍል (Income redistribution)፣ኢኮኖሚ ማረጋጋትና እና የታክስ ማዋሐድን እንዳያከናውን ስለሚያደርገው ተቀባይነቱ እምብዛም አይደለም፡፡ በተጨማሪም በክልሎች መካከል የኢኮኖሚ ልዩነት ባለ ጊዜ የክልል መንግሥታት በፌዴራል መንግሥቱ ውስጥ ከመሳተፍ ወደ ኃላ እንዲሉ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡

ሶስተኛው ዘዴ የታክስ ሥልጣኑን በሁለቱ የመንግሥት እርከኖች መካካል የሚከፋፈል ነው፡፡ ይህ በአብዛኛው የፌዴራል ሥርዓት ተከታይ ሐገሮች ሕገመንግሥት ተቀባይነት ያገኘ የታክስ ሥልጣን ክፍፍል ዘዴ ነው፡፡ የታክስ ሥልጣንን በሁለቱ የመንግስት እርከኖች መካከል እንዲከፋፈል የሚያደርገው ዘዴ በስሩ ሶስት ንዑስ ክፍሎች አሉት፡፡ አንደኛው ብቸኛ የታክስ ሥልጣን ነው፡፡ ሕገመንግስቱ የተወሰነ የታክስ ምንጮች ለፌዴራልና ለክልል መንግሥታት ብቻ ለብቻ ለያይቶ ሊሰጥ ይችላል፡፡ የፌዴራል መንግሥት ወይም የክልል መንግሥታት በተለያዩ ነገሮች ፣የንግድ ሥራዎች ወይም ሰዎች ላይ ራሱን የቻለ የታክስ ሥልጣን ያላቸው ከሆነ ይሔ ብቻኛ የታክስ ሥልጣን ይባላል፡፡ ብቸኛ የታክስ ሥልጣን አጠቃላይ የህግ ማውጣት ሥልጣን ክፍፍልን ሊከተል ይችላል፡፡ ይህም በመርህ ደረጃ እያንዳንዱ የመንግሥት እርከን በራሱ ህገ ማውጣት ሥልጣን ክልል ውስጥ በሚወድቁ የገቢ ምንጭ መሰረቶች ላይ ማንኛውንም አይነት ታክሶችን ሊጥል ይችላል፡፡

ሁለተኛው የጋራ የታክስ ሥልጣን (concurrent power of taxation) ነው፡፡ ሕገመንግሥቱ ሁለቱም የመንግሥት እርከኖች የተወሰኑ የታክስ አይነቶች ወይም ሁሉንም የታክስ አይነቶች በተመለከተ ሕግ ማውጣት፣ መሰብሰብና የሚሰበሰበውን ገቢ የመጠቀም ሥልጣን ሊሰጣቸው ይችላል፡፡ የፌዴራል መንግሥት እና የክልል መንግሥት በተመሳሳይ የንግድ እንቅስቃሴዎች ወይም የተወሰነ ነገር ላይ ታክስ የመጣል እኩል ሕገመንግስታዊ ሥልጣን ያላቸው ከሆነ የታክስ ሥልጣኑ የጋራ ነው ለማለት ይቻላል፡፡

በመርህ ደረጃ እያንዳንዱ የመንግሥት እርከን የታክስ ሥልጣኑን ራሱን ችሎ ተግባራዊ የማድረግ መብት አለው፡፡ ነገር ግን የፌዴራል ሥረዓት ተከታይ ሐገሮች ሕገመንግስት

የተለያዩ የጋራ ታክስ ሥልጣን ይደነግጋሉ፡፡ ለምሳሌ የጋራ የታክስ ሥልጣን የካናዳ፣ የአሜሪካና የሕንድ ሕገመንግስት አይነተኛ ባህሪ ነው፡፡

በካናዳ ሕገመንግሥት  የክልል መንግሥታት የታክስ ሥልጣን ቀጥተኛ በሆኑ ታክሶች ላይ ብቻ ነው፡፡ በሌላ በኩል የፌዴራል መንግሥት ታክስን በመጠቀም ማንኛውንም ገቢ መፍጠር እንደሚችል ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡ ስለዚህ ቀጥታኛ ታክሶችን በተመለከተ የፌዴራል መንግሥትና የክልል መንግሥታት የጋራ የታክስ ሥልጣን አሏቸው ማለት ነው፡፡

ከሌሎች ፌደሬሽኖች ጋር ሲነፃፀር የአሜሪካ ህገመንግሥት ሰፊ የጋራ ታክስ ሥልጣን ይደነገጋል፡፡ ለምሳሌ በሕገመንግስቱ ሁለቱም የመንግሥት እርከኖች በግለሰብ እና በኩባኒያ ኮርፐሮቲ ገቢ፣ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ (payroll) እና ኤክሲይዝ ታክስን በሞተር ዘይት፣ አልኮል እና የትንባሆ ምርቶች ላይ የታክስ ሥልጣን አሏቸው፡፡ በሕገመንግሥቱ እኩል የታክስ ሥልጣን መሰጠቱ የታክስ መደራረብን እና የፌዴራል እና የክልል ታክስ ሕጎች መቃረንን ይፈጥራል፡፡ የፌዴራል ሕግ በላይነት ይህን ችግር ይፈታዋል፡፡ በሕንድ የገቢ ታክስ፣ የውርስ ታክስ፣ ኤክሳይዝ ታክስ፣ በማስታወቂያ ላይ የሚጣል ታክስና የንብረት ታክስ የጋራ ታክስ ናቸው፡፡

የአንዳንድ ፌዴሬሽን ሕገመንግሥት የፌዴራል መንግሥት የክልል መንግሥታትን የጋራ ታክስ ሥልጣን እንዲቋረጥ ማድረግ የሚችልበትን ሁኔታ ይደነግጋል፡፡ ለምሳሌ የጀርመን ህገመንግሥት መጥቀስ ይቻላል፡፡ በጀርመን የሁለቱ የመንግስት እርከኖች የጋራ ነው በተባሉ ጉዳዮች ለይ በጋራ ሕግ ማውጣት ሥልጣን አሏቸው፡፡ ሆኖም ግን የፌዴራል መንግስት በሕገመንግስቱ የጋራ ሥልጣን ነው በተባሉ ጉዳዮች ላይ ሕግ የሚያወጣው ሕግ ማውጣቱ ብሔራዊ ፋይዳ ካለውና በሙሉ በሐገሪቱ እኩል የሆነ የኑሮ  ሁኔታንና ኢኮኖሚ አንድነትን ለመፍጠር አስፈላጊ ሲሆን ነው፡፡ በሌላ በኩል የጋራ ተብለው በተሰጡ ጉዳዮችን በተመለከተ ክልሎች (Lander) የህግ ማውጣት የሚችሉት በጉዳዮች ላይ የፌዴራል መንግስት ቀድሞ ሕግ ካለወጣ ወይም እስኪያወጣ ብቻ ነው፡፡ ይህ በመሆኑ የጀርመን ህገመንግስት ሁለቱም የመንግስት እርከኖች ተመሳሳይ በሆኑ ጉዳይ ላይ በአንድ ጊዜ በጋራ ሕግ የማውጣት

ሥልጣንን ተግባራዊ እንዲሆን የሚፈቅድ አይደለም፡፡ ስለዚህ በጀርመን ሕገመንግስት የጋራ ሥልጣን ለየት ያለ ትርጉም ያለው መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

ሶስተኛው የታክስ ሥልጣን ክፍፍል ዘዴ shared power of taxation ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የታክስ ሥልጣን ሶስት ገፅታዎች አሉት፡፡ እነሱም ሕግ ማውጣት፣ መሰብሰብ እና ገቢውን መጠቀም ናቸው፡፡ እነዚህን የታክስ ሥልጣን ገፅታዎች በሁለቱ የመንግስት እርከኖች መካከል የሚከፋፍሉ ሐገሮች አሉ፡፡ ሕገመንግስቱ በመርህ ደረጃ አንድ የተወሰነ ታክስን በተመለከተ የታክስን የመጣል ሥልጣን ለፌዴራል መንግሥት ሰጥቶ ከታክሱ የሚሰበሰበውን ገቢ የተወሰነውን ወይም ሙሉ በሙሉ የክልሎች እንዲሆን ሊደነግግ ይችላል፡፡ በዚህ መሰረት አንዱ የመንግስት እርከን የታክስ ህግን ያወጣል ሌላው ደግሞ የተጣለውን ታክስ በመሰብሰብ ሕጉን ያስተዳድራል፤አሁንም ሌላው ከታክስ የሚገኘውን ገቢ ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ የሕንድ ህገመንግሥት የፌዴራል መንግሥት የቴንብር ቀረጦችንና በመድሓኒቶች ላይ ኤክሳይዝ ታክሶችን የመጣል ሥልጣን አለው፡፡ ከእነዚህ የሚገኘው ገቢ የመሰብሰብ ሥልጣን ደግሞ ለክልል መንግስታት የተሰጠ ነው፡፡ በተመሳሳይ የፌዴራል መንግሥት የሽያጭ ታክስን ሕግ ማውጣትና የታክሱን የመሰብሰብ ሥልጣን አለው፡፡ ነገር ግን ከእነዚህ ታክሶች የሚገኘውን የተጣራ ገቢ የክልሎች ነው፡፡ ይህ የተጣራ ገቢም ህግ አውጪው በሚያወጣው የክፍፍል ቀመር መሰረት በክልሎች መካከል እንዲከፋፈል ይደረጋል፡፡

በጀርመን ሕገ-መንግሥትም ውስጥም shared tax ተደንግጓል፡፡ በጀርመን ሕገመንግት መሰረት ከገቢ ታክስ፣ ኮሮፕሬሽን ታክስና ከተርን ኦቨር ታክስ የሚገኘው ገቢ የሁለቱም መንግስት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ሁለቱም መንግሥት እርከኖች ከገቢ ታክስና ኮሮፕሬሽን ታክስ እኩል ድርሻ ያላቸው ሲሆን ከተርን ኦቨር ታክስ የሚገኘው ገቢ የሚከፋፈልበትን ቀመርም ተደንግጓል፡፡

በአጠቃላይ የፌዴራል መርህ አላማ እያንዳንዱ የመንግሥት እርከን ተለይቶ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር ራሱን ችሎ እንዲያከናውን የወጪ ፍላጎቱን ለማሟላት የሚያስችለው የፋይናስ አቅም እንዲኖረው ማድረግ ነው፡፡ ሆኖም ግን በተግባር የክልሎች የገቢ ምንጭና የወጪ ፍላጎትን ማመጣጠን አዳጋች እንደሆነ በዘርፉ ጸሐፊዎች ብዙ የተባለበት ጉዳይ ነው፡፡ ፌዴሬሽኖች ይህን ችግር የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ለመፍታት ይሞክራሉ፡፡

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. የታክስ ህግ አላማ እና በኢፌድሪ ህግመንግስት የተደነገገው የመልማት መብት መካከል ያለው ግንኙነት እንዴት ይገለጻል?
2. በሞጁሉ ውስጥ ከተጠቀሱት የታክስ አላማዎች ውጪ ሌሎች ካሉ ተወያዩበት፡፡
3. ከታክስ አንጻር በኢፌድሪ መንግስት የተለያዩ የኢኮኖሚ መስኮችን እንዲሁም የውጪ ንግድን ለማበረታታት በሕግ አውጭው አካል የተወሰዱት ወይም እየተወሰዱ ያሉት እርምጃዎች ምንድናቸው? ለምሳሌ ከሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 7/1988 አንጻር፡፡
4. ሕግ አውጭው አካል የታክስ ሥልጣኑን ተግባራዊ በሚያደርግበት ጊዜ ምን አይነት ነገሮችን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት ብላችው ታስባላችሁ?
5. ለአንድ ፌዴራል ሥርዓት የገቢ ክፍፍል በአጠቃላይ እና የታክስ ገቢ በተለይ ያለው ሚና እና ትርጉም ምንድነው?

## 1.3. የታክስ ሥልጣን ክፍፍል በኢፌዴሪ ሕገመንግስት

የታክስ ሥልጣን ክፍፍል በኢፌዴሪ ሕገመንግሥት ዘርዘር ባለ መልኩ ተደንግጓል፡፡ ሕገመንግሥቱ የታክስ ሥልጣንን በሶስት መደቦች ከፋፍሏል፡፡ እነሱም፡-

1. የፌዴራል መንግስት የታክስ ብቸኛ ሥልጣን፣
2. የክልል መንግሥታት  ብቸኛ የታክስ ሥልጣን እና
3. የፌዴራልና የክልል መንግሥታት የጋራ የታክስ ስልጣን ናቸው፡፡

እነዚህንም የፌዴራልና የክልል መንግስታት ብቸኛ የታክስ ሥልጣን እና የፌዴራልና ክልል መንግስታት የጋራ ታክስ ሥልጣን በማለት ሁለት ቦታ ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡

### 1.3.1. የፌዴራልና የክልል መንግሥታት ብቸኛ የታክስ ሥልጣን

በኢፌድሪ ሕገመንግሥት የፌዴራል መንግሥት ለፌዴራሉ መንግሥት በተሰጡ የገቢ ምንጮች ክልል ግብርና ቀረጥ መጣልና መሰበሰብ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ (አንቀፅ 51(10)). በተመሳሳይ ሁኔታ የክልል መንግሥታትም በተሰጣቸው የገቢ ምንጮች ክልል ግብርና ቀረጥ መጣልና መሰብሰብ ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡ (አንቀፅ 52 (2)) ስለዚህ ሁለቱም የመንግሥት

እርከኖች በተሰጣቸው የታክስ ክልል ህግ ማውጣትና ታክስ የመስተዳደር ሥልጣን አሏቸው ማለት ነው፡፡ በተጨማሪም ከየራሳቸው የታክስ ምንጭ የሚያገኙትን ገቢ የመጠቀም መብት አሏቸው፡፡

የኢፌዴሪ ሕግ መንግሥት "**የፌዴራል መንግሥት ታክስና ግብር ሥልጣን**" እና "**የክልል መስተዳድሮች የታክስና የግብር ሥልጣን**" በሚል ርእስ ብቸኛ የታክስ ሥልጣን ዘርዝሯል፡፡ የታክስ ሥልጣን ክፍፍሉ በአጠቃላይ ግብር ከፋዮች ምደባ ወይም የገቢ ምንጭን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የእያንዳንዱ የመንግስት እርከን ብቸኛ የታክስ ሥልጣን መሰረት የታክስ መሰረት ሳይሆን የታክስ ምንጭ ነው፡፡ ይህ በመሆኑ በህገመንግስቱ የተደነገገው የታክስ ሥልጣን ክፍፍል ሥርዓት ሁለቱም የመንግስት እርከኖች በተመሳሳይ ገቢ ወይም ታራንዛክሽን ላይ በአንድ ጊዜ ታክስ እንዲጥሉ የሚፈቅድ አይደለም፡፡

በህገመንግሥቱ በሁለቱ የመንግሥት እርከኖች መካከል እንዲከፋፈሉ የተደረጉ የታክስ ገቢ ምንጮች፡-የወጪና የገቢ ዕቃዎች ታክስና ክፍያዎች፣የገቢ ታክስ፣የሽያጭና የኤክሳይዝ ታክስ፣ የንብረት ታክስ እና የአገልግሎት ክፍያዎች በማለት ከፋፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ (አንቀፅ 96 እና 97)

### የወጪና የገቢ ዕቃዎች ታክሶችና ክፍያዎች

በሁሉም ፌዴሬሽኖች ማለት ይቻላል የወጪና የገቢ ዕቃዎች ላይ የጉምሩክ ቀረጥ መጣል እና የመሰብሰብ የፌዴራል መንግሥት ብቸኛ ሥልጣን ነው፡፡ የኢፌድሪ ህገመንግስትም ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ በወጪና ገቢ እቃዎች ላይ የጉምሩክ ቀጥተኛ ታክስና ሌሎች ክፍዎች መጣልና መሰብሰብ የፌዴራል መንግሥት ብቸኛ ሥልጣን መሆኑ በሕገመንግስቱ ተመልክቷል፡፡ (አንቀጽ 96(1))

### የገቢ ታክስ

የገቢ ታክስን መጣልና መሰብሰብ ሥልጣን ለየትኛው የመንግሥት እርከን መስጠት አለበት ለሚለው ጥያቄ አንድ ወጥ የሆነ መልስ የለም፡፡ አንዳንዶቹ የግል ገቢ ታክስን (personal income taxes ) ለፌዴራል መንግሥት ሲሰጡ ሌሎች ደግሞ ለክልሎች ይሰጣሉ፡፡ ለምሳሌ፣-

በጀርመን ሁለቱንም የመንግሥት እርከኖች የገቢ ታክስን በጋራ የመጣልና የመሰብሰብ ሥልጣን አሏቸው፡፡ በአሜሪካ ደግሞ የገቢ ታክስን መጣል እና መሰብሰብ ሥልጣን የክልል መንግሥታት ነው፡፡

የኢፌድሪ ሕገመንግስት የገቢ ታክስን የመጣልና የመሰብሰብ ሥልጣን ለፌዴራል መንግስት ብቻ ወይም ለክልል መንግስታት ብቻ አልሰጠም፡፡ በሕገመንግስቱ የገቢ ታክስን የመጣልና የመሰብሰብ ሥልጣን በሁለቱ የመንግስት እርከኖች መካከል እንዲከፋፈል ነው ያደረገው፡፡ በዚሁ መሰረት የፌዴራል መንግሥት እና የክልል መንግሥታት በምን ዓይነት የታክስ ምንጮች ላይ የገቢ ታክስ መጣልና መሰብሰብ እንደሚችሉ ተለይቶ ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም ሁለቱም የመንግሥት እርከኖች ተለይተው በተሰጧቸው የገቢ ምንጮች ላይ የገቢ ታክስን የመጣልና የመሰብሰብ ሥልጣን አሏቸው ማለት ነው፡፡

የገቢ ታክስ የሚጣልባቸው የታክስ ምንጮች ውስጥ አንደኛው የግል የስራ ግብር (Personal income from employment) ነው፡፡  የግል የስራ ግብርን በተመለከተ ህገመንግሥቱ ታክስ ከፋዮችን በአምስት ከፍሏቸዋል፡፡ እነሱም የፌዴራል መንግስት ተቀጣሪዎች፣ የክልል መንግስታት ተቀጣሪዎች፣የመንግስት ልማት ድርጅት ተቀጣሪዎች፣ የአለም አቀፍ ድርጅቶች ተቀጣሪዎችና የግል ተቀጣሪዎች ናቸው፡፡ የፌዴራሉ መንግሥት ተቀጣሪዎች፣ የፌዴራል መንግሥት የሆኑ የልማት ድርጅቶች ተቀጣሪዎች እና የአለም አቀፍ ድርጅቶች ተቀጣሪዎች ገቢ ላይ የፌዴራል መንግስት የስራ ግብር የመጣልና የመሰብሰብ ብቸኛ ሥልጣን አለው፡፡ በተመሳሳይ ክልሎች የክልል መንግስታት የሆኑ የልማት ድርጅቶች ተቀጣሪዎችና በግል ተቀጣሪዎች ላይ የስራ ገቢ ታክስ የመጣልና የመሰብሰብ ብቸኛ ሥልጣን አሏቸው፡፡

ሁለተኛው የገቢ ታክስ የልማት ድርጅቶች የንግድ ትርፍ ግብር የሚመለከተ ነው፡፡  በፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት ስር በሆኑ የልማት ድርጅቶች ላይ የንግድ ትርፍ ግብር መጣልና መሰብሰብ የፌዴራል መንግሥት ብቸኛ ሥልጣን ነው፡፡ የክልል መንግሥታት ባለቤትነት ስር በሆኑ የልማት  ድርጅቶች ላይ የንግድ ትርፍ ግብር መጣልና መሰብሰብ ደግሞ የክልል መንግሥታት ብቸኛ ሥልጣን ነው፡፡የዚህ ታክስ ሥልጣን ክፍፍልም ባለቤትነት መሰረት ያደረገ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ሶስተኛው በየክልሉ የሚገኙ ግለሰብ ነጋዴዎችን የሚመለከት ነው፡፡ በየክልሉ የሚገኙ ግለሰብ ነጋዴዎችን በተመለከተ የክልል መንግሥታት የንግድ ትርፍ ግብር የመጣልና የመሰብሰብ ሥልጣን አሏቸው፡፡ (አንቀጽ 97(4))

አራተኛው የአየር፣የባቡር፣የባህር ትራንስፖርት ገቢዎችን የሚመለከት ሲሆን በእነዚህ ስራዎች በሚገኘው ገቢዎች ላይ የፌዴራል መንግስት የገቢ ታክስ መጣልና የመሰብሰብ ብቸኛ ሥልጣን አለው፡፡ በሌላ በኩል የክልል መንግሥታት ክልል ውስጥ በውሃ ላይ ከሚደረግ ትራንስፖርት በሚገኘው ገቢ ላይ የታክስ ስልጣን አሏቸው፡፡

አምስተኛው የብሔራዊ ሎተሪ እና ሌሎች የእድል ሙከራ ገቢዎች ላይ የሚጣልና የሚሰበሰብ የገቢ ታክስ ነው፡፡ ይህ የፌዴራል መንግስት ብቸኛ ሥልጣን ነው፡፡

ስድስተኛው ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች በማከራየት በሚገኘው ገቢ ላይ የሚጣል የገቢ ታክስ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ የፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት ሥራ በሚገኙ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች ገቢ ላይ የፌዴራል መንግስት ታክስ የመጣልና የመሰበሰብ ብቸኛ ሥልጣን ያለው ሲሆን የክልል መንግስታት ደግሞ በግል ባለቤትነት ሥር ባሉ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች በሚገኝ ገቢ ላይ የገቢ ታክስ የመጣልና የመሰብሰብ ብቸኛ ሥልጣን አሏቸው፡፡ የዚህ ታክስ ሥልጣን ክፍፍልም ባለቤትነትን መሰረት ያደረገ መሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡

ሰባተኛው የእርሻ ሥራ ገቢ ታክስ ነው፡፡ የእርሻ ሥራ ገቢ ታክስን በተመለከተ የክልል መንግስታት በግል በሚያርሱ እና በህብረት ሥራ ማህበራት በተደራጁ ገበሬዎች ላይ የእርሻ ሥራ ገቢ ታክስ የመጣልና የመሰብሰብ ብቸኛ ሥልጣን አሏቸው፡፡

ስምንተኛው ከአነስተኛ ማዕድን ሥራዎች የሚገኝ ገቢን የሚመለከት ነው፡፡ በሕገመንግስቱ ከአነስተኛ ማዕድን ሥራዎች በሚገኘውን ገቢ ላይ የገቢ ታክስ የመሰበሰብ ሥልጣን የክልሎች ብቸኛ ሥልጣን ነው፡፡ (አንቀጽ 97 (8))

**የሽያጭ እና ኤክሳይዝ ታክሶች**

የሽያጭ እና ኤክሳይዝ ታክሶች በፌዴራልና በክልል መንግሥታት መካከል የተከፋፈለ ነው፡፡ በፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት ሥር በሆኑ የልማት ድርጅቶች ሽያጭ ምርቶች ወይም አገልግሎት በተመለከተ የፌዴራል መንግስት የሽያጭ ታክስ እና ኤክሳይዝ ታክስ የመጣል እና የመሰብሰብ ብቸኛ ሥልጣን ተሰጥቷል፡፡ (አንቀፅ 96(3)) ክልሎች ደግሞ በእነሱ ባለቤትነት ሥር ባሉ የልማት ድርጅቶች ላይ ተመሳሳይ ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡ ((አንቀፅ 97(7)). በተጨማሪም የክልል መንግስታት በክልላቸው ውስጥ በሚገኙ ግለሰብ ነጋዴዎችን ላይ የሽያጭ እና ኤክሳይዝ ታክስ የመጣልና የመሰበሰብ ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡

**የንብረት ታክሶች**

ለታክስ አላማ ንብረቶች በተለያ መደቦች ሊመደቡ ይችላሉ፡፡ በንብረት ላይ የሚጣል ታክስ የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በመሬት እና በሕንፃ በአመታዊ የመሬት ዋጋ ታክስ ወይም መሬት ሲሸጥ የሚከፈል የመሬት ዝውውር ታክስ ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ የተፈጥሮ ሐብትን ፍለጋ በተመለከተ የሚጣሉ ልዩ ክፍያዎች ወይም ታክሶች ብዙን ጊዜ እንደ ንብረት ታክስ ይቆጠራሉ፡፡ ለመኪናዎች ምዝገባ የሚከፈለው ክፍያ እንደ ንብረት ታክስ ሊቆጠር ይችላል፡፡ በአንዳንድ ሐገሮች በሟች ንብረት ዋጋ ላይ የሚጣል የውርስ ታክስ (inheritance tax) ከንብረት ታክስ ይመደባል፡፡

በሐገራችን ከቤቶች፣ ከመሬት፣ ከደን እና ከማዕድን ሥራዎች ጋር በተያያዘ የሚጣሉና የሚሰበሰቡ ታክሶች እንደ ንብረት ታክስ የሚቆጠሩ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ የክልል መንግስታት በእነሱ ባለቤትነት ሥር ባሉ ቤቶች፣ የመሬት መጠቀሚያ፣ ከደን የሚገኝ ሮያሊቲ እና በዝቅተኛ የማዕድን ሥራዎች ላይ የሮያሊቲ ክፍያዎችን መወሰንና መሰብሰብ ሥልጣን አሏቸው፡፡

**የአገልግሎት እና ሌሎች ክፍያዎች**

የኢፌድሪ ሕገመንግስት የፌዴራል እና የክልል መንግስት የታክስ ሥልጣን በሚደነግጉ አንቀጾች ስር የአገልግሎት ክፍያዎች እና የቴንብር ቀረጥ የመወሰንና የመሰብሰብ ሥልጣን የማን እንደሆነ በግልፅ ደንግጓል፡፡

የአገልግሎት ክፍያዎች እና የቴንብር ቀረጥ አገልግሎቱ በሚሰጥበት ቦታ መሰብሰብ አለባቸው፡፡ ይሔም ከአመቺነት አንፃር ነው፡፡ ይህም ማለት አገልግሎቱን የሰጠው የፌዴራል መስሪያ ቤት ከሆነ የፌዴራል መንግስት ክፍያውን ይወስናል፣ ይሰበስባል፡፡ በተመሳሳይ አገልግሎቱን የሰጠው የክልል መሥሪያ ቤት ከሆነ የክልል መንግስት ክፍያውን ይወስናል ይሰበስባል ማለት ነው፡፡

በዚሁ መሰረት በሕገመንግስቱ የፌዴራል (አንቀጽ 96(7)) እና የክልል መንግስታት (አንቀጽ 97(9)) እያንዳንዳቸው ከሚሰጧቸው ፈቃዶችና አገልግሎቶች የሚመነጩ ክፍያዎችን የመወሰንና የመሰበሰብ ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡ እንዲሁም የፌዴራል የቴምብር ሽያጭ መጣል እና የመሰብሰብ ስልጣን ለፌዴራል መንግስት የተሰጠ ነው፡፡

1.3.2. **የጋራ የታክስ ሥልጣን** (Concurrent power of taxation)

የኢፌዴሪ ሕገመንግስት የፌዴራል መንግስትና የክልል መንግስት እያንዳንዳቸው ሊኖራቸው የሚችለውን ሥልጣን ብቻ ሳይሆን ሁለቱ በጋራ ሊኖራቸው የሚችለውንም ሥልጣን በዝርዝር አስቀምጧል፡፡ በኢፌድሪ ሕገመንግስት የተደነገገው የጋራ ሥልጣን ውስጥ አንድ የታክስ ሥልጣን ነው፡፡ የጋራ የታክስ ሥልጣን የሚመለከታቸው ታክሶችና የጋራ የታክስ ሥልጣን ያለው ችግር ቀጥለን እንመለከታልን፡፡

**ሀ. የጋራ የታክስ ሥልጣን የሚመለከታቸው ታክሶች**

ከላይ እንደተመለከተው በኢፌድሪ ሕገመንግስት የተደነገገው ሌላው የታክስ መደብ የጋራ ታክስ ሥልጣን ነው፡፡ የጋራ ታክስ ሥልጣን መሰረታዊ ይዘት እና የጋራ ታክስ ሥልጣን የሚመለከታቸው ታክሶች በሕገመንግስቱ አንቀጽ 98 ሥር ተመልክቷዋል፡፡ ይህ አንቀጽ እንደሚከተለው ይነበባል፡-

1. *የፌዴራል መንግስትና ክልሎች በጋራ በሚያቋቁሟቸው የልማት ድርጅት ላይ የንግድ ትርፍ ግብር፣የስራ ግብር፣ የሽያጭና የኤክሳይዝ ታክስ በጋራ ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡*
2. *በድርጅቶች የንግድ ትርፍ ላይ እና በባለ አክስዮኖች የትርፍ ድርሻ ላይ ግብርና የሽያጭ ታክስ በጋራ ይጥላሉ፣ይሰበስባሉ፡፡*

*3. በከፍተኛ የማዕድን ሥራዎች በማናቸውም ፔትሮሊየምና የጋዝ ሥራዎች ላይ የገቢ ግብርና የሮያሊቲ ክፍያዎች በጋራ ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡*

ከዚህ ድንጋጌ መረዳት እንደሚቻለው የጋራ የታክስ ሥልጣን ከሚመለከታቸው ታክሶች ውስጥ አንዱ በፌዴራል መንግስትና ክልሎች በጋራ የሚቋቋሙ የልማት ድርጅት ላይ የሚጣሉ ታክሶች ሲሆኑ ታክሶቹም፡- የንግድ ትርፍ ግብር፣ የሥራ ግብር፣ የሽያጭና ኤክሳይዝ ታክስ ናቸው፡፡ የልማት ድርጅቶቹም የፌዴራል ሥርዓቱ ከተመሰረተ በኃላ የፌዴራል መንግስት እና ክልሎች በጋራ የሚያቋቁሟቸው እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ከ1983 ጀምሮ የመንግስት የኢኮኖሚ ፖሊሲ አቅጣጫ በነፃ ገበያ መርህ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ የፌዴራል መንግስት ከክልሎች ጋር አዲስ የጋራ ልማት ድርጅቶችን ከማቋቋም ይልቅ ነባር የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል እያዛወረ ይገኛል፡፡ የፌዴራል ሥርዓቱ ከተመሰረተ በኂላ የፌዴራል መንግስት እና የክልሎች በጋራ ያቋቋሟቸው የልማት ድርጅቶች የሉም፡፡ ስለዚህ በተግባር በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 98(1) መሰረት በፌዴራል መንግስት እና ክልሎች በጋራ የሚጣል እና የሚሰበሰብ ታክስ አለ ለማለት አይቻልም፡፡

የጋራ ታክስ ሥልጣን የሚመለከታቸው ሁለተኛው የታክስ አይነቶች በድርጅቶች እና በባለአክስዮኖች የትርፍ ድርሻ ላይ የሚጣሉና የሚሰበሰቡ ሲሆኑ የታክሶቹም ንግድ ትርፍ ግብርና የሽያጭ ታክስ ናቸው፡፡የንግድ ትርፍ እና የሽያጭ ታክስ የሚመለከታቸው ድርጅቶችም የአክስዮን ማህበር (Share Company) እና ሐላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር(Private Limited Company) መሆናቸው በህገመንግስት ጉባኤ ላይ የተደረገው ውይይት መረዳት ይቻላል፡፡ ስለዚህ የጋራ የታክስ ሥልጣን በግለሰብ ነጋዴዎች (sole proprietorship) እና የሽርክና ማህበርን (partnership) የሚመለከት አይደለም፡፡

ሶስተኛው የጋራ የታክስ ሥልጣን የተፈጥሮ ሀብትን የሚመለከት ነው፡፡ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 98 (3) መሰረት ከፍተኛ የማዕድን ሥራዎች እና ማናቸውም ፔትሮሊየምና የጋዝ ሥራዎች ላይ የገቢ ግብር እና ሮያሊቲ ክፍያዎችን መጣልና መሰብሰብ የፌዴራል እና የክልሎች የጋራ ሥልጣን ነው፡፡

ብዙ ፌዴሬሽኖች በተፈጥሮ ሀብት ላይ ታክስ የመጣልና የመሰብሰብ ሥልጣን ለፌዴራል መንግስት ይሰጣሉ፡፡ የኢፌድሪ ሕገመንግስት በተፈጥሮ ሀብት ላይ ታክስ የመጣልና የመሰብሰብ የፌዴራል መንግስት ብቸኛ ሥልጣን አድርጎ አልሰጠም፡፡ ከጥቂት በስተቀሮች በስተቀር ይህ የታክስ ሥልጣን የጋራ ነው፡፡ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 98(3) በግልጽ እንደተመለከተው በማናቸውም ፔትሮሊየምና የጋዝ ሥራዎች ላይ የገቢ ግብር እና የሮያሊቲ ክፍያዎች መጣልና መሰብሰብ የፌዴራል መንግስቱ እና የክልሎች የጋራ ሥልጣን ነው፡፡

የማዕድን ስራዎችን በተመለከተ ግን የታክስ ሥልጣኑ በሁለት ቦታ የተከፈለ ነው፡፡ አንደኛው የክልሎች ብቸኛ የታክስ ሥልጣን ሲሆን ሁለተኛው የጋራ የታክስ ሥልጣን ነው፡፡ ክፍፍሉም የተመሰረተው በማዕድን ሥራዎቹ መጠን ላይ መሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚሁ መሰረት ሕገመንግስቱ የማዕድን ሥራዎችን ከፍተኛና ዝቅተኛ ብሎ ከፋፍሏል፡፡ ቀደም ሲል እንዳየነው በዝቅተኛ የማዕድን ሥራዎች ላይ የሮያሊቲ ክፍያዎችን መወሰንና መሰብሰብ የክልሎች ብቸኛ ሥልጣን ነው፡፡ የፌደራል እና የክልሎች የጋራ የታክስ ሥልጣን የሚመለከተው ከፍተኛ ማዕድን ሥራዎች ላይ የሚጣሉና የሚሰበሰቡ የገቢ ግብር እና የሮያሊቲ ክፍያዎችን ብቻ ነው፡፡ ከፍተኛው እና ዝቅተኛው የማዕድን ሥራዎች ምን እንደሆኑ በአዋጁ ቁጥር 53/1993 እና ደንብ ቁጥር182/1994 በዝርዝር ተመልክቷል፡፡

በአጠቃላይ የተፈጥሮ ሀብት ላይ የሚጣሉና የሚሰበሰቡ ታክሶችን በተመለከተ የታክስ ሥልጣኑ ክፍፍል የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የሕዝብ ብቻ ነው የሚለውን የሕገመንግስቱን አንቀጽ 40(3) መሰረት ያደረገ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ስለዚህ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 98(1)፣(2) እና (3) የተጠቀሱትን ታክሶች የመጣልና የመሰብሰብ ሥልጣን የጋራ በመሆኑ እነዚህን ታክሶች የፌዴራል መንግስት ብቻውን ወይም የክልል መንግስታት ብቻቸውን መጣልና መሰብሰብ አይችሉም፡፡

ሌላው መታየት ያለበት ነጥብ የጋራ ታክስ ሥልጣን ገጽታዎች ናቸው፡፡ የጋራ የታክስ ስልጣን ከሚደነግገው የህገመንግስቱ አንቀጽ መረዳት እንደሚቻለው የጋራ ታክስ ሥልጣን ሁለት ገጽታዎች አሉት፡፡ እነሱም ታክሶችን መጣል እና መሰብሰብ ናቸው፡፡ ማለትም የጋራ ታክስ ሥልጣን ገጽታ የሚጣለው እና የሚሰበስበውን የታክስ ገቢ መጠቀምን(the power to

apportion the proceeds) የሚያጠቃልል አይደለም። በመሆኑም የፌዴራል መንግስትም ሆነ የክልል መንግስታት በጋራ ታክስ ሥልጣን መሰረት ከሚጣሉት እና ከሚሰበሰቡት ከታክሶች የሚገኘውን ገቢ የመወሰን ሥልጣን የላቸውም።

በጋራ ታክስ ሥልጣን መሰረት ከሚጣሉት እና ከሚሰበሰቡት ታክሶች በሚገኘው ገቢ ላይ የመወሰን ሥልጣን ያለው የፌዴሬሽን ምክር ቤት ነው። ፌዴሬሽን ምክር ቤት የፌዴራል መንግስትና የክልሎች የጋራ የተባሉ ገቢዎች በሁለቱ የመንግስት እርከኖች መካካል የሚከፋፈልበትን ሁኔታ የመወሰን ሥልጣን በሕገመንግስቱ ተሰጥቶታል። አንቀጽ 62(7)

በፌዴራል ሥርዓት የታክስ ገቢን በሁለቱ የመንግስት እርከኖች መካካል እንዲከፋፈል የማድረጉ ሥርዓት (tax sharing) ይባላል። የታክስ ክፍፍሉ ሥርዓት እንደ ሐገሩ ይለያያል። ለምሳሌ በሕንድ የፌዴራል መንግስቱ ታክሶችን ይጥላል፣ ይሰበስባል። ገቢው ግን ከክልል መንግስታት ጋር የሚከፋፈል ነው።

በኢፌድሪ ህገመንግስት የታክስ ክፍፍል ሥርዓቱ ከሕንድ የተለየ ነው። የታክስ ክፍፍሉ ሥርዓት የሚመለከታቸው የታክስ ገቢዎች በአንዱ የመንግስት እርከን ብቻ የሚጣሉና የሚሰበሰቡ አይደሉም። በመሆኑም ከኢፌድሪ ሕገመንግስት አንጻር የታክስ ገቢ ክፍፍል ማለት የጋራ ከተባሉ ታክሶች የሚያገኘውን ገቢ መከፋፈል ብቻ የሚመለከት ሳይሆን የጋራ የተባሉትን ታክሶችን በጋራ መጣልና መሰብሰብን የሚያጠቃልል ነው።

### ለ. ከጋራ ታክስ ሥልጣን ጋር በተያያዘ የሚነሱ ችግሮች

የህገመንግስቱ አንቀጽ 98 ሁለት መሰረታዊ ጉዳዮችን ተፈፃሚ የሚያደርግ ነው። እነዚህም የታክስ አጣጣል እና አሰባሰብ ናቸው። ታክስ የመጣል ሥልጣንም በተወሰነ ገቢ ላይ ሊሰበሰብ የሚገባውን የታክስ መጠን መወሰን እና ታክስ ከፋዩ ላይ ግዴታን መጣልና የሚያመለክት መሆኑን ቀደም ሲል ተመልክተናል።

የጋራ የታክስ ሥልጣንን የሚደነገገው የህገመንግስቱ ድንጋጌ ሁለት መሰረታዊ ችግሮች አሉበት ለማለት ይቻላል። አንደኛው ከመርህ አንፃር የሚታየው ነው። የፌዴራሉ መንግስት

ከእያንዳንዱ ክልል ጋር በየጊዜው በሚያደርገው ስምምነት የሚመሰረቱ ኩባኒያዎች በባህርያቸው ሥርጭታቸው በአንዱ ክልል የሚወሰን አይደለም፡፡ በመሆኑም እያንደንዱ ኩባኒያ ከየክልሉ ጋር በሚያደርገው ስምምነት ቢመሰረት እንቅስቃሴያቸው በአንድ ክልል የተወሰነ ስለማይሆን በታክስ አያያዝ (tax treatment) ረገድ በእኩልነት መታየት ስላለባቸው አንድ አገራዊ ታክስ መጣኔ ሊገዛቸው ይገባል፡፡

በሌላ በኩል ኩባኒያዎች፣በነዳጅ፣በጋዝና በማዕድን ስራ ላይ የተሰማሩትን ጨምሮ ከእያንዳንዱ ክልል ጋር በጋራ በሚወሰን መጣኔ ታክስ ይክፈሉ ቢባል የካፒታል ሥረጭት ችግር ከማስተከሉም በላይ የዚህ ዓይነቱ ኩባኒያዎች አገራዊ ባህርይ ያላቸው በመሆኑ በተወዳዳሪነታቸው ላይ ተፅዕኖ የሚያሳርፍ ይሆናል፡፡

በመሆኑም በኩባኒያዎች ገቢ ላይ የተለያዩ የታክስ መጣኔ (Tax rate) መወሰን ለኢኪኖሚ ምክንያት ትክክል አይሆንም፡፡ በአንድ አቋም ላይ ያሉ ታክስ ከፋዮች በአንድ አይነት መጣኔ ታክስ መክፈላቸው የታክስን ገለልተኝነት ይጠብቃል፡፡ ይህ ደግሞ ትክክለኛ የኢኮኖሚ አመራር ያሰርፃል፡፡ የጋራ ታክስ ሥልጣን የሚደነግገው የህገመንግስቱ አንቀጽ ከእነዚህ መርሆች አንጻር ሲፈተሽ ችግር ያለበት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ሁለተኛው ከተግባር አንፃር ያለበት ችግር ነው፡፡ የሕገመንግስቱ አንቀጽ 98 ከተግባር አንፃርም መሰረታዊ ችግር ያለበት ነው፡፡ ችግሩም **"በጋራ መጣልና እና መሰብሰብ"** ከሚለው ሐረግ የሚመነጭ ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተመለከተው ከታክስ ጋር በተያያዘ "መጣል" (Levy) የሚለው ቃል በተወሰነ ገቢ ላይ ሊሰበሰብ የሚገባውን የታክስ መጠን መወሰን እና ታክስ ከፋዩ ላይ ግዴታ መጣልን የሚመለከት ነው፡፡ የታክስ መጣኔ የሚወሰነው በአዋጅ ብቻ ነው፡፡ አዋጁ ደግሞ የሚወጣው በሕግ አውጪው አካል ማለትም እንደአግባብነቱ በፌዴራል መንግስት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና በክልል ምክር ቤቶች ስብሰባ ነው፡፡

በሕግመንግስቱ አንቀጽ 98 ሥር በተደነገገው መሰረት በጋራ ታክስ በሚጣልባቸው ገቢዎች ላይ የታክሱ መጣኔ ሊወሰን የሚችለው ከላይ እንደ ተጠቀሰው በአዋጅ ስለሚሆን የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና በክልል ምክር ቤቶች ስብሰባ ነው፡፡ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 98 ስር በተደነገገው

መሰረት በጋራ ታክስ በሚጣልባቸው ገቢዎች ላይ የታክሱ መጣኔ ሊወሰን የሚችለው በአዋጅ ስለሚሆን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት እና የእያንዳንዱ ክልል ምክር ቤት በየጊዜው የጋራ ስብሰባ በማድረግ ውሳኔ ማስተላለፍ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ ደግሞ በተግባራዊ ችግሮች ምክንያት ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል አይደለም፡፡

የታክስ አሰባሰብ መታየት ያለበት ከመብት ወይም ከሥልጣን አንፃር ሳይሆን ከተግባር አመቺነት ነው፡፡ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 98 መሰረት ታክሱ በጋራ ለመሰብሰብ አመቺ አይደለም፡፡ ይህ አመቺ ሊሆን የሚችለው ታክሱን የመሰብሰብ ሥራ ለአንድ የመንግስት እርከን ከተሰጠ ብቻ ነው፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የተነሳ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 98 ሥር የተደነገገው ተግባራዊ ሆኖ አያውቅም፡፡ ድንጋጌውን ተግባራዊ እንዲሆን ለማድረግ ያለው ብቸኛው መፍትሔ ማሻሻል መሆኑ ታምኖበት በ1989 ዓ.ም ማሻሻል ሥራ ተጀምሮ የማሻሻያ ረቂቁም ቀርቦ የህዝብ ተወካዮች ምር ቤት የማሻሻያ ረቂቁን መጋቢት 30/1989 ዓ.ም በሰላሳ ስምንተኛው መደበኛ ስብሰባው በሙሉ ድምጽ፣ በፌዴሬሽን ምክር ቤት ደግሞ በሚያዝያ 1/1989 ዓ.ም በሁለተኛው መደበኛ ጉባኤ ላይ በአንድ ድምጽ ፀድቋል፡፡ በተጨማሪም ረቂቁ በሁለቱ ምክር ቤቶች የጋራ ስብሰባ ሚያዝያ 2/1989 ፀድቋል፡፡

ረቂቁ የማሻሻያው ሃሳቡም በሕገመንግስቱ አንቀጽ 98 የተጠቀሱትን ታክሶች የመጣልና የመሰብሰብ ሥልጣን የፌዴራል መንግስት እንዲሆን፤ ነገር ግን ታክሱን የመሰብሰብ በተመለከተ የፌዴራል መንግስት ሥልጣኑን ለክልሎች በውክልና መስጠት እንደሚቻል የሚገልፅ ነው፡፡

ነገር ግን ይህ የማሻሻያ ረቂቅ አዋጅ ለውይይትና ውሳኔ ለመላው ሕዝብና ለክልል ምክር ቤቶች ቀርቦ መጽደቅ አለመጽደቁ የሚታወቅ ነገር የለም፡፡ ማሻሻያው ግን በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ አለመውጣቱን በእርግጠኝነት ለመናገር ይቻላል፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ በአሁኑ ጊዜ በተግባር በህገመንግስቱ አንቀጽ 98(2) እና (3) ስር የተጠቀሱት ታክሶች የሚጣሉትና የሚሰበሰቡት በፌዴራል መንግስት ነው፡፡

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. በኢፌድሪ ህገመንግስት ተለይተው በፌዴራል መንግስት ወይም በክልል መንግስታት እንዲጣሉ እና እንዲሰበሰቡ የተደረጉ ታክሶች በተመለከተ የታክስ ሥልጣን ክፍፍሉ መሰረት ምንድነው? እያንዳንዱን የታክስ አይነት በማንሳት የክፍፍሉን መሰረት ለዩ፡፡
2. ከአጠቃላይ ታክስ ባህሪ እና በሕገመንግስቱ ከተደነገገው የታክስ ሥልጣን ክፍፍል አንጻር በታክስና በአገልግሎት ክፍያዎች መካከል ያለው ልዩነትና ተመሳሳይነት ምንድነው? የህገ መንግስቱ አንቀጽ 96 እና 97 ርእስ እና ይዘት ምን አይነት ችግር ይታይባቸዋል?
3. ብዙ ፀሐፊዎች የታክስ አይነቶችን ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶች በማለት ይከፋፍላሉ፡፡ በሁለቱ መካካል ያለው መሰረታዊ ልዩነት ምንድነው? በሕገመንግስቱ በፌዴራል እና በክልል መንግስታት መካካል እንዲከፋፈሉ ከተደረጉት የታክስ አይነቶች ውስጥ የትኞቹ ቀጥተኛ፤ የትኞቹ ደግሞ ቀጥተኛ ያልሆኑ ናቸው?
4. በኢፌድሪ ሕገመንግስት የተደነገገው የታክስ ሥልጣን ክፍፍል ሥርዓት ከህግ ማውጣት የስልጣን ክፍፍል ሥርዓት የተለየ ነው? የተለየ ነው የሚባል ከሆነ እንዴት? የህግ ማውጣትን ሥልጣን መሰረት በማድረግ በፌዴራል ወይም በክልል መንግስታት እንዲጣሉ እና እንዲሰበሰቡ የተደረጉ የታክስ አይነቶች አሉ?
5. በኢፌድሪ ህገመንግስት የተደነገገው የታክስ ሥልጣን ክፍፍል ዘዴ ከህገመንግስቱ አንቀጽ 94 ጋር ያለው ግንኙነት እንዴት ይገለፃል?
6. የፌዴራል መንግስት በሕገመንግስቱ የተሰጠውን የታክስ ሥልጣን፣ ለምሳሌ ታክስ የመጣል ሥልጣኑን ለክልሎች በውክልና ሊሰጥ ይችላል? ያለው ልምድ ምን ይመስላል?
7. በኢፌድሪ ህገመንግስት የተደነገገው የጋራ ታክስ ሥልጣን ከሌሎች ፌዴሬሽኖች አንፃር እንዴት ይታያል?
8. የህገመንግስቱ አንቀጽ 98 ሕገመንግስቱ በሚያዘው መሰረት ተሻሽሏል ብላችሁ ታስባላችሁ? ለምን? በአሁኑ ጊዜ የፌዴራል መንግስት የጋራ የተባሉ ታክሶችን

መጣሉና መሰብሰቡ ሕገመንግስታዊ ነው? አይደለም የሚባል ከሆነ መፍትሔው ምንድነው?

9. በአጠቃላይ በኢፌድሪ ህገመንግስት የተደነገገው የታክስ ሥልጣን ክፍፍል ከሌሎች ፌዴሬሽኖች አንጻር ሲታይ ምን ጠንካራና ደካማ ጎን አለው ትላላችሁ? ለምሳሌ ከአሜሪካ አንጻር

10. ከፌዴራሊዝም ፅንሰ ሐሳብ አኳያ የታክስ ገቢን መከፋፈል (tax sharing) ምን ፋይዳ አለው?

## 1.4. ተለይተው ያልተሰጡ የታክስ ሥልጣኖች (Residual taxes)

የኢፌዴሪ ህገመንግስት የታክስ ሥልጣንን ክፍፍልን በተመለከተ የገቢ ምንጮችን የመለያየት (separation of revenue sources) ዘዴን የተከተለ ነው፡፡ የታክስ አይነቶችና መሰረቶች ላይ በመመስረት ሕገመንግስቱ ለፌዴራልና ለክልል መንግስታት የታክስ ሥልጣን ብቸኛና የጋራ በማለት ለያይቶ ደንግጓል፡፡ ቀጥሎ መታየት ያለበት ነጥብ አዲስ ታክስ የመጣልና የመሰብሰብ ሥልጣን የማነው የሚለው ነው፡፡

ብዙ ፌዴሬሽኖች አዲስ ታክስ የመጣልና የመሰብሰብ ሥልጣን ለፌዴራሉ መንግስት ይሰጣሉ፡፡ ለምሳሌ ሕንድና ብራዚልን መጥስ ይቻላል፡፡ የሕንድ ሕገ መንግስት በጋራ ታክስ ሥልጣን ዝርዝር ወይም በክልል መንግስታት የታክስ ሥልጣን ዝርዝር ውስጥ ያልተጠቀሱ ታክሶች የመጣልና የመሰብሰብ ሥልጣን የፌዴራል መንግስቱ ነው፡፡

በሌላ በኩል አዲስ ታክስን የመጣልና ሥልጣን ለክልል መንግስታት የሚሰጡ ሐገሮችም አሉ፡፡ ለምሳሌ አሜሪካን መጥቀስ ይቻላል፡፡ በአሜሪካ በሕገመንግስቱ ለፌዴራል መንግስት በግልፅ ያልተሰጡ ሥልጣኖች የክልል መንግስታት በመሆኑ ክልል መንግስታት በህገመንግስቱ ተለይተው ያልተሰጡ ታክሶች ላይ ሥልጣን አሏቸው፡፡

ተለይተው ያልተሰጡ የታክስ ሥልጣኖችን በተመለከተ የኢፌድሪ ሕገ መንግስት ከላይ ከተጠቀሱት ፌዴሬሽኖች ለየት ይላል፡፡ ሕገመንግስቱ እንደ ሌሎች ፌዴሬሽኖች አዲስ ታክስን የመጣል ሥልጣን የፌዴራል መንግስት ወይም የክልል መንግስት ነው በማለት ቁርጥ ያለ

መልስ ከመስጠት ይልቅ በሕገመንግስቱ ተለይተው የፌዴራል መንግስት ወይም የክልሎች ብቸኛ የታክስ ሥልጣን ወይም የጋራ ያልተባሉ ታክሶች ላይ እንዴት ውሳኔ እንደሚሰጥ ብቻ ይደነግጋል፡፡ ይህን አስመልክቶ አንቀፅ 99 እንደሚከተለው ይነበባል፡፡

> *"በዚህ ሕገመንግስት ተለይተው ያልተሰጡ ታክስና ግብር የመጣል ሥልጣኖችን በሚመለከት የፌዴሬሽን ምክር ቤትና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በጋራ ስብሰባ በሁለት ሶስተኛ ድምፅ ይወስናሉ፡፡"*

ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው በህገመንግስቱ ተለይተው ያልተሰጡ ታክሶችን ወይም አዲስ ታክሶችን የመጣልና የመሰብሰብ ሥልጣን በሁለቱ ምክር ቤት የጋራ ስብሰባ የሚወሰን ነው፡፡ ስለዚህ ሁለቱም የመንግስት እርከኖች በሕገመንግስቱ ውስጥ ተለይተው ከተሰጣቸው የታክስ አይነቶች ውጪ አዲስ ታክሶችን መጣልና መሰብሰብ አይችሉም፡፡ በሕገመንግስቱ ውስጥ ያልተጠቀሱ ማንኛውም የታክስ አይነት መጣልና መሰብሰብ በቅድሚያ የሁለቱን ምክር ቤት ውሳኔ የሚጠይቅ ነው፡፡

በዚሁ መሰረት ሁለቱም ምክር ቤቶች በጋራ በሚያደርጉት ስብሰባ አዲስ ታክሶችን የመጣልና የመሰብሰብ ሥልጣን የፌዴራሉ መንግስት ብቸኛ ሥልጣን ወይም የክልሎች ብቸኛ ሥልጣን ወይም የጋራ እንዲሆን ሊወስኑ ይችላሉ፡፡ ይህ ከሆነ ብቻ ነው የፌዴራል ወይም የክልል መንግሥታት የታክስ ሥልጣን ሊሰፋ የሚችለው፡፡ በተግባርም በሕገመንግስቱ ተለይተው ያልተሰጡ የታክስ ሥልጣኖችን በተመለከተ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የፌዴሬሽን ምክር ቤት በጋራ ባደረጉት ስብሰባ በተለያየ ጊዜ ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡ ለምሳሌ ተጨማሪ እሴት ታክስ እና ተርን ኦቨር ታክስን መጥቀስ ይቻላል፡፡

እነዚህ ታክሶች በህገመንግስቱ የፌዴራል መንግስት ወይም የክልል መንግስት ብቸኛ የታክስ ሥልጣን ወይም የጋራ የታክስ ሥልጣን ዝርዝር ውስጥ አልተጠቀሱም፡፡ ህገመንግስቱ ከፀደቀ በኋላ ግን ሁለቱ ም/ቤቶች በጋራ ባደረጉት ስብሰባ እነዚህ ታክሶችን የመጣል እና የመሰብሰብ ሥልጣን የፌዴራል መንግስት እንዲሆን በመወሰናቸው ምክንያት የፌዴራል መንግስት በአሁኑ ጊዜ ይህን የታክስ ሥልጣን ተግባራዊ እያደረገ ነው፡፡ የጋራ እንዲሆኑ የተወሰኑ የታክስ ሥልጣኖችም አሉ፡፡ ለምሳሌ የድርጅቶች ኤክሳይስ ታክስ፣ የፈጠራ መብትን በማከራየት የሚገኝ ገቢ (ድርጅት) መጥቀስ ይቻላል፡፡ በተጨማሪም ሁለቱ ምክር ቤቶች በጋራ

በሚያደርጉት ስብሰባ አዲስ ታክሶችን የመጣል ሥልጣን የማን መሆን አለበት ብቻ ሳይሆን በሚጣሉት ታክሶች ገቢ ክፍፍል ላይም ውሳኔ ይሰጣሉ፡፡ ለምሳሌ  ተጨማሪ እሴት ታክስ እና ተርን ኦቨር ታክስ በተመለከተ የገቢ ክፍፍሉ፡-

- ግለሰቦች ነጋዴዎች የሚመለከት ከሆነ ፌዴራል መንግስት 0% - ክልል መንግስት 100%
- ድርጅቶች (companies) ፌዴራል መንግስት 70%--ክልል 30%
- የፌዴራል መንግስት የልማት ድርጅት ፌዴራል መንግስት 100% - ክልል 0% እንዲሆን ተወስኗል፡፡

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. ከተጨማሪ እሴት ታክስ፤ ተርን ኦቨር ታክስ፤ የድርጅቶች ኤክሳይስ ታክስ፤ እና የፈጠራ መብትን በማከራየት የሚገኝ ገቢ (ድርጅት) በተጨማሪ በሕገ መንግስቱ ለፌዴራል መንግስት ወይም ለክልል መንግስት ብቸኛ የታክስ ሥልጣን ወይም የጋራ ተብለው ያልተጠቀሱ ታክሶች ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ አንቀጽ 99 መሰረት በማድረግ በክልል መንግስት ወይም በፌዴራል መንግስት የሚጣሉና የሚሰበሰቡ ሌሎች ታክሶችን ጥቀሱ፡፡
2. የሕገመንግስቱ አንቀጽ 99 ድንጋጌ መኖር ጥቅሙ ምንድነው?
3. ሁለቱ ምክር ቤቶች በህገመንግስቱ ውስጥ ያልተጠቀሱ የታክስ አይነቶች ላይ ውሳኔ ለመስጠት ምን አይነት ነገሮችን ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል ብላችሁ ታስባላችሁ?

## 1.5. የታክስ ሥልጣን ገደቦች

የታክስ ሥልጣንን በሁለቱ የመንግሥት እርከኖች መካከል መከፋፈል እያንዳንዱ የመንግሥት እርከን የታክስ ሥልጣን ተለይቶ በተሰጠው የታክስ ዓይነቶች ወይም የታክስ መሠረቶች ላይ ብቻ የተወሰነ እንዲሆን በማድረግ ገደብ የሚጥል ነው፡፡ ለምሣሌ ጉምሩክ ቀረጥን መጣልና መሰብሰብ የፌዴራል መንግሥት ብቸኛ ሥልጣን በመሆኑ ክልሎች የጉምሩክ ቀረጥ የመጣልና የመሰብሰብ ሥልጣን የላቸውም፡፡ በተመሳሳይ ለክልሎች የተሰጡ የታክሶችን በተመለከተ

የፌዴራል መንግሥት የታክስ ሥልጣን የተገደበ ነው፡፡ ስለዚህ በሕገ-መንግሥቱ የተደነገገው የታክስ ሥልጣን ክፍፍል ራሱ በታክስ ሥልጣን ላይ ገደብ የሚጥል ነው ለማለት ይቻላል፡፡

በዚህ ንዑስ ክፍል የምንመለከተው ሌሎች የታክስ ሥልጣን ገደቦችን ይሆናል፡፡ በፌዴራል ሥርዓት በአጠቃላይ ሶስት ዓይነት የታክስ ሥልጣን ገደቦች አሉ፡፡ እነሱም፡- አድሏዊ በሆኑ የፌዴራል ታክስ ሕጎች ላይ የተጣለ ገደብ (the prohibition of federal discrimination tax laws)፤ክልል ዘለል በሆኑ የክልል መንግሥት የታክስ ሕጎች ላይ የተጣለ ገደብ (The prohibition of the extra territoriality of state taxes) እና አንዱ መንግሥት በሌላው መንግስት ንብረት ላይ ታክስ አለመጣል (Intergovernmental Tax immunity) ናቸው፡፡

### 1.5.1. አድሏዊ በሆኑ የፌዴራል የታክስ ሕጎች ላይ የተጣለ ገደብ

ይህ ገደብ የፌዴራል መንግሥት ታክስ ሥልጣንን የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ መርህ መሰረት የፌዴራል መንግሥት በክልሎች መካከል ልዩነት የሚያደርጉ ወይም አንዱን ክልል መንግሥት ከሌሎች በተለየ መንገድ ተጠቃሚ የሚያደርግ የታክስ ሕግ ማውጣት የለበትም፡፡ ፌዴራል መንግሥት የሚያወጣው የታክስ ህግ ክልሎችን በእኩል ደረጃ ወይም በተመሳሳይ ሁኔታ የሚመለከት መሆን አለበት፡፡

ይህ ዓይነቱ ክልከላ በብዙ ፌዴሬሽኖች ሕገ-መንግሥት በግልፅ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ የአሜሪካ ሕገ-መንግሥት በፌዴራሉ መንግሥት የሚጣሉና የሚሰበሰቡት ቀረጦችና ኤክሳይዝ እና የገቢ ታክሶች ሁሉ በሐገሪቱ ሙሉ በሙሉ ተመሳሳይ ወይም ወጥ (uniform) እንዲሆኑ ይጠይቃል፡፡ እነዚህን ታክሶች በተመለከተ የፌዴራል መንግሥት በክልሎች መካከል ልዩነት የሚያደርግ የታክስ ህግ ሊያወጣ አይችልም፡፡ የአውስትራሊያ ሕገ-መንግሥትም የፌዴራል መንግሥት የታክስ ሥልጣኑን በክልሎች መካከል አድሏዊ ልዩነትን በሚፈጥር መልኩ ተግባራዊ ማድረግ እንደሌለበት ይደነግጋል፡፡

በፌዴራል መንግሥት የታክስ ሥልጣን ላይ የዚህ ዓይነቱን ገደብ ማስቀመጡ የፌዴራሉ መንግሥት የክልል መንግሥት እኩል አይደሉም በመካከላቸው ልዩነት አለ የሚለውን ምክንያት ለይስሙላ በመጠቀም የተለያዩ ክልል መንግሥት ሕዝቦች ለፌዴራል መንግሥት የተለያየ

የታክስ አያያዝ (tax treatment) እንዳይጋለጡ ለመከላከል ሊረዳ ይችላል፡፡ ይህም በሕገመንግሥቱ ሁሉም የክልል መንግሥታት እኩል ናቸው የሚለውን መርህ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በዚህ ገደብ መሠረት የፌዴራል መንግሥት አንድን ክልል ለመጥቀም በክልሎች መካከል የተለያየ የታክስ መጣኔ የሚጥሉ ወይም የታክስ መብትን የሚደነግጉ የታክስ ሕጎችን ማውጣት የለበትም፡፡

በሌላ በኩል አንዳንድ ፌዴሬሽኖች በክልል መንግሥታት መካከል ያለውን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልዩነቶች ትኩረት የሚሰጡ አሉ፡፡ ለዚህም በታክስ መጣኔ ላይ ልዩነት ሳያደርጉ እገዛ የሚያስፈልጋቸውን የክልል መንግሥታት የሚታገዙበትን መንገድ ያስቀምጣሉ፡፡

በኢትዮጵያ በክልሎች መካከል ያለው ልዩነት በግልፅ የሚታይ ነው፡፡ ለዚህም ሕገመንግሥቱ በልማት ወደኋላ ለቀሩ ክልሎች የፌዴራል መንግሥት ለእነዚህ ክልሎች በተለያየ መንገድ ድጋፍ ሊያደርግ ይችላል፡፡ አንዱ መንገድ የፌዴራል መንግሥት ከክልሎች የሚገኙ ገቢዎችን በተመለከተ በሚያወጣው የታክስ ህጎች የተለያዩ የታክስ እርምጃዎች እንዲካተቱ ማድረግ ነው፡፡ ለምሣሌ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ ቀጥር 7/1988 መሠረት በጋምቤላ፤ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፤ ሶማሌ እና አፋር ክልል አዲስ ድርጅት በማቋቋም ኢንቨስት የሚያደርግ ሰው ለአምስት ዓመት ከታክስ ነፃ እንዲሆን ተደንግጓል፡፡፡ ኢንቨስትመንቱ በቀሪዎቹ ክልሎች ከሆነ ግን ከታክስ ነፃ የሚኮሆነው ለሶስት ዓመት መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ይህ የታክስ ማበረታቻ አላማ በእድገት ኋላ ቀር ወደ ሆኑት ክልሎች ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ነው፡፡

### 1.5.2. ክልል ዘለል በሆኑ የክልል መንግስታት የታክስ ሕጎች ላይ የተጣለ ገደብ

ሁለተኛው ገደብ የክልል መንግስታትን የታክስ ሕጎች የሚመለከት ነው፡፡ በአንድ ክልል መንግስት የሚወጣው የታክስ ሕግ በሌላ ክልል መንግሥት ላይ ጫና የሚፈጥር መሆን የለበትም፡፡ ከመጀመሪያውኑ ይህን አይነት ባህሪ ያላቸው ታክሶች የመጣል ሥልጣን ለፌዴራል መንግስት መስጠት አለባቸው፡፡ ለምሳሌ የጉምሩክ ቀረጥን መጥቀስ ይቻላል፡፡

የዚህ ገደብ ዋናው አላማ በአንድ ክልል መንግስት የሚጣለው ታክስ ተፈፃሚነት ወሰን ታክሱን በጣለው መንግሥት ግዛት ክልል የተወሰነ እንዲሆን ለማደረግ ነው፡፡ ምክንያቱም በአንድ ክልል

መንግስት የሚጣለው ታክስ በሌላ ክልል መንግስት ውስጥ በሚከናወነው ኢኮኖሚያዊ እና የንግድ እንቅስቃሴ ላይ ጫና ሊፈጥር ስለሚችል ነው፡፡ በተጨማሪም የእቃዎች፣ አገልግሎቶችና የካፒታል ነፃ ፍሰት እንዲኖር ይህ ገደብ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ በሰፊው ሲተነተን ይህ ክልከላ አድሏዊ የክልል መንግሥታት የታክስ ሕጎች ላይ ገደብ የሚጥል ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ የክልል መንግስት የምርቶችን ምንጭ መሰረት ያደረገ አድሏዊ ልዩነት የሚያደርጉ የታክስ ሕጎችን ማውጣት የለበትም፡፡

በሕገመንግስቱ መሰረት የፌዴራል መንግስት በክልሎች መካካል የሚደረግን የንግድ ግንኙነት የመምራትና የመቆጣጠር ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡ (አንቀጽ 51(12)) በክልሎች መካካል የሚኖረውን የንግድ እንቅስቃሴ ላይ ችግር የሚፈጥሩ የክልል መንግስታት የታክስ ህጎች በዚህ ድንጋጌ መፍትሔ የሚያገኙ ይሆናሉ፡፡ በኢፌድሪ የክልል መንግስታት የታክስ ሥልጣን ሁሉም ማለት ይቻላል ተግባራዊ የሚሆኑት በክልል ግዛት የተገደቡ የታክስ መሰረቶች ላይ ብቻ በመሆኑ የዚህ ገደብ ተፈፃሚነት የጎላ ነው፡፡

### 1.5.3. አንዱ የመንግሥት እርከን በሌላው መንግስት ንብረት ላይ ታክስ አለመጣል

ሶስተኛው ገደብ አንድ የመንግስት እርከን በሌላኛው መንግስት ላይ ታክስ መጣል ሥልጣንን የሚመለከት ነው፡፡ የተለያዩ የመንግስት እርከኖች በሚኖሩበት ጊዜ አንድ የመንግስት እርከን በሌላኛው የመንግስት እርከን ታክስ መክፈል አለበት ወይስ የለበትም የሚለው ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም፡፡ በፌዴራል ሥርዓት ውስጥ ሁለቱም የመንግስት እርከኖች የራሳቸው ሥልጣንና ተግባር አሏቸው፡፡ የታክስ ሥልጣኑም ከዚሁ ጎን ለጎን የሚታይ በመሆኑ አንዱ መንግስት በሌላው መንግስት ሥልጣን ጣልቃ አይገባም፡፡ በተግባር ግን አንድ መንግስት በሌላው መንግስት ሥልጣን ጣልቃ እንዳይገባ ማድረግ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፡፡ የታክስ ሥልጣንን በተመለከተ አንዱ የመንግስት እርከን በሌላው መንግስት ሥልጣን ጣልቃ እንዳይገባ ለመከላከል the doctrine of intergovernmental tax immunity የሚለው መርህ ተቀባይነት እያገኘ መጥቷል፡፡

የዚህ ዶክትሪን ምንጭ አሜሪካ ስትሆን ዶክትሪኑንም ሕገመንግስቱ የተደነገገ ሳይሆን በህግ ክለሳ (Judicial Review) የዳበረ ነው፡፡ በዚህ ዶክትሪን መሰረት የፌዴራል መንግስት

ንብረት ከክልል መንግስት፣የክልል መንግስት ንብረት ደግሞ ከፌዴራል መንግስት ታክስ ነፃ ነው። ሆኖም ግን ይህ ዶክትሪን በንግድ ድርጅቶች ላይ የሚጣሉ ታክሶችን አይመለከትም።

የአውስትራሊያ ህገመንግስትም አንዱ የመንግስት በሌላው መንግስት ንብረት ላይ ታክስ እንዳይጥል ይከለክላል። ሆኖም ግን ይህን ድንጋጌ በሐገሪቱ ውስጥ ያሉ የክልል መንግስታት ንብረቶችና ከውጭ ወደ ሐገሩ ውስጥ የሚገቡ ንብረቶች በማለት ልዩነት በማድረግ በጠባቡ ተተርጉሞ ተግባራዊ እንዲሆን ተደርጓል። በዚህ መሰረት የጉምሩክ ቀረጥም በንብረት ላይ ሳይሆን ወደ ሐገር ውስጥ በማስገባቱ ሒደት ላይ የሚጣል ታክስ ተደርጎ ይወሰዳል። ስለዚህ በአውስትራሊያ የክልል መንግስታት ከውጪ በገዥ የሚያስገቧቸው ንብረቶች ላይ የፌዴራል መንግስት የጉምሩክ ቀረጥ ይጥላል።

የአንዱን መንግሥት ንብረት ከሌላው መንግሥት ታክስ ነፃ የሚያደርገው መርህ በሕንድ ሕገመንግስት ውስጥም ተካቷል። በሕንድ ሕገመንግስት የክልል መንግስት ንብረት እና ገቢ ከፌዴራል መንግስት ታክስ ነፃ ናቸው። ሆኖም ግን ይህ በክልል መንግስታት የሚካሔደውን ንግድ እና ከንግድ የሚገኘውን ገቢ ወይም ለንግድ የሚያገለግሉ ንብረቶችን አይመለከትም። በሌላ በኩል የፌዴራል መንግስቱ ለንግድ የሚገለገልባቸው ንብረቶች ሆኑ ሌሎች ንብረቶች ከክልል መንግስታት ታክስ ነፃ ናቸው።

በኢትዮጵያ ይህን ዶክትሪን በሕገመንግስቱ አንቀጽ 100 (3) ተካቷል። ይህም አንቀጽ እንደሚከተለው ይነበባል፡-

> *"ለትርፍ የቆመ ድርጅት ካለሆነ በስተቀር ክልሎች በፌዴራል መንግስት ንብረት ላይ፣ የፌዴራሉ መንግስትም በክልሎች ንብረት ላይ ግብር ወይም ቀረጥ የማስከፈል ሥልጣን አይኖራቸውም።"*

በዚሁ ድንጋጌ መሰረት ለትርፍ የተቋቋሙ የመንግስት ልማት ድርጅት ላይ ይህ መርህ ተፈፃሚነት የለውም። የመርሁን ተፈፃሚነት ወሰን ለመወሰን መታየት ያለበት ድርጅቱ ባለቤት ማነው የሚለው ሳይሆን የተቋቋመበት አላማ ምንድነው የሚለው ነው። በዚህ መሰረት በክልል መንግስታት የግዛት ክልል ውስጥ በንግድ ሥራ የተሰማሩ የፌዴራል መንግስት እንዱስትሪዎችና ሆቴሎች ከመሬት መጠቀሚያ ክፍያዎች ነፃ አይደሉም። ስለዚህ የፌዴራል

መንግሥት ንብረቶች የሚገኙበት የክልል መንግሥት የመሬት መጠቀሚያ ክፍያዎችን ይጥላል፤ይሰበስባል፡፡ በክልል የሚገኙ የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ መ/ቤቶች ግን ከመሬት መጠቀሚያ ክፍያዎች ነፃ ናቸው፡፡ ክልሎች በክልላቸው ውስጥ በሚገኙ የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ መ/ቤቶች ላይ የመሬት መጠቀሚያ ክፍያዎች እንዳይጥሉ ሕገመንግስቱ ገደብ ይጥልባቸዋል ማለት ነው፡፡

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. የፌዴራል መንግስት በክልል መንግስት ንብረቶች ላይ እንዲሁም የክልል መንግስት በፌዴራል መንግስት ንብረቶች ላይ ታክስ እንዳይጥሉ የሚከለክለው መርህ ዋና አላማ ምንድነው?
2. አንድ የክልል መንግስት የክልሉ ተወላጆች መዋለ ነዋያቸውን እንዲያፈሱ ለማበረታታት በክልል ተወላጆችና የክልሉ ተወላጆች ባልሆኑ ሰዎች መካካል የተለያየ የታክስ ማስከፈያ መጠን የሚደነግግ የታክስ ሕግ ሊያወጣ ይችላል? ለምን?
3. ክልሎች ወደ ክልላቸው ኢንቨስትመንት ለመሳብ የተለያዩ የታክስ ማስከፈያ መጠን፣ታክስ ማበረታቻ እርምጃዎች ሊወስዱ ይችላሉ? ይህ ከሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናስ ደንብ ቁጥር 17/1989 አንቀጽ 76 ጋር እንዴት ይታያል?

# ክፍል ሁለት

# የታክስ መዋቅር በኢፌድሪ መንግሥት

## መግቢያ

በዚህ ክፍል በኢፌዴሪ መንግሥት ያሉ የታክስ አይነቶችን በዝርዝር እንመለከታለን፡፡ በኢፌዴሪ መንግሥት ከሚጣሉና ከሚሰበሰቡ የታክስ አይነቶች ውስጥ፡- የገቢ ታክስ፤ ተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ተርን ኦቨር ታክስ፤ኤክሳይዝ ታክስ፤ ሱር ታክስ፤ የቴንብር ቀረጥ እና የጉምሩክ ቀረጥ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በዚህ ክፍል የምንመለከተው የገቢ ታክስ፣ ተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ተርን ኦቨር ታክስ፤ ኤክሳይዝ ታክስ እና የቴንብር ቀረጥን ብቻ ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል የገቢ ታክስ፣ ተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ተርን ኦቨር ታክስ፤ ኤክሳይዝ ታክስ እና የቴንብር ቀረጥን የሚመለከቱ ህጎች ሰፊ ይዘት ያላቸው በመሆኑ በዚህ አጭር ፅሑፍ እነዚህን ታክሶች የሚመለከቱ ሕጎችን አጠቃላይ ይዘት ሙሉ በሙሉ ማቅረብ የሚቻል አይደለም፡፡ ስለዚህ ፅሑፉ ወይም ትምህርቱ የሚያተኩረው በህጎቹ በታቀፉ የተወሰኑ ነጥቦች ላይ ብቻ ይሆናል፡፡ በተለይም ትምህርቱ የሚያተኩረው ስለታክሶቹ ምንነት፤አጣጣል፤ የታክስ ከፋዮች ግዴታን እና የታክስ ግዴታን አለመወጣት የሚያስከትለውን ኃላፊነት ላይ ይሆናል፡፡

በዚሁ መሰረት ይህ ክፍል አምስት ንዑስ ክፍሎች አሉት፡፡ በመጀመሪያው ንዑስ ክፍል በቅድመ ኢፌዲሪ ያለውን የታክስ መዋቅር በአጭሩ ይዳሰሳል፡፡  በሁለተኛው ንዑስ ክፍል በኢፌዲሪ ያለው የታክስ መዋቅር በሁለት መደብ ማለትም ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ተብለው ይቀርባሉ፡፡ በንዑስ ክፍል ሶስት ደግሞ የቴምብር ቀረጥ ይቀርባል፡፡ በንዑስ ክፍል አራት የታክስ ወንጀሎች፤ በመጨረሻው ንዑስ ክፍል ደግሞ የታክስ ይርጋ ይቀርባል፡፡

በዚሁ መሰረት ሰልጣኞች ይህን ክፍል ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- በኢፌዴሪ መንግስት የሚጣሉ እና የሚሰበሱ የታክስ አይነቶች ላይ የተወሰነ ግንዛቤ ይጨብጣሉ፡፡

- በኢፌድሪ መንግስት ያለውን የታክስ መዋቅር ከቀድመ ኢፌድሪ ካለው የታክስ መዋቅር ጋር ያነጻጽራሉ፡፡
- የገቢ ታክስ ምንነት፤ አጣጣል፤ ማስከፈያ መጠን (መጣኔ) በቂ ግንዛቤ ይኖራቸዋል፡፡
- የገቢ ታክስ አይነቶችን አንድ በአንድ ይለያሉ፡፡
- የገቢ ታክስ ከፋዮች ግዴታ ይዘረዝራሉ፡፡
- የገቢ ታክስ ግዴታ አለመወጣት የሚያስከትለውን ኃላፊነት ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡
- የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የተርን ኦቨር ታክስ ምንነት፣አላማ፤ አጣጣል ያስረዳሉ፡፡
- የተጨማሪ እሴት ታክስና የተርን ኦቨር ታክስ ከፋዮች ግዴታና ይተነትናሉ፡፡
- የተጨማሪ እሴት ታክስና የተርን ኦቨር ታክስ ግዴታአለመወጣት የሚያስከትለውን ኃላፊነት ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡
- የኤክሳይዝ ታክስ ምንነት፤ አላማ፣ የሚከፈልበት ሁኔታና የሚከፈልባቸው ዕቃዎች እና የአከፋፈል ሥርዓት ያስረዳሉ፡፡
- የኤክሳይዝ ታክስ ከፋዮች ግዴታ ያውቃሉ፡፡
- የኤክሳይዝ ታክስ ግዴታን አለመወጣት የሚያስከትለው ሐላፊነት ይረዳሉ፡፡
- የቴምብር ቀረጥ ህጋዊ መሰረትና አፈፃፀም ይገነዘባሉ፡፡
- የቴምብር ቀረጥ ህግን መተላለፍ የሚያስከትለውን ውጤት ይገነዘባሉ፡፡
- በታክስ ላይ ስለሚሰሩ ወንጀሎች በቂ ግንዛቤ ይጨብጣሉ፡፡
- ታክስ የመክፈል ግዴታ በይርጋ የሚታገድበትን ሁኔታ ይረዳሉ፡፡

## 2.1. የታክስ መዋቅር በቅድመ ኢፌድሪ በአጭሩ

በሀገራችን ታክስ የረጅም ጊዜ ታሪክ ያለው ነው፡፡ ታክስ ከመቼ ጀምሮ መጣልና መሰብሰብ እንደተጀመረ በትክክል ባይታወቅም ብዙ ፀሐፊዎች ታሪኩን ከመንግስት ምስረታ ጋር ያቆራኙታል፡፡

በቅድመ ኢፌድሪ የነበረውን የታክስ መዋቅር ከሐይለስላሴ ዘመን በፊት፣ በሐይለስላሴ ዘመን፤ በደርግ ዘመን፤ በሽግግር መንግስት ዘመን ብሎ ከፋፍሎ በአጭሩ ማየት ይቻላል፡፡

በዚህ መሰረት ከሐይለስላሴ ዘመን በፊት ያለው የታክስ ሥርዓት ዘመናዊ አልነበረም፡፡ ታክስ የሚከፈለው በአይነት ነበር፡፡ የዚህ ዘመን ታክስ የእህል ምርቶች፣ የቤት እንስሳዎችና የቤት እንስሳዎች ውጤት (የበግ ፀጉር፣ ቅቤ፣ ወተት) የሚመለከቱ ነበር፡፡

በሐይለስላሴ ዘመን ደግሞ የታክስ ሥረዓቱ ቀደም ሲል ከነበረው የተሻለ ቢሆንም ሙሉ በሙሉ ዘመናዊ አልነበረም፡፡ በዚህ ዘመን በርካታ የታክስ ህጎች የወጡ ሲሆን እነዚህ ህጎችም የ1947 ህገመንግስትን መሰረት ያደረጉ ነበር፡፡ በዚህ ዘመን ከነበሩት የታክስ አይነቶች ውስጥ የገቢ ታክስ፣ የመሬት ታክስ፣ የትምህርት፣ የጤና፣ የእርሻ፣ የመንገድ፣ የጨው፣ የትንባሆ፣ የአልኮል፣የከብት፣አስራት፣ የጉምሩክ ቀረጥ፤የቴንብር ቀረጥ በዋነኝነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በደርግ ዘመን ቀደም ሲል ሥራ ላይ ከነበሩ ታክሶች ውስጥ፡- የመሬት ታክስ፣ የትምህርት ታክስ፣ የጤና ታክስ፣ የኪራይ ገቢ ታክስ፣አስራት፣የተባሉት የታክስ አይነቶች እንዲሰረዙ ተደርገዋል፡፡ በሌሎች ላይም የተለያዩ ማሻሻያዎች ተደርጎባቸዋል፡፡ በዚህ ዘመን ሲጣሉና ሲሰበሰቡ ከነበሩ የታክስ አይነቶች ውስጥ የገቢ ታክስ፣ የከተማ መሬት ኪራይ፣ ታክስ የከተማ ቤት ኪራይ ታክስ፣ የገጠር መሬት መጠቀሚያና ክፍያ፣ ኤክሳይዝ ታክስ፣ ታራዛክሽን ታክስ፣ የሽያጭ ታክስ፣ የጉምሩክ ቀረጥ እና የቴንብር ቀረጥ በዋነኝነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በሽግግር መንግስት ዘመን በክልሎች መቋቋም ምክንያት መሰረታዊ የታክስ ፖሊሲ ለውጥ ተደርጓል፡፡ የተለያዩ ታክሶች ላይ ታክስ መጣኔው እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡ ለምሳሌ ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ የሚጣል ታክስ፣ የንግድ ትርፍ ሥራ ታክስን መጥቀስ ይቻላል፡፡ የታክስ መሰረት እንዲሰፉ ተደርጓል፡፡ ለዚህም አዳዲስ ታክሶችን ተጥለዋል፡፡ ለምሳሌ የማዕድን ገቢ፤የካፒታል ንብረቶች በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ የሚጣል የገቢ ታክስን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ወደ ውጭ በሚላኩ እቃዎች፤- ቡና፣ ሌጦ እና ቆዳ፣ እንሰሳ፣ የዝሆን ጥርስ እና ሌሎች ላይ የተጣሉት ታክሶች ከቡና በስተቀር እንዲነሱ ተደርገዋል፡፡

## 2.2. በኢፌድሪ፡- ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶች

በአሁኑ ጊዜ በስራ ላይ ላሉት የታክስ አይነቶች ሕጋዊ መሰረት ሕገመንግስቱ ነው፡፡ ሕገመንግስቱን መሰረት በማድረግም የተለያዩ የታክስ አዋጆች ወጥተዋል፡፡ አዋጆችን በመንተራስ የተለያዩ ደንቦች ተደንግገዋል፡፡ መመሪያዎችም ወጥተዋል፡፡ በሕገመንግስቱ እና

በእነዚህ ሕጎች መሰረት ሥራ ላይ ያሉ የታክስ አይነቶችን በዝርዝር ከማየታችን በፊት ታክስን በተመለከተ በኢፌድሪ ዘመን የተደረጉ አንዳንድ ለውጦችን ጠቅለል ባለ መልኩ ማየቱ ጠቃሚ ነው፡፡ ከእነዚህ ለውጦች ውስጥ ጥቂቶቹም፡-

- የታክስ ማስከፈያው መጠን መቀነስ፡- ለምሳሌ ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ የሚጣለው የታክስ ማስከፈያ መጠን ከ40% ወደ 35% እንዲቀነስ ተደርጓል፡፡ የጉምሩክ ቀረጥም ማስከፈያ መጠን እንዲሁ ቀንሷል፡፡
- ወደ ውጪ በሚላክ ቡና ላይ የተጣለው ታክስ ተነስቷል፡፡
- የሽያጭ ታክስ በተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲተካ ተደርጓል፡፡
- ታክስን ከተከፋይ ሒሳብ ላይ ገቢ የማድረግ ሥርዓት (tax withholding) ተግባራዊ እንዲሆን ተደርጓል፡፡
- የታክስ ከፋዩ መለያ ቁርጥ ተግባራዊ እንዲሆን ተደርጓል፡፡
- የታክስ መሰብሰብ ሥልጣንም ለገቢ ሚኒስቴር የተሰጠ ሲሆን ታክስ አስገቢው ባለሥልጣንም ግዴታቸውን በማይወጡ ታክስ ከፋዮች ላይ የሚፈለገውን ታክስ በቀጥታ በህግ አስገድዶ ለመሰብሰብ የሚያስችለው ሥልጣን እንዲኖረው ተደርጓል፡፡

### 2.2.1. ቀጥተኛ ታክስ፡- የገቢ ታክስ

በኢፌድሪ መንግስት ከቀጥተኛ ታክስ ጎራ የሚመደበው የታክስ አይነት የገቢ ታክስ ነው፡፡ ለማንኛውም አይነት ታክስ የህግ መሰረቱ ህገመንግስቱ በመሆኑ የገቢ ታክስ መሰረትም የሔው ህገመንግስት ነው፡፡ በአሁኑ ግዜ የገቢ ታክስ የሚጣለው እና የሚሰበሰበው ህገመንግስቱን መሰረት በማድረግ በወጡ ሁለት ሕጎች ነው፡፡ እነሱም፡- የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 እና የሚኒስትሮች ምክር ቤት የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/1994 ናቸው፡፡ እነዚህ ሕጎች የገቢ ታክስን በተመለከተ ለአርባ ዓመት ሲሰራበት የነበረውን የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 173/1961 እና በየጊዜው የተደረጉትን ማሻሻያዎች የተኩ ናቸው፡፡ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 ሁለት ምዕራፍ፤ 16 ክፍሎች እና 120 አንቀጾች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው ክፍል መሰረታዊ ድንጋጌዎችን የያዘ ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ሥነስረታዊ ድንጋጌዎችን የያዘ ነው፡፡ ቀጥለን የመጀመሪያው ክፍል ስር አጠቃላይ ድንጋጌዎች ተብለው ከተቀመጡት ውስጥ መታየት ያለባቸውን አንዳንድ ነጥቦች እንመለከታለን፡፡ መጀመሪያ የገቢ ታክስ ምንነት፡፡

## 2.2.1.1. ምንነት

የገቢ ታክስ ምንነትን ለመረዳት በመጀመሪያ ገቢ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ማየቱ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ ገቢ ለሚለው ቃል አንድ ወጥ የሆነ ትርጉም የለም፡፡ ብዙ ሙሑሮች ወይም ኤክስፐርቶች ቃሉን በተለያየ መንገድ ይጠቀሙበታል፡፡ በመሆኑም ገቢ የሚለው ቃል እንደ አገባቡ የተለያየ ትርጉም ሊይዝ ይችላል፡፡ ይሔን አንድ ፀሐፊ፡-

> Scholars and experts in various discipline tend to give a definition to the terms from the vantage-point of their own fields of specialization and concerns as result of which a consensus on its meaning is hard to come-by በማለት ገቢ ለሚለው ቃል አንድ ወጥ የሆነ ትርጉም ላይ መድረስ እንዳልተቻለ በጥሩ ሁኔታ ገልጾታል፡፡

ስለዚህ የተለያዩ ሙሑሮችና ኤክስፐርቶች ገቢ ለሚለው ቃል የሚሰጡት ትርጉም ከተሰማሩበት ሞያ አንጻር የሚታይ ነው፡፡ ለምሳሌ የኢኮኖሚስት እና የሕግ ባለሙያ ለገቢ የሚሰጡት ትርጉም አንድ ላይሆን ይችላል፡፡ እንዲሁም ገቢ ለሚለው ቃሉ የሚሰጠው ትርጉም እንደ ሐገሩ ሁኔታ ሊለያይ ይችላል፡፡ ይዘቱም እንዲሁ፡፡ በታክስ ሕግ ውስጥ እንኳ ገቢ ለሚለው ቃል ተቀባይነት ያለው አንድ ወጥ ትርጉም ለማግኘት አይቻልም፡፡ ሐገሮች የሔን ችግር ለመፍታት የመረጡት ዘዴ በታክስ ሕግ ውስጥ ገቢ ለሚለው ቃል ትርጉም መስጠትን ነው፡፡ በእኛም ሐገርም የተወሰደው አማራጭ ይሄው ነው፡፡ ለታክስ አላማ የገቢ ግብር አዋጅ ገቢ ለሚለው ቃል የሚከተለውን ትርጉም ሰጥቶታል፡፡

> «**ገቢ**» ማለት ማናቸውም የኢኮኖሚ ጥቅም ሲሆን፣ በመደበኛነት የተገኘ ባይሆንም ከማናቸውም ምንጭ በጥሬ ገንዘብ ወይም አይነት በማናቸውም መልክ ለግብር ከፋዩ የተከፈለው በስሙ የተያዘለትን ወይም የተቀበለውን ጥቅም ሁሉ ይጨመራል፡፡ (አንቀጽ 2(10))

ከዚህ እንደምንረዳው ገቢ የሚከተሉትን ነጥቦችን የያዘ ነው፡፡ እነሱም፡-

- **ኢኮኖሚያዊ ጥቅም**፡- ገቢ በገንዘብ ሊተመኑ የሚችሉ ጥቅሞች እንደ ደመወዝ፣ አለዋንስ፣ ነጻ የጉዞ ትኬት፣ ነጻ ምግብ፣ ነጻ የቤት ኪራይ እና የመሳሰሉት ቀጣሪው ለተቀጣሪው የሚከፍላቸውን የሚመለከት ሊሆን ይችላል፡፡

- **ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙ አይነት**፡ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙ በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት ሊሆን ይችላል፡፡
- **ከመደበኛነት ውጭ የተገኘ፡-** በዚህ ትርጉም ለመሸፈን ገቢ በመደብኛነት የሚገኝ ጥቅም ብቻ የሚመለከት አይደለም፡፡ ገቢው ከመደበኛነት ውጭ የተገኘ ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ አለዋንስ መጥቀስ ይቻላል፡፡
- **ምንጭ፡-** የገቢው ምንጭ የተለያየ ሊሆን ይችላል፡፡ ለገቢ ታክስ አላማ የገቢው ምንጭ የተለያየ መሆን አለመሆኑ ምንም ልዩነት አያመጣም፡፡
- **የገቢውን መሰረት፡-** ታክስ ከፋዩ ገቢው በስሙ የተያዘለት ወይም የተቀበለው ሊሆን ይችላል፡፡ ታክስ ከፋዩ ገና ወደፊት ሊያገኝ የሚችለው ገቢ ለገቢ ታክስ አላማ ገቢ በሚለው ትርጉም የሚሸፈን አይደለም፡፡

አንድ ሰው ከላይ የተጠቀሱትን አምስት ነጥቦች የሚያሟላ ገቢ ማግኘቱ ከተረጋገጠ የገቢ ግብር የመክፈል ሕጋዊ ግዴታ አለበት፡፡(አንቀጽ 4) ባጭሩ የገቢ ታክስ ማለት አንድ ሰው በሚያገኘው ገቢ ላይ የሚጣል እና የሚሰበሰብ ታክስ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ታክስ ከፋዩም ማንኛውም ግለሰብ፤ ድርጅት ወይም ማህበር ሊሆን ይችላል፡፡

አንድ ታክስ ከፋይ የሆነ ሰው የሚያገኘው ገቢ ሁሉ ታክስ የሚከፈልበት ላይሆን ይችላል፡፡ አንድ ታክስ ከፋይ መክፈል ያለበትን የታክስ መጠን ለመወሰን ጥቅል ወይም ያልተጣራ ገቢ እና ታክስ የሚከፈልበት ገቢን መለየት ያስፈልጋል፡፡ ጥቅል ወይም ያልተጣራ ገቢ ማንኛውም ኢኮኖሚያዊ ጥቅምን የሚመለከት (አንቀጽ 2(10)) ሲሆን ታክስ የሚከፈልበት ገቢ ማለት ደግሞ በገቢ ግብር አዋጅን በአዋጁ መሰረት በሚወጡት ደንቦች ማናቸውም ወጪ እና ሌሎች ተቀናሽ ሂሳቦች ከተቀነሱ በኋላ የሚቀረው የገቢ መጠን ነው፡፡ (አንቀጽ 2(11)) በመሆኑም ግብር የሚከፈልበት ገቢ የሚወሰነው አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሰረት ከጥቅል ገቢ መቀነስ ያለባቸው ወጪዎች እና ሌሎች ተቀናሽ ሂሳቦች ከተቀነሱ በኋላ ነው፡፡ ለምሳሌ የገቢ ግብር አዋጅ የገቢ ግብር የማይከፈልባቸው ገቢዎች (exemption)፣የገቢ ግብር ከሚከፈልበት ገቢ ውስጥ የማይካተቱ (exclusion) እና ተቀናሽ ወጪዎችን (deductible expenses) ይደነግጋል፡፡ ስለዚህ የገቢ ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለመወሰን መጀመሪያ ከጥቅል ገቢ ላይ ግብር የማይከፈልባቸው ገቢዎች ወይም የገቢ ግብር ከሚከፈልበት ገቢ ውስጥ የማይካተቱ

ወይም ተቀናሽ ወጪዎችን መቀነስ አለባቸው ማለት ነው፡፡ በአጭሩ ታክስ የሚከፈልበት ገቢ ማለት የገቢ ግብር መጠንን ለማስላት መሰረት የሆነ የገቢ መጠን ነው ለማለት ይቻላል፡፡

### 2.2.1.2. ተፈጻሚነት ወሰን

የገቢ ህግ ተፈጻሚነት ወሰን ለመገንዘብ የገቢ ታክስን የመጣል ሥልጣንን ለመወሰን የሚረዱ መርሆችን ማየቱ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ የገቢ ታክስን የመጣል ሥልጣንን ለመወሰን የሚረዱ ሶስት መርሆች አሉ፡፡

አንደኛው የግዛት ወይም የምንጭ መርህ ነው፡፡ በዚህ መርህ መሰረት የገቢ ግብርን የመጣል ሥልጣን የሚወሰነው የገቢው መሰረት ምንጭ በማየት ነው፡፡ የገቢ ሥልጣንን ለመወሰን የገቢው መሰረት ምንጭ በማድረግ ከሆነ አንድ ሰው በአንደ ሐገር ውስጥ ነዋሪ ባይሆንም የገቢ ግብር ሊጣልበት ይችላል፡፡

ሁለተኛው የነዋሪነት መርህ ነው፡፡ በዚህ መርህ መሰረት የገቢ ግብርን ለመጣል የሚታየው የገቢው ባለቤት መኖሪያ ነው፡፡ ገቢውን ያገኘው ሰው ነዋሪነቱ በአንድ ሐገር ውስጥ ከሆነ ያ ሰው በሚያገኘውን ገቢ ላይ የሚኖርበት ሐገር መንግሥት የገቢ ግብር የመጣል ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

ሶስተኛው የዜግነት መርህ ነው፡፡ በዚህ መርህ መሰረት የገቢ ግብር ሥልጣን ለመወሰን የሚታየው ገቢውን ያገኘው ሰው ዜግነት ነው፡፡ በዚህ መርህ መሰረት የሐገሪቱ ዜግነት ያለው ሁሉ መኖሪያው የትም ሆነ የት እንዲሁም የገቢ ምንጭ የሚገኝበት ግዛት የትም ሆነ የት በሚያገኘው ገቢ ላይ ግብር መክፈል አለበት፡፡ ሐገሮች የገቢ ግብርን ለመጣል አንዱን ወይም ሁሉንም መርሆች በማጣመር ተግባራዊ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

ወደ ሐገራችን ስንለመለስ ኢትዮጵያ የተከተለችው የነዋሪነት መርህን ነው፡፡ (አንቀጽ 3(1)) በመሆኑም በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ የሆነ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሁም በኢትዮጵያ ውጭ ባገኘው ገቢ ላይ ነዋሪ ለሆነበት ለኢትዮጵያ መንግስት የገቢ ታክስ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡ ስለዚህ ታክስ ከፋይ ነዋሪነቱ በኢትዮጵያ እስከ አሁን ድረስ የገቢ ምንጩ ከኢትዮጵያ ውስጥ

ወይም ውጭ መሆኑ ልዩነት አያመጣም፡፡ ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው ከኢትዮጵያ ውጪ ባገኘው ገቢ ላይ ገቢው ለተገኘበት አገር ግብር የከፈለ መሆኑ ሲረጋገጥ በውጭ አገር የተከፈለው ታክስ እንዲካካስለት መጠየቅ ይችላል፡፡ (አንቀጽ 7)

በሌላ በኩል አዋጁ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆኑ ሰዎችን በተመለከተ ተፈፃሚ የሚሆነው ኢትዮጵያ ውስጥ ባገኙት ገቢ ላይ ብቻ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ ለምሳሌ ዋና መሥሪያ ቤቱ አሜሪካ የሆነ ድርጅት በኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ ሥራ የሚከናውን ከሆነ በድርጅቱ ላይ ታክስ የሚጣለው በኢትዮጵያ ውስጥ በሚያገኘው ገቢ ላይ ብቻ ይሆናል፡፡ ድርጅቱ በዋናው መሥሪያ ቤቱ በሚያገኘው ትርፍ ላይ ታክስ ሊጣል አይችልም፡፡ ምክንያቱም ድርጅቱ በኢትዮጵያ ነዋሪ ስላልሆነ ነው፡፡ ስለዚህ አለም አቀፍ ታክስን በተመለከተ የታክስ ከፋዩ መኖሪያ ወይም የገቢ ምንጩ መሰረት በኢትዮጲያ ውስጥ መሆን አለበት፡፡ ከታክስ ከፋዩ ዜግነት ግን ታክስን ለመጣል መሰረት ሆኖ አያገለግልም፡፡

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. አንድ ታክስ ከፋይ በኢትዮጵያ ነዋሪ ነው የሚባለው መቼ ነው?
2. የገቢ ግብር የመጣል ሥልጣንን ነዋሪነትን መሰረት ከማድረጉ በስተጀርባ ያለው ምክንያት ምንድነው?
3. የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 7 ዋና አላማ ምንድነው?

### 2.2.1.3. የገቢ ምንጭ

ለገቢ ግብር መሰረት አንድ ግብር ከፋይ የሚያገኘው ገቢ ነው፡፡ ስለዚህ የገቢ ግብር ለመጣል መጀመሪያ ግብሩ የሚከፈልባቸው የገቢ ምንጮች መኖር አለበቸው፡፡ የገቢ ግብር የሚጣልባቸው የገቢ ምንጮችም በህጉ ተለይተው መታወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ በመሆኑም ግብር የሚከፈልባቸው የገቢ ምንጮች በገቢ ግብር አዋጅ ውስጥ እንዲዘረዘሩ ተደርገዋል፡፡ (አንቀጽ 6) በአዋጁ የተዘረዘሩት ግብር የሚከፈልባቸው ገቢ ምንጮችም፡-

- ከቅጥር የሚገኝ ገቢ
- ከንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የሚገኝ ገቢ

- የመዝናናት ሥራ የሚሰራ፣ ሙዚቀኛ ወይም ስፖርተኛ፣ በግል ካከናወነው ሥራ የሚያገኘው ገቢ
- ነዋሪነቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ያልሆነ ሰው በቋሚ የንግድ ሥራ ድርጅት አማካኝነት ከሚያከናውነው የንግድ ሥራ የሚያገኘው ገቢ
- በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኝ ቋሚ የንግድ ሥራ ድርጅት ተንቀሳቃሽ ንብረት የሚገኝ ገቢ እና እነዚህን ንብረቶች በመሸጥ የሚገኝ ገቢ
- ከማይንቀሳቀሱ ንብረቶች እና ከተንቀሳቃሻቻቸው የተገኘ ገቢ፣ ከቁም ከብት፣ ከግብርና እና ከደን የሚገኝ ገቢ፣ ከማይንቀሳቀሱ ንብረቶች አላባ እና ማናቸውም ሌላ መብት የሚገኝ ገቢ፣ እነዚህ ንብረቶች በኢትዮጵያ ውስጥ እስከሆኑ ድረስ፣
- ነዋሪነቱ በኢትዮጵያ የሆነ ኩባንያ የሚያከፋፍለው የአክስዮን ድርሻ
- ነዋሪነቱ በኢትዮጵያ የሆነ የተመዘገበ የሽርክና ማህበር የሚያከፋፍለው የትርፍ ድርሻ፣
- የራስ በሆነ ነገር ሌላ ሰው እንዲጠቀምበት የተሰጠ ፈቃድ ክፍያ
- የፈጠራ መብት በማከራየት የሚገኝ ገቢ፣

ግብር የሚከፈልባቸው የገቢ ምንጮች እነዚህ የተዘረዘሩት ብቻ እንዳልሆኑና ከእነዚህ ከተዘረዘሩት ውጪ ሌሎች የገቢ ምንጮች ሊኖሩ እንደሚችሉ በአንቀጹ ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ ከተዘረዘሩት የገቢ ምንጮች ውጭ ሌሎች በገቢ ግብር በአዋጁ ለመሸፈን አዋጁ ለገቢ የሰጠውን ትርጉም ማሟለት ይኖርባቸዋል፡፡

### 2.2.1.4. የገቢ ታክስ ሥርዓት

በአለም ላይ ሁለት ዓይነት የታክስ ሥርዓቶች አሉ፡፡ እነሱም ግሎባል (global) እና ሠንጠረዣዊ (scheduler)ሥርዓት ናቸው፡፡ የመጀመሪያ ሥርዓት የድምር ዘይቤን የተከተለ ነው፡፡ ግብር ከፋዩ የሚያገኘው ማናቸውም ገቢ አንድ ላይ ከተደመሩ በኋላ ባለው የታክስ ማስከፈያ መጠን መሰረት ታክሱ ተሰልቶ እንዲከፈል ይደረጋል፡፡ አንድ ታክስ ከፋይ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የንግድ ሥራዎች ቢኖረው፣ በአንዱ ንግድ ሥራ ላይ የደረሰው ኪሳራ በሌላው ንግድ ሥራ ከተገኘው ገቢ ጋር እንዲቻቻል ተደርጎ ታክሱ የሚሰላ ይሆናል፡፡

በሁለተኛው ሥርዓት ለገቢ ታክስ አላማ ሲበል የተለያዩ ገቢዎች በተለያዩ ሠንጠረዦች ይመደባሉ፡፡ ምደባውም የገቢውን ባህሪ እና ምንጭ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ገቢዎቹ

የሚወድቁበት ምድብም ሠንጠረዥ ይባላል፡፡ በዚህ ሥርዓት አንድ ሰው ለእያንዳንዱ ሠንጠረዥ ለብቻ ለብቻ ግብር ይከፍላል፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው ከመቀጠር የሚያገኘው ገቢ በአንድ ሠንጠረዥ ውስጥ ሆኖ፤ ከንግድ ሥራ የሚያገኘው ገቢ ዳግም በሌላ ሠንጠረዥ ሥር ሊሆን ይችላል፡፡ የገቢ ግብሩን ለማስላት ከመቀጠር እና ከንግድ ሥራ የሚያገኘው ገቢ ለብቻ ለብቻ ይታያል ማለት ነው፡፡ ታክስ ከፋዩ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ ንግድ ሥራ ቢኖረው በአንዱ ንግድ ሥራ ላይ ደረሰው ኪሳራ ከሌላው ንግድ ሥራ ከተገኘው ገቢ ጋር እዲቻቻል አይደረግም፡፡

ለገቢ ግብር አወሳሰን ሐገሮች ከሁለቱ አንዱን ሥርዓት ሊከተሉ ይችላሉ፡፡ ኢትዮጵያ የተከተለችው ሠንጠረዣዊ ሥርዓትን ነው፡፡ በዚሁ መሰረት የገቢ ግብር አዋጅ የተለያዩ የታክስ መሠረቶችን በአራት ሠንጠረዥ ከፋፍሏል፡፡ እነሱም፡- ሠንጠረዥ ‘ሀ’፤ ሠንጠረዥ ‘ለ’፤ ሠንጠረዥ ‘ሐ’ እና ሠንጠረዥ ‘መ’ ናቸው፡፡ ሠንጠረዥ ‘ሀ’ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ላይ የሚጣል ታክስን፣ ሠንጠረዥ ‘ለ’ ደግሞ የቤት ኪራይ ታክስን፣ ሠንጠረዥ ‘ሐ’ ንግድ ሥራ ትርፍ ታክስን፣ ሠንጠረዥ ‘መ’ ደግሞ ሌሎች ገቢዎች ላይ የሚጣሉ የገቢ ታክስን የሚመለከቱ ናቸው፡፡

#### 2.2.1.5. የገቢ ታክስ አይነቶች

በገቢ ግብር አዋጅ የታቀፉት የገቢ ታክስ አይነቶች፡- ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ታክስ፣ የቤት ኪራይ ታክስ፣ ንግድ ሥራ ትርፍ ታክስ፣ ሌሎች ገቢዎች ላይ የሚጣሉ ታክስ ሲሆኑ እነዚህንም አንድ በአንድ ቀጥለን ለማየት እንሞክራለን፡፡ መጀመሪያ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ታክስ፡፡

##### 2.2.1.5.1. ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ታክስ (ሠንጠረዥ “ሀ”)

**ሀ. ምንነት**

ከመቀጠር የሚገኝ የገቢ ታክስ በብዙ ሐገሮች ያለ አንዱ የገቢ ታክስ አይነት ነው፡፡ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ማለት ከመቀጠር በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት የተገኘ ማናቸውም ክፍያ ወይም ጥቅም ሲሆን ከቀድሞ ቅጥር የተገኘን ገቢ እና ወደፊት ለመቀጠር አስቀድሞ የሚደረግ ክፍያን እንደሚጨምር በአዋጅ ተመልክቷል፡፡ (አንቀጽ12) ከመቀጠር የሚገኘው ኢኮኖሚያዊ ጥቅም

የተለያየ ሊሆን ይችላል፡፡ ቀጣሪው ለተቀጣሪው የሚከፍለው ደመወዝ፣ ትርፍ ሰአት ክፍያ፣አለዎንስ(ትራንስ ፓርት፣ የቤት፣ የቦታ፣ የመዛወሪያ፣ የበረሐ፣የትምህርት እና የመሳሰሉት) ቦነስ፣ጡረታ፣ የስንብት ክፍያ፣ካሳ ወ.ዘ.ተ መጥቀስ ይቻላል፡፡

ከመቀጠር የሚገኘውን ገቢ ግብር ለማስላት በመጀመሪያ ታክስ ከሚከፈልበት ገቢ ውስጥ የማይካተቱ ወይም ከገቢ ታክስ ነፃ የሆኑ ገቢዎች መታወቅ አለባቸው፡፡ ለስሌቱም የታክስ ማስከፈያ መጠን (Tax rate) በአዋጅ ተቀምጧል፡፡ የታክስ ማስከፈያ መጠንም እንደሚያመለክተው አንድ ወጥ (uniform) ሳይሆን እስከ ተወሰነ ድረስ (እስከ ብር 5001) እየጨመረ የሚሄድ (progressive) ነው፡፡ ከአምስት ሺ አንድ ብር ድረስ ከቅጥር የሚገኘው ገቢ እየጨመረ በሄደ ቁጥር የታክስ ማስከፈያው መጠን እየጨመረ ይሄዳል ማለት ነው፡፡ ከ አምስት ሺ አንድ በላይ ግን የማስከፈያው የተወሰነ ነው፡፡ (ሰላሳ አምስት ፐርሰንት)

**ለ. ከታክስ ነጻ የሆኑ ገቢዎች**

ከመቀጠር ከሚገኝ ገቢ ታክስ ነፃ የሆኑ ገቢዎች በሁለት ክፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ አንደኛው common exemption የምንለው ሲሆን ይሔም በአዎጁ አንቀጽ 10 ተመልክቷል፡፡ በዚህ አንቀፅ መሰረት ለአንድ ተቀጣሪ በመቀጠር ከሚያገኘው ገቢ የመጀመሪያው አንድ መቶ አምስት ብር ግብር ከሚከፈልበት ገቢ ውስጥ አይካተትም፡፡ ይህ አለመካተቱ (exclusion) ከመቶ አምሳ ብር በታች የሚያገኝ ተቀጣሪን ብቻ ሳይሆን ከመቶ ሃምሳ ብር በላይ የሚያገኝ ተቀጣሪንም የሚመለከት ነው፡፡ ስለዚህ ከዜሮ እስከ አንድ መቶ ሃምሳ ብር የሚያገኝ ተቀጣሪ ከገቢ ግብር ነፃ ሲሆን ከመቶ አምስት ብር በላይ የሚያገኝ ተቀጣሪም በተመለከተ በመጀመሪያው መቶ አምሳ ብር ላይ ግብር አይከፍልም ወይም የመጀመሪያው መቶ አምሳ ብር ግብር ከሚከፈልበት ገቢ ውጪ ነው ማለት ነው፡፡

ሁለተኛው direct exemption የምንለው ነው፡፡ እነዚህም በገቢ ግብር አዋጅ፣ በገቢ ግብር እና ደንብ በቀጥታ ከገቢ ታክስ ነፃ የተደረጉ ገቢዎችን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ በገቢ ግብር አዋጅ መሰረት ከታክስ ነፃ የሆኑ ገቢዎችም፡-

- በማናቸውም የአስራ ሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ለአንድ ቀጣሪ ከአንድ ወር ለበለጠ ጊዜ ያገለገለ ማንኛውም ባለሙያ ያልሆነ ተቀጣሪ የሚያገኘው ገቢ፣
- በቀጣሪዎች የሚዋጣ ከሰራተኛው የወር ደመወዝ 15% ያልበለጠ የጡረታ መዋጮ ፕሮቪዳንት ፈንድ እና ማናቸውም ዓይነት የጡረታ ጥቅም
- ለዲፕሎማቲክና የቆንስላዎች ወኪሎች እና ሌሎች ተቀጣሪዎች የሚከፈል ክፍያ
- የአካል ጉዳት ወይም በሞት አደጋ ምክንያት የሚከፈል ካሳ
- በአለም ዓቀፍ ስምምነቶች ከገቢ ታስ ነፃ የተደረጉ ገቢዎች ናቸው፡፡

በገቢ ግብር ደንብ መሰረት ነፃ የተደረጉ ክፍያዎች ደግሞ፡- ለሕክምና አገልግሎት የሚከፈል ገንዘብ፤ የመዛዋሪያ አበል፤ የአየር ፀባይ አበል፤ የመጓጓዣ አለዋንስ፤ ውሎ አበል፤ የቦርድ አበል፤ የቤት ውስጥ ሥራዎችን ለማከናወን በመኖሪያ ቤት የሚቀጠሩ ሰዎች የሚያገኙት ገቢ ናቸው፡፡

### ሐ. ግዴታዎች

የሰንጠረዥ 'ሀ' ገቢን በተመለከተ ቀጣሪው ለተቀጣሪው ከሚከፍለው ክፍያ ላይ ግብሩን ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ አለበት፡፡ ቀጣሪው ለቀጣሪው ቀንሶ የስቀረውንም ግብር ከእያንዳንዱ ወር መጨረሻ አንስቶ ባሉት ሰላሳ ቀን ውስጥ ለግብር አስገቢው ባለስልጣን ገቢ የማድረግ አለበት፡፡ በተጨማሪም ቀጣሪው የተቀነሰውን ግብር ለግብር አስገቢ ባለስልጣን ገቢ በሚያደረግበት ጊዜ በወሩ ውስጥ ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ያገኙትን ሰራተኞች ዝርዝር የሚያሳይ መረጃ አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡ ይህ የሚሰጠው ተቀጣሪው ካገኘው ገቢ ላይ ተቀንሶ የቀረውና ከቀጣሪው ከሚቀርብ መግለጫ ጋር ለግብር አስገቢው ባለስልጣን ገቢ የተደረገው ሂሳብ ገንዘብ ገቢ ከተደረገበተ ቀን ጀምሮ የሚፀና በግብር አስገቢው ባለስልጣን የተወሰነ ግብር እንደሆነ ተደረጎ ይወሰዳል፡፡

የገቢ ግብር አዋጅ በቀጣሪ ብቻ ሳይሆን በተቀጣሪው ላይም ግዴታ ይጥላል፡፡ አንዱ ግዴታም ገቢን የማሳወቅ ግዴታ ነው፡፡ ይህም ግዴታ የተጣለው በሁሉም ተቀጣሪ ላይ ሳይሆን በተወሰኑ

ተቀጣሪዎች ላይ ነው። የመጀመሪያው ከአንድ ቀጣሪ በላይ ተቀጥሮ የሚሰራን ተቀጣሪ የሚመለከት ነው። በዚህ መሰረት አንድ ተቀጣሪ ከአንድ በላይ ለሆነ ቀጣሪ ተቀጥሮ ገቢ የሚያገኝ ከሆነ ገቢውን የማሳወቅ ግዴታ አለበት። ሁለተኛው የዲፕሎማቲክ መብት ባላቸው ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ የውጭ ሐገር መንግስታት ኤምባሲዎች ሚሲዮኖችና በማናቸውም የኮንሰለር ተቋሞች የሚሰራ ተቀጣሪን የሚመለከት ነው። የዲፕሎማቲክ መብት ባላቸው ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ የውጭ ሐገር መንግስታት ኤምባሲዎች ሚሲዮኖችና በማናቸውም የኮንሰለር ተቋሞች የሚሰራ ተቀጣሪ ገቢውን ራሱ አስታውቆ ግብሩን መከፈል አለበት። አንድ ተቀጣሪ በአንድ የግብር አመት ውስጥ ያገኘው ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሠንጠረዥ 'ሀ' ገቢ ብቻ የሆነ እንደሆነ ገቢውን የማሳወቅ ግዴታ የለበትም።

***የመወያያ ጥያቄ***

*የተወሰኑ ገቢዎችን በተመለከተ አንድ ሰው ገቢ እያገኘ መሆኑ እየታወቀ ከገቢ ግብር ታክስ ነጻ እንዲሆን ተደርጓል ወይም ታክስ አይከፍልም። ከሥራ ግብር ነጻ ከተደረጉት እያንዳንዱ ገቢዎች በስተጀርባ ያለው ምክንያት ምንድነው?*

### 2.2.1.5.2. የቤት ኪራይ ገቢ ታክስ (ሠንጠረዥ "ለ")

#### ሀ. ምንነት

በአዋጅ መሠረት በማናቸውም ሁኔታ ከተከራየ ቤት በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር መከፈል እንዳለበት ተደንግጓል። (አንቀጽ 14) የገቢ ግብር ደንብ የአንቀጽ 5 መሰረት ገቢ ተከራዩ ለአከራዩ በጥሬ ገንዘብና በሌላም ዓይነት የሚከፍለው ሂሳብ፣ ተከራዩ በአከራዩ ስምና ስለአከራዩም ሆኖ የሚከፍለው ሂሳብ፣ ተከራዩ ከአከራዩ ጋር ባደረገው የኪራይ ውል መሰረት ለመሬቱ ወይም ለቤቱ ማሻሻያ ወይም ማደሻ የሚያደርገው ወጪ፣ በዚህ ዓይነት የሚደረገው የመሬት ወይም የቤት ማደሻ ወይም ማሻሻያ ወጪ ተከራዩ ለአከራዩ ከሚከፍለው የቤት ኪራይ ሌላ በተጨማሪ ተከራዩ ወጪ የሚያደርገውን የሚጨምር ነው። (አንቀጽ 5)

በተጨማሪም ግብር ከፋዩ ቤቱን ወይም ግቢውን ከነዕቃው ያከራየ ከሆነ የዕቃው ወይም የመሣሪያው ኪራይ በጠቅላላው ገቢ ጋራ ይደመራል። ተከራይቶ በማከራየት የሚገኘው ገቢ የቤቱ ባለቤት ለሆነው አከራይ ከሚከፈለው የኪራይ ዋጋ የበለጠ ከሆነ ተከራይተው የሚያከራዩ

ግብር ከፋዮች ግብሩን የሚያከራዩ ግብር ከፋዮች ግብሩን የሚከፍሉት በሚያገኙት የገቢ ልዩነት ላይ ነው፡፡

ተከራይ የተከራየውን ቤት መልሶ እንዲያከራይ የሚፈቅድ የቤት ባለቤት ተከራዩ ግብሩን ባይከፍል ስለእርሱ ሆኖ ግብሩን የመክፈል ኃላፊነት አለበት፡፡ ምክንያቱም ቤቱን ተከራይቶ ያከራየው በባለቤቱ ፈቃድ በመሆኑ ነው፡፡ ተከራዩ ቤቱን መልሶ ያከራየው ከቤቱ ባለቤት ፈቃድ ውጪ ከሆነ የቤቱ ባለቤት ይህ ግዴታ የለበትም፡፡

ለኪራይ የሚሰሩ ቤቶችን አስመልክቶ በቤቱ ባለቤት እና በሕንፃው ሥራ ተቋራጭ የቤቱ ግንባታ የተጠናቀቀ ወይም ቤቱ የተከራየ መሆኑን ለሚመለከተው አካል የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው፡፡

በአጠቃላይ የሠንጠረዥ 'ለ' የአፈፃፀም ወሰን ቤትን በማከራየት በሚገኝ ገቢ ላይ የተወሰነ ነው፡፡ ነገር ግን በዚህ ሠንጠረዥ ውስጥ የማይሸፈን በስተቀር አለ፡፡ ይህም በስተቀር የንግድ ድርጅትን ለንግድ ሥራው ጥቅም ላይ የሚውሉ ዕቃዎችንና መሣሪያዎችን በቤቱ ጭምር ማከራየት ነው፡፡ ለንግድ ሥራው ጥቅም ላይ የሚውሉ ዕቃዎችንና መሣሪያዎችን ከቤቱ ጭምር ማከራየት በሠንጠረዥ 'ሐ' ሥር የሚወድቁ ናቸው፡፡

### ለ. ተቀናሽ የሚደረጉ ወጪዎች

የገቢ ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለመወሰን ከጠቅላላው ገቢ መቀነስ ያላባቸው ተቀናሽ ሒሳቦች በአዋጅ ተዘርዝረዋል፡፡ እነዚህም መዝገብ የሚይዙ እና የማያዙ ብላን ከፋፍለን ማየት እንችላለን፡፡ መዝገብ የማይዙ ግብር ከፋዮችን በተመለከተ የመሬት ግብር፤ የሕንፃ ታክስ እና የሚከራየውን ንብረት ማደሻ፣ መጠገኛና የእርጅና መተኪያ (ዲፒሪሲየሺን) የሚሆን ከቤት፤ ከቤት እቃና ከመሳሪያ ከሚገኘው ጠቅላላ ገቢ አንድ አምስተኛው መቀነስ ያለባቸው ተቀናሽ ሒሳቦች ናቸው፡፡

መዝገብ የሚይዙ ግብር ከፋዮች ደግሞ፡- የመሬት ግብር፤ የሕንፃ ታክስ እና ግብር ከፋዮች የኪራዩን ገቢ ለማግኘት፤ለኪራዩ ንግድ ሥራ ዋስትና ለመስጠት፤ እንቅስቃሴውን ለማስቀጠል የተደረጉ ወጪዎች ከጠቅላለው ገቢ ላይ ተቀናሽ መሆን ያለባቸው ሒሳቦች ናቸው፡፡ እነዚህም ተቀናሽ ሒሳቦችም የመሬት ሊዝ፤ ለቤቶች፤ ለቤት እቃና ለመሳሪያ ማደሻ፤መጠገኛና ለእርጅና

መተኪያ፣ የባንክ ወለድ፤ የኢንሹራንስ አረቦን የሚያጠቃልሉ ናቸው፡፡ እነዚህ ተቀናሽ ሂሳቦች የሚከራየውን ንብረት ለማደስና ለመጠገን የሚወጡ ወጪዎች ናቸው፡፡ አንድ ንብረት ሁል ጊዜ ባለበት ሁኔታ ሊቆይ አይችልም፡፡ በእርጅና ምክንያት ዋጋው ሊቀንስ ይችላል፡፡ ግብር የሚከፈልበት ጊዜ የዋጋ ዲፕሪሲያሽን ከጠቅላላው ገቢ መቀነስ አለበት፡፡ ተቀናሽ የሚደረጉት ሒሳቦች ግብር ከፋዩ ያወጣውን ወጪ ለመሸፈን ነው፡፡

**ሐ. ማስከፈያ መጠን**

የሠንጠረዥ ‘ለ’ ገቢ ግብር ታክስ የሚከፈለው በአመት ነው፡፡ አዋጅ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅቶች ገቢ እና በግለሰቦች ገቢ ላይ የተለያዩ የግብር ማስከፈያ መጠን ደንግጓል፡፡ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅቶች ገቢ በተመለከተ የማስከፈያ ልኩ በቁርጥ የተወሰነ ነው፡፡ ይሔም ግብር ከሚከፈልበት ገቢ ላይ ሰላሳ በመቶ ነው፡፡ በሌላ በኩል የግለሰቦችን ገቢ የግብር ማስከፈያው መጠን እየጨመረ የሚሔደ ነው፡፡ ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው ከዜሮ እስከ አንድ ሺ ስምንት መቶ ብር የቤት ኪራይ ገቢ ከገቢ ግብር ነፃ ነው፡፡

2.2.1.5.3. **የንግድ ሥራ ትርፍ ታክስ (ሠንጠረዥ “ሐ”)**

**ሀ. ምንነት**

በአዋጅ በግልፅ እንደተመልከተው የሰንጠረዥ ሐ የገቢ ግብሩ የሚጣለው እና የሚሰበሰበዉ ከንግድ ሥራ እንቅስቃሴ በተገኘ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ላይ ነው፡፡ (አንቀጽ 17) የንግድ ሥራ ወይም ንግድ ማለት በማናቸውም ሰው አማካኝነት ለትርፍ የሚከናወን የኢንዱስትሪ፣ የንግድ፣ የሙያ ወይም የጣልቃ ገብ ሥራ እቅስቃሴ ወይም በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ እንደ ንግድ ሥራ ዕውቅና የተሰጠው ማናቸውም ሌላ እንቅስቃሴ ነው፡፡ ሆኖም ግን የክልል መንግስታት በሚያወጡት የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ሥራ ገቢ ግብርን አያጠቃልልም፡፡ (አንቀጽ 8 (3))

ግብር የሚከፈልበት የንግድ ሥራ ገቢ ግብር የሚወሰነው የግብር አመቱ የሚዘጋጀውን የትርፍና ኪሣራ ሂሳብ መግለጫ ወይም የገቢ መግለጫ ነው፡፡ የገቢ መግለጫውም የሚዘጋጀው በአጠቃላይ የሒሳብ አያያዝ መርህን በገቢ ግብር አዋጅ ድንጋጌ እና ግብር አስገቢው ባለስልጣን በሚያወጣውን መመሪያ መሰረት በማድረግ ነው፡፡

## ለ. ከታክስ ነፃ የሆኑ ገቢዎችና ተቀናሽ መደረግና ተቀናሽ የማይደረጉ ወጪዎች

ከገቢ ግብር ነፃ የሆኑ ገቢዎች እንዲሁም ተቀናሽ መደረግ ያለባቸው እና ተቀናሽ የማይደረጉ ወጪዎችን በገቢ ግብር አዋጅ እና ገቢ ግብር ደንብ ተዘርዝረዋል፡፡ በዚሁ መሰረት ከንግድ ሥራ ገቢ ግብር ነፃ የሆኑ ገቢዎች፡-

- አንድን ቴክኖሎጅ ለተወሰነ ሁኔታ እንዲስማማ በማድረግ ወይም አዲስ የፈጠራ ሐሳብ በማቅረብ እና ወጪን ለመቀነስ የሚያስችሉ አሠራሮችን ሥራ ላይ በማዋል የሚሰጥ ሽልማት፡
- በማናቸውም መልክ የላቀ ተግባር ላከናወኑ ሰዎች የሚሰጥ ሽልማት፡
- በኢትዮጵያ ውስጥ ፀንቶ በሚሠራበት ሕግ በዓለም አቀፍ ስምምነት ወይም ሚኒስትሩ በሚያደርገው ወይም በሚፈቅደው ስምምነት መሰረት በተለይ ግብር እንዳይከፈልበት የተደረገ ገቢ
- የፌዴራል እና የክልል መንግስታት እንዲሁም የከተማ መስተዳድሮች የመንግስት መ/ቤቶች እና የኢትዮጲያ ብሔራዊ ባንክ በሥራቸው አጋጣሚ የሚያገኙት ገቢ ናቸው፡፡

እንዲሁም ከንግድ ሥራ ትርፍ ተቀናሽ መደረግ ያለባቸው ወጪዎች በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 20-29 እና ገቢ ግብር ደንብ አንቀጽ 8-14 ሥር ተዘርዝረዋል፡፡ በአጠቃላይ ከንግድ ሥራ ትርፍ ተቀናሽ መደረግ ያለባቸው ወጪዎች ግብር ከፋይ ለንግድ ሥራው ገቢን ለማግኘት፣ ለንግድ ሥራው ዋስትና ለመስጠትና እንቅስቃሴውን ለመቀጠል የተደረጉ ወጪዎችን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ተቀናሽ የማይደረጉ ወጪዎች ዝርዝር በርካታ ሰሆኑ ጥቂቶቹ፡-

- የእርጅና ቅናሽ የሚደረግለትን የንግድ ሥራውን ሀብት ለማግኘት፣ ለማሻሻል፣ ለማደስ እና መልሶ ለመገንባት የተደረገ ወጪ፣

- የኩባንያውን አክስዮን ወይም ለተመዘገበ የሽርክና ማህበር መሰረት የሆነውን ካፒታል ማሳደግ፣
- ከተቀጣሪው የወር ደሞዝ 15% (አስራ አምስት በመቶ) በላይ የሚደረግ የጡረታ መዋጮ ወይም የፕሮቪደንት ፈንድ፣
- ባለአክስዮኖች እንዲያውቁት የተደረገ አክስዮን ድርሻ እና የተከፈለ የትርፍ ድርሻ፤
- በብሔራዊ ባንክና በንግድ ባንኮች መካካል በተደረገ ብድር ከሚታሰብ የወለድ መጣኔ 2 (ሁለት በመቶ) በላይ የወለድ ወጪ፣
- የመድን ዋስትና ሽፋን፣
- በጥፋት ምክንያት የተከፈለ የጉዳት ካሳ እና መቀጫ፣
- በሰንጠረዥ "ሐ" ገቢ ላይ የተከፈለ ግብር ፣ወይም ተመሳሽ የሚደረግ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ የንግድ ድርጅቱን ወክሎ በተለያዩ ቦታዎች ለመገኘት የሚደረግ ወጪ፣
- የግል ፍጆታ ወጪዎች
- በዚህ አዋጅ ወይም ይህንን አዋጅ መሰረት በማድረግ በሚወጣ ደንብ ከተደረገ ገደብ በላይ የተደረገ ወጪ፣
- የመዝናኛ ወጪዎች፣
- ስጦታ ወይም ዕርዳታ ናቸው፡፡

**ሐ. ማስከፈያ መጠን**

አዋጁ ግብር ከፋዮችን በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅትቶች እና በንግድ ሥራ የተሰማሩ ሌሎች ግብር ከፋዮች በማለት የተለያዩ የግብር ማስከፈያ መጠን ይጥላል፡፡ በሕግ ሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅቶች ግብር ከሚከፈልበት ገቢዎች ላይ ሰላሳ በመቶ ግብር የሚከፍሉ ሲሆን በንግድ ሥራ የተሰማሩ ሌሎች ግብር ከፋዮች ደግሞ በተቀመጠው ሠንጠረዥ ሐ መሠረት ይከፍላሉ፡፡ ከብር ዜሮ እስከ አንድ ሺ ስምንት መቶ ብር በንግድ ሥራ ትርፍ ከገቢ ግብር ነፃ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡

## መ. የግብር ከፋዮች ደረጃ

ለንግድ ሥራ ትርፍ ግብር አላማ ግብር ከፋዮችን በሶስት ደረጃ ይመደባሉ፡፡ እነሱም ደረጃ 'ሀ' ደረጃ 'ለ' እና ደረጃ 'ሐ' ናቸው፡፡ ደረጃ 'ሀ ሥር ከሚመደቡት ድርጅቶችና ሰዎች ውስጥ አንዱ በኢትዮጵያ ወይም በውጭ አገር ህግ መሰረት የተቋቋመ የህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ሲሆን ሁለተኛው የአመቱ ጠቅላላው ገቢው አምስት መቶ ሺ ብር የሆነ ወይም ከዚያ ብልጫ ያለው ገቢ የሚያገኝ ማናቸውም ንግድ ሥራ ነው፡፡ ደረጃ ለ ደግሞ በደረጃ ሀ ሥር የማይሸፈን የአመት ጠቅላላው ገቢው ከአንድ መቶ ሺ ብር በላይ የሆነ ማናቸውም የንግድ ሥራ ነው፡፡ ደረጃ 'ሐ' ደግሞ የአመት ጠቅላላ ገቢው እስከ አንድ መቶ ሺ ብር የሚደርስ ማናቸውንም የንግድ ሥራ የሚያጠቃልል ነው፡፡ ከኩባንያዎች በስተቀር የግብር ከፋዮች አመዳደብ አመታዊ ጠቅላላ ገቢን መሰረት ያደረገ ነው፡፡

## ሠ. ግዴታዎች

የግብር ሕግ በገቢ ግብር ከፋዮች ላይ የተለያዩ ግዴታዎችን ይጥላል፡፡ አንዱ ግዴታ ገቢን ማስታወቅ እና ግብር መክፈል ነው፡፡ በሕግ ገቢያቸውን እንዲያሳውቁ ግዴታ የተጣለባቸው የገቢ ግብር ከፋዮች ገቢያቸውን ለሚመለከተው አካል የማስታወቅ ግዴታ አለባቸው፡፡ ገቢን ማስታወቅ አላማው ግብር ከፋዮች ግዴታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ለማድረግ ነው፡፡ ስለዚህ አንድ ግብር ከፋይ ያገኘውን ገቢ ለሚመለከተው አካል ሲያስታውቅ ግብሩንም ይከፍላል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ አንድ ግብር ከፋይ የሚያገኘውን ገቢ በሐቀኝነትና በትክክል የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

ገቢን የማሳወቅ ግዴታ በሁሉም ገቢ ግብር ከፋዮች ላይ የተጣለ አይደለም፡፡ በገቢ ግብር አዋጅ ገቢያቸውን የማሳወቅ ግዴታ የተጣለባቸው የሰንጠረዥ 'ለ' እና 'ሐ' ግብር ከፋዮች በመጀመሪያ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ የደረጃ ሐ ግብር ከፋዮች ገቢን የማሳወቅ ግዴታ የለባቸውም፡፡ የሠንጠረዥ 'ለ' እና 'ሐ' ግብር ከፋዮች የግብር አስገቢው ባለስልጣን በሚያዘው ቅጽ መሰረት ገቢያቸውን የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው፡፡ ገቢያቸውንም መቼ ማሳወቅ እንዳለባቸው በአዋጅ ተመልክቷል፡፡

ሁለተኛው የንግድ ሥራ ትርፍ ግብር ከፋዮች ግዴታ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ነው፡፡ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለባቸው ደግሞ የደረጃ ሀ እና ለ ግብር ከፋዮች ሲሆኑ የደረጃ ሐ ግብር ከፋዮች ግን የሒሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ የለባቸውም፡፡ የደረጃ ሀ እና ደረጃ ለ ግብር ከፋዮች ከሒሳብ መዝገባቸው ጋር የገቢ ማስታወቂያ ቅጽ ሞልተው ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የሂሳብ መዝገብና ሰነዶችን የመያዝ ግዴታ ያለባቸው ግብር ከፋዮች የሚይዙት መዝገብ የሚከተሉትን መረጃዎች አሟልቶ መያዝ አለበት፤

- ቋሚ ንብረቶችን የተገዙበትን ቀን የተገዙበትን ዋጋ እና አሁን ያላቸውን ዋጋ የሚያሳይ የቋሚ ንብረት መዝገብ ጨምሮ የንግድ ስራውን ሀብትና ዕዳ የሚያሳይ ሰነድ፣
- ከንግድ ስራው እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ በየቀኑ የተገኘውን ገቢ እና የተደረገውን ወጪ በተለይ ከገቢና ወጪው ምክንያት ጋር በማያያዝ፣
- ከንግድ ስራው ጋር በተያያዘ የተገዙ እና የተሸጡ ዕዎችንና አገልግሎቶች፤ይህም የተሸጣውን ዕቃና የተሰጠውን አገልግሎት በመለየት፤ ዕቃውን የገዙ ወይም የሸጡ ወይም አገልግሎቱን የሰጡ ሰዎችን ስም፣ የግብር አስገቢው ባለስልጣን ለይቶ እንዲያውቃቸው በሚያስችል አኳኋን፣የሻጩን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የያዙ አስቀድሞ ቁጥር የተሰጣቸው ደረሰኞች በመጠቀም፣
- በመጋዘን የተከማቹ የንግድ ዕቃዎችን ዓይነት፣ ብዛት እና ለዕቃዎቹ ተደረገውን ወጪ እንዲሁም ዕቃዎቹ የተገመቱበትን ዘዴ ጨምሮ በሒሳብ ዘመኑ መጨረሻ በእጅ ያሉትን ዕቃዎች የሚያሳይ የሰነድ መረጃ
- የሚፈለገው ግብር ለመወሰን የሚያስችሉ ማናቸውም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች፣

ግብር ከፋዩ ከላይ የተዘረዘሩትን የሂሳብ መዝገቦችና ሰነዶች፣ የያዙት ሂሳብ አግባብነት ካለው የግብር ዘመን አንስቶ ለአስር ዓመታት ማቆየት አለበት፡፡ በተጨማሪም የሒሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ የተጣለባቸው ግብር ከፋዮች የሚጠቀሙባቸውን ደረሰኞች ከማሳተማቸው በፊት የደረሰኞችን አይነትና ብዛት ከግብር አስገቢው ባለስልጣን ዘንድ የማስመዝገብ ግዴታ አለባቸው፡፡

**ረ. አወሳሰን**

የንግድ ሥራ ትርፍ ታክስ አወሳሰን ሥረዓት እንደ ግብር ከፋዮች ደረጃ አመዳደብ እና በገቢ ግብር ሰንጠረዥ የተለያየ ቢሆንም በአጠቃላይ የገቢ ግብር በሶስት መንገድ ሊወሰን ይችላል፡፡

አንደኛው መንገድ ግብርን በመረጃ መወሰን ነው፡፡ በመርህ ደረጃ ገቢያቸውን ማስታወቅ ግዴታ ያለባቸው ግብር ከፋዮች እና የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ የተጣለባቸው ግብር ከፋዮች ግብር አወሳሰን የገቢ ግብር ማስታወቂያንና የሒሳብ መዝገቡን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ሰንጠረዥ 'ለ' እና 'ሐ' ገቢ ግብር የሚመለከታቸው ገቢ ግብር ከፋይ እና የደረጃ 'ሀ' እና 'ለ' ግብር ከፋዮች በገቢው ማስታወቂያ መሰረት ከተጣለው ግብር ላይ በአዋጅ ተቀናሽ መደረግ ያለባቸው ሂሳቦች ከተቀነሱ ወይም መካካስ ያለባቸው ሂሳቦች እንዲካካሱ ከተደረጉ በኃላ ከገቢ ማስታወቂያው ጋር የሚፈለግባቸውን ግብር በአንድነት ለግብር አስገቢው ባለስልጣን ገቢ ማድረግ አለባቸው፡፡ በዚህ መልኩ በገቢ ማስታወቂው ላይ የተመለከተው ግብር በአመቱ መከፈል የሚገባውን ግብር ለግብር አስገቢው ባለስልጣን የተወሰነ ግብር ሆኖ ይቆጠራል፡፡

ሆኖም ግን በዚህ መልኩ በገቢ ማስታወቂያው መሰረት ተሰልቶ የሚከፈለው ግብር የመጨረሻ አይደለም፡፡ ግብር አስገቢው ባለስልጣን በዚህ መልኩ ተሰልቶ የቀረበውን ወይም የተከፈለውን ግብር የማጣራት ሥልጣን አለው፡፡ በማጣራቱም ሒደት ግብሩ ስህተት ወይም ያልተካተተ ገቢ ያለ መሆኑ የተረጋገጠ ከሆነ ባለስልጣኑ የቀረበውን ግብር ወይም ማስታወቂያ አሰተካክሎ ግብሩን ይወስናል፡፡ የተስተካከለው ወይም የተሻሻለው የግብር ውሳኔ ማስታወቂያው ለግብር ከፋዩ መሰጠት አለበት፡፡ የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ ይዘትና ለግብር ከፋዩ የሚደርስበት ሁኔታ በአዋጅ ተመልክቷል፡፡

ሁለተኛው መንገድ ግብርን በቁርጥ መወሰን ነው፡፡ የቁርጥ ግብር አወሳሰን የሚመለከተው የደረጃ 'ሐ' ግብር ከፋዮችን ነው፡፡ የደረጃ 'ሐ' ግብር ከፋዮ በንግድ ዘርፍ የሚከፈል የመደበኛ ቁርጥ ግብር መጠንም በገቢ ግብር ደንብ ጋር በተያያዘ ሰንጠረዥ ተዘርዝሯል፡፡ የቁርጥ ግብር መጠንም የንግድ ሥራ አይነት፣ የንግድ ሥራ ስፋት፣ የንግድ ሥራ በሚያገኝበት ቦታ ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው፡፡ በሌላ በኩል የደረጃ 'ሐ' ግብር ከፋይ ተቀባይነት ያለው የሒሳብ መዝገብ ካቀረበ ግብሩን በሒሳብ መዝገብ መሰረት ሊከፍል ይችላል፡፡

ሶስተኛው መንገድ ግብርን በግምት መወሰን ነው፡፡ አንድ ግብር ከፋይ መክፈል ያለበት ግብር በግምት ሊወሰን የሚችለው፡-

- ግብር ከፋዩ ምንም አይነት የሂሳብ መዝገብና ሰነድ ያልያዘ ከሆነ ወይም
- የሂሳብ እና ሠነዱን የግብር አስገቢው ባለስልጣን ያልተቀበለው ከሆነ ወይም
- ግብር ከፋዩ በሕግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ገቢውን ያላሳወቀ እንደሆነ ነው፡፡

ከእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ ሲያጋጥም ግብር አስገቢው ባለስልጣን የግብር ከፋዩን ገቢ ግብር በግምት ሊወሰን ይችላል፡፡

## ሸ. ከተከፋይ ሒሳብ ግብርን ቀንሶ የማስቀረት ሥረዓት

የንግድ ሥራ ትርፍ ታክስን በተመለከተ የገቢ ግብር አዋጅ እና የገቢ ግብር ደንብ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብርን ቀንሶ የማስቀረት ሥረዓት ተግባራዊ የሚሆንበት ሁለት ሁኔታዎች ደንግጓዋል፡፡ አንደኛው ለንግድ ወደ አገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የሚከፈለውን የንግድ ትርፍ ግብር የሚመለከት ነው፡፡ ወደ አገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የሚሰበሰው የንግድ ትርፍ ግብር አስመጪው ለዕቃው በከፈለው ዋጋ፣የመድን አረቦን እና የመጓጓዣ ወጪ (ሲ.አይ ኤፍ) ላይ የሚታሰብ ሶስት በመቶ ነው፡፡ በዚህ አይነት የሚሰበሰበው ግብር ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ቀንሶ እንደቀረ ግብር ተቆጥሮ ግብር ከፋዩ በአመቱ መጨረሻ መክፈል ከሚገባው የግብር መጠን ላይ ይታሰብለታል፡፡

ሁለተኛው በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅቶች፣ የመንግስት መ/ቤቶች፣ ለትርፍ ያልተቋቋሙ የግል ድርጅቶች እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተለያዩ አገልግሎቶችና ዕቃዎች ለሚያቀርቡ ግብር ከፋዮች ከሚፈጽሙት ክፍያ ላይ ሁለት በመቶ የንግድ ግብር ቀንሰው የማስቀረት ግዴታ አለባቸው፡፡ ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግ ሥርዓት የሚመለከታቸው አገልግሎቶች፡-

- የምክር አገልግሎት
- ዲዛይን ሥራዎች፣ ጽሑፎች፣ ትምህርት ገላጻዎች እና መረጃ ማሰራጨት ሥራዎች

- ለጠበቆች፣ ለሂሳብ ባለሙያዎች፣ ለኦዲተሮች እና ሌሎች ተመሳሳይ አገልግሎቶች.
- ሸያጭ ለሚያከናውኑ ሰራተኞች፣ የኪነጥበብና የስፖርት ባለሙያዎች፣ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ሻጮችን ጨምሮ ከማንኛውም ደላላ እና ሌሎች የኮሚሽን ወኪሎች
- በቴሌቭዥንና በሬድዮ ከሚተላላፈ ማስታወቂያዎች እና ለመዝናኛ ዝግጅቶች
- ለስራ ተቋራጮች ከሚከፈል የአገልግሎት ዋጋ
- ከሳይንስ ግኝቶች እና የፈጠራ ውጤቶች ባለመብትነት
- ኮፒውተሮችን ጨምሮ ከተለያዩ ማሽነሪዎች ሕንፃዎችና ሌሎች ዕቃዎች ኪራይ
- ከጥገና አገልግሎት
- ከልብስ ስፌት
- ከሕትመት
- ከመድን ዋስትና

እነዚህን አገልግሎቶች ለሚያቀርቡ ታክስ ከፋዮች ክፍያ የሚፈፀም አካል በአንድ ጊዜ ግዥ ወይም በአንድ አገልግሎት ውል ከብር አምስት መቶ ብር በላይ በሚፈፀም ክፍያ ሁለት ፐርሰንት የንግድ ትርፍ ታክስ ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ አለበት፡፡

ታክስን ቀንሶ ገቢ የማድረግ ሐላፊነት ያለባቸው አካላት በገቢ ግብር ደንብ ተጠቅሰዋል፡፡ እነሱም፡- በሕግ ሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅቶች (አክስዮን ማህበሮች፤ ሐላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፣ የመንግስት ልማት ድርጅቶች)፤ የመንግስት መ/ቤቶች፤ ለትርፍ ያልተቋቋሙ የግል ድርጅቶች እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ናቸው፡፡ የግብር አስገቢው ባለስልጣንም ከተከፋይ ሒሳብ ላይ ግብር ቀንሶ የማስቀረት ሐላፊነት ለተሰጣቸው ሰዎች የመታወቂያ ወረቀት መስጠት አለበት፡፡

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. የሠንጠረዥ ለ እና ሐ በተመለከተ ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለማስላት በህጉ ተቀናሽ መደረግ ያለባቸው ወጪዎች መቀነስ ይኖርባቸዋል፡፡ የዚህ አላማ ምንድነው?
2. ግብር ከፋዮችን በደረጃ መከፋፈሉ ጠቀሜታው ምንድነው?
3. በሠንጠረዣዊ ሥርዓት እና ግብር ከፋዮች ደረጃ አመዳደብ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?
4. ከተከፋይ ሒሳብ ላይ ታክስን ቀንሶ የማስቀረት ሥርዓት ዋና አለማ ምንድነው?

**2.2.1.5.4. የሠንጠረዥ 'መ' ገቢ ግብር**

**ሀ. በሠንጠረዡ የታቀፉ ገቢዎች**

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ሠንጠረዥ 'መ' ሌሎች ገቢዎች የሚመለከት ነው፡፡ ይሔም በሶስቱ ሰንጠረዥ ሥር የማይወድቁ ገቢዎች ላይ በታክስ ባለስልጣን የሚጣሉ ታክሶችን የሚመለከት ነው፡፡ በገቢ ግብር አዋጅ መሰረት ሰባት የገቢ አይነቶች በዚህ ሰንጠረዥ ሥር እንዲታቀፉ ተደርገዋል፡፡

አንደኛው የፈጠራ መብትን ማከራየት የሚገኝ ገቢ ሲሆን የግብር ማስከፈያው መጠንም አምስት በመቶ ነው፡፡

ሁለተኛው የቴክኒክ አገልግሎት በመስጠት የሚገኝ ገቢ ነው፡፡ በአዋጅ የቴክኒክ አገልግሎት ማለት ማናቸውም የባለሙያ ምክር ወይም ቴክኖሎጂ አገልግሎት ነው (አንቀጽ 32 (2))፡፡ በኢትዮጵያ ነዋሪ ለሆኑ ሰዎች ከኢትዮጵያ ውጪ ለተሰጠ የቴክኒክ አገልግሎት የተፈፀመ ክፍያ አስር በመቶ የገቢ ግብር ይከፈልበታል፡፡

ሶስተኛው ከዕድል ሙከራ የሚገኝ ገቢ ነው፡፡ በዕድል ሙከራ ውድድር አሸናፊ በመሆን (ለምሳሌ ከሎተሪ ቶንቦላ ወይም ከሌሎች ተመሳሳይ እንቅስቃሴዎች) ገቢ ያገኘ ሰው ገቢ ግብር መክፈል ግዴታ አለበት፡፡ የግብሩ ማስከፈያው መጠን ከመቶ ብር በላይ በሆነው ገቢ ላይ አስራ አምስት በመቶ ነው፡፡ ይህም ማለት እስከ መቶ ብር የሆነ የዕድል ሙከራ ገቢ የገቢ ግብር ነፃ ነው፡፡ (አንቀጽ 33)

አራተኛው የአክስዮን ትርፍ ድርሻ ነው። የአክስዮን ማህበር ካከፋፈለው አክስዮን ድርሻ ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከሚያከፋፍላቸው ትርፍ ገቢ የሚያገኝ ሰው ባገኘው ገቢ ላይ አሥር በመቶ ግብር ይከፍላል። (አንቀጽ 34)

አምስተኛው ከንብረት ኪራይ የሚገኘው ገቢ በሠንጠረዥ 'መ' ሥር የሚሸፈን ሌላዉ ገቢ ነው። በገቢ ግብር ደንብ ከንብረት የሚገኝ ገቢ ማለት በንግድ ሥራ በመደበኛነት ያልተሰማራ ሰው የሚንቀሳቀሱ ወይም የማይንቀሰቀሱ ንብረቶችን አልፎ አልፎ በመከራየት የሚያገኘው ጠቅላላ ገቢ ነው። (አንቀጽ 17) ይህ ከንብረት ኪራይ የሚገኝ ገቢ በሰንጠረዥ 'ሐ' ገቢ ግብር የተለየ ነው። የገቢ ግብሩም የሚከፈለው ከአጠቃላይ አመታዊ ገቢ ላይ ነው። የግብር ማስከፈያው መጠንም አስራ አምስት በመቶ ነው። (አንቀጽ 35)

ስድስተኛው በተቀማጭ ገንዘብ ላይ ሚከፈል ወለድ ገቢ ነው። የግብር ማስከፈያው መጠንም አምስት በመቶ ነው። (አንቀጽ 36)

በዚህ ሰንጠረዥ ሥር የሚወድቀው የመጨረሻው ገቢ በተወሰኑ የካፒታል ንብረቶችን በማስተላለፍ የሚገኝ ጥቅም ነው።(አንቀጽ 37) የካፒታል ንብረቶችን በማስተላለፍ የሚገኝ ጥቅም ቀደም ሲል በአዋጅ ቁጥር 108/1994 የሚተዳደር ነበር። ይህ አዋጅ በዚህ ገቢ ግብር አዋጅ ተሽሯል። በአጠቃላይ ይህ ታክስ ለንግድ፣ ለፋብሪካ፣ ለቢሮ ተያዙ ሕንፃዎች እና የኩባንያ አክስዮንን በስጦታ ወይም በሽያጭ በማስተላለፉ የሚገኝ ጥቅም የሚመለከት ነው። ይህ አይነቱ ማስተላለፍ ለመኖሪያነት የማያገለግሉ ሕንፃዎችና የኩባንያ አክስዮን ጋር የተገናኙ መሆን አለበት። በተጨማሪም በማስተላለፍ የተገኘ ጥቅም መኖር አለበት። በሌላ በኩል አዋጅ በስተቀሮችን ዘርዝሯል። (አንቀጽ 24)

በግል መኖሪያነት የተያዘ ቤት በማስተላለፍ የሚገኝ ጥቅም ከገቢ ግብር ነፃ ነው። ነገር ግን የግል መኖሪያ ቤት በማስተላለፍ የሚገኘው ጥቅም ከግብር ነፃ ሊሆን የሚችለው መኖሪያ ቤቱ ከተላለፈበት ቀን በፊት ባለው የሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ለመኖሪያነት ያላገለገለ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው። (ደንብ አንቀጽ 16)

የግብር ማስከፈያው መጠንም ለንግድ፣ ለፋብሪካ ለቢሮ የተያዙ ሕንጻዎች ላይ አስራ አምስት በመቶ ሲሆን የኩባንያዎች አክስዩን ላይ ግን ሰላሳ በመቶ ነው፡፡ (አዋጅ አንቀጽ 37 (1)).

በመጨረሻ ከዕድል ሙከራ፣ የአክስዩን ትርፍ ድርሻ፣ ከንብረት ኪራይ እና በተቀማጭ ገንዘብ ላይ የሚከፈል የወለድ ገቢ በተመለከተ ታክሱ የመጨረሻ እንደሆነ በአዋጁ ተመልክቷል፡፡

**ለ. ግዴታዎች**

በሠንጠረዥ 'መ' ገቢ ግብርን በተመለከተ በህጉ የተጣለው ግዴታ ግብሩን ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ ነው፡፡ ግዴታው የተጣለው ገቢውን ለባለመብቱ በሚከፍል ሰው ላይ ነው፡፡ (አንቀጽ 54) በዚሁ መሰረት ግብሩን ቀንሶ ገቢ የማድረግ ሃላፊነት የተጣለበት ሰው ግብር የሚከፍልበትን ገቢ ለባለመብቱ ሲከፍል ተገቢውን የግብር መጠን ከተከፋዩ ሂሳብ ላይ ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ አለበት፡፡ ከፋዩ ከተከፋዩ ገቢ ላይ ቀንሶ ማስቀረት ካለበት ሌላ ማናቸውም ግዴታ ቀዳሚነት አለው፡፡ ከፋዩ ቀንሶ ያስቀረውንም ግብር ከእያንዳንዱ ወር መጨረሻ አንስቶ ባሉት አስራ አምስት ቀናት ውስጥ ለግብር አስገቢው ባለስልጣን ገቢ የማድረግ አለበት፡፡ እንዲሁም ቀንሶ ያስቀረውንም ግብር ገቢ በሚያደርግት ጊዜ በወሩ ውስጥ ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ያገኙትን ግብር ከፋዮች ዝርዝር የሚያሳይ መረጃ አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ በዚህ መልኩ የሚቀርበው መግለጫ የግብር አስገቢው ባለስልጣን በሚወስነው ቅርጽና አኳኃን የሚቀርብ ነው፡፡

በተጨማሪም ከፋዩ ግብሩን ቀንሶ ቀሪ ማድረጉን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ለግብር ከፋዩ መስጠት አለበት፡፡ የምስክር ወረቀቱ ይዘት በአዋጁ የተመለከተ ሲሆን የምስከር ወረቀቱም በሠንጠረዥ መ መሰረት ግብር በሚከፈልበት ገቢ ላይ ተቀንሶ ለቀረው ግብር ማስረጃ ሆኖ የሚያገለግል ነው፡፡

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. አንድ ግብር ከፋይ በአንድ ሠንጠረዥ ሥር ግብር የሚከፈልበት ገቢ ከተለያየ የገቢ ምንጭ የሚያገኝ ከሆነ ግብሩ የሚወሰነው ገቢውን በማጠቃለል ነው፡፡ ለምን?

2. በገቢ ግብር አዋጅ እንደተመለከተው በተቀማጭ ገንዘብ ላይ የሚከፈል ወለድ ገቢ እና የካፒታል ንብረቶችን በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ ፌዴራል መንግስት የገቢ ታክስ የመጣልና የመሰብሰብ ሥልጣን አለው፡፡ የዚህ ሥልጣን ሕገመንግስታዊ መሰረቱ ምንድነው?
3. ከዕድል ሙከራ፤ አክስዮን ትርፍ ድርሻ፣ ከንብረት ኪራይ እና ተቀማጭ ገንዘብ ላይ የሚከፈል የወለድ ገቢ በተመለከተ ታክሱ የመጨረሻ ነው፡፡ ይህ ምን ማለት ነው?
4. በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 14 እና 35 መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው? የመኖሪያ ቤትን አልፎ አልፎ በማከራት በንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ግብሩን የሚከፍሉት በአንቀጽ 14 ነው ወይስ በአንቀጽ 35? አዳራሽ እና ሌሎች ተቋሞችን አልፎ አልፎ በማከራየት ገቢ የሚያገኙ ሰዎች ግብርመክፈል ያለባቸው በአንቀጽ 14 ነው ወይስ በአንቀጽ 35 ነው?
5. ከሠንጠረዥ መ አንፃር ታክስ የሚከፈልበት ገቢ ማለት ምን ማለት ነው? የሠንጠረዥ መ ገቢ ታክስ በሌሎች ሠንጠረዥ ሥር ከተመለከቱት ታክሶች ጋር ሲነጻጸር ምን ለየት ያለ ባህሪ አሏቸው ብላችው ታስባላችሁ?

### 2.2.1.1.6. የፍትሐብሔር ሐላፊነት ሊያስከትሉ የሚችሉ የገቢ ግብር ግዴታዎች

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የገቢ ግብር መክፈል ግዴታ ያለበት ግብር ከፋይ የተለያዩ ግዴታዎች ተጥለውበታል፡፡ ከተጠቀሱት ግዴታዎች በተጨማሪ ህጉ በታክስ ከፋዩ ላይ ሌሎች ግዴታዎች ጥሏል፡፡ አንዱ ግዴታም መለያ ቁጥር መያዝ ነው፡፡ የገቢ ግብር አዋጅ ማንኛውም ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የመያዝ ግዴታ እዳለበት ይደነግጋል፡፡ (አንቀጽ 43(ሀ)) አንድ ግብር ከፋይም ከአንድ የበለጠ ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እንድይዝ አይፈቀድለትም፡፡

ሌላው የአድራሻ ለውጥና ንግድ ስራን ማቋረጥ የማስታወቅ ግዴታ ነው፡፡ ማንኛውም ግብር ከፋይ የንግድ አድራሻውን የሚለውጥ ከሆነ እንዲሁም ንግድ ሥራውን የሚያቋርጥ ከሆነ

የአድራሻ ለውጥ ካረገበት ወይም ንግድ ሥራውን ካቋረጠበት ቀን ጀምሮ በሰለሳ ቀናት ውስጥ ለግብር አስገቢው ባለስልጣን ማስታወቅ ግዴታ አለበት፡፡

እነዚህ ግዴታዎችን አለመወጣት የፍትሐብሔር ሐላፊነትን ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡ ገቢ ግብር ግዴታን አለመወጣት የሚያስከትለው የፍትሐብሔር ሐላፊነት አስተዳደራዊ መቀጮን የመክፈል ግዴታ ነው፡፡ በገቢ ግብር አዋጅ መሰረት አስተዳደራዊ መቀጮ የመክፈል ሐላፊነት ሊያስከትሉ የሚችሉ ግዴታዎች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ፡-

- ገቢን ያለማሳወቅ ወይም ዘግይቶ ማሳወቅ
- ግብርን ቀንሶ ማሳወቅ
- ግብርን አዘግይቶ መክፈል
- ተገቢ የሒሳብ መዝገብ፣ ሒሳብ ሰነድ እና መግለጫ አለመያዝ
- የመለያ ቁጥር አለመያዝ
- ታክስን ቀንሶ አለመክፈል ናቸው፡፡

ማንኛውም ግብር ከፋይ የሚፈለግበትን ግብር በወቅቱ ያልከፈለ ከሆነ ግብሩን መክፈል ከነበረበት ጊዜ ጅምሮ እስከተከፈለበት ቀን ድረስ ባልተከፈለው የግብር መጠን ላይ ወለድ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡ (አንቀጽ 75) እንዲሁም አንድ ግብር ከፋይ ለሁለት ተከታታይ አመታት ተገቢውን የሂሳብ መዝገብ ካልያዘ ከገንዘብ መቀጮ በተጨማሪ የንግድ ስራ ፈቃድ ሊታገድበት ወይም ሊሰረዝበት ይችላል፡፡

አስተዳደራዊ መቀጮ በግብር ከፋይ ላይ ብቻ ሳይሆን ከተከፋይ ሂሳብ ግብርን ቀንሶ ገቢ የማድረግ ሐላፊነት ባለበት ኣካል ላይ ሊጣል ይችላል፡፡ በዚሁ መሰረት ግብርን ቀንሶ ገቢ ማድረግ ግዴታ ያለበት ሰው ቀንሶ ገቢ ያላደረገውን የግብር መጠን ለግብር አስገቢው ባለስልጣን ገቢ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡ ሆኖም ግን በዚህ አይነት የከፈለውን ሒሳብ ከግብር ከፋዩ መልሶ የማግኘት መብት አለው፡፡ በተጨማሪም ከተከፋይ ሒሳብ ላይ ግብርን ቀንሶ ገቢ የማድረግ ሐላፊነት ያለበት ሰው ለእያንዳንዱ ተገቢውን ግብር ቀንሶ ገቢ ሳያደርግ ለፈጸመው ክፍያ የገንዘብ መቀጮ ይከፍላል፡፡ መቀጮውንም የሚከፍለው ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብርን ቀንሶ ገቢ ያለመደረጉን ያወቀ ወይም ማወቅ ያለበት ሥራ አስኪያጅ ወይም ይህን ሥረአት የመከታተል ወይም የመቆጣጠር ኃላፊነት ያለበት ሆኖ ክትትሉን ወይም ቁጥጥሩን በተገቢው

መንገድ ባለማከናውኑ ግብሩ ተቀንሶ ገቢ ላለመደረጉ ምክንያት የሆነ የሂሳብ ኃላፊ ወይም ማንኛውም ሌላ ኃላፊ ነው፡፡ (አንቀጽ 90)

የግብሩ አይነት ከተከፋይ ሒሳብ ግብርን ቀንሶ ማስቀረት ሥረአት የሚሸፈን ከሆነ ግብር ከፋዩ የግብር መለያ ቁጥሩን ግብርን ቀንሶ ለሚያስቀረው ሰው የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡ የግብር ከፋዩ መለያ ቁጥሩን ያላቀረበ እንደሆነ ግብሩን ቀንሶ የሚያሰቀረው ሰው ከተከፋዩ ሂሳብ 30% ቀንሶ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡ በተጨማሪም ይህን ግዴታ ያለተወጣ ግብር ከፋይ የገንዘብ መቀጮ ይጣልበታል፡፡ (አንቀጽ 91)

የገቢ ግብር ህግ የሚጥለውን ግዴታዎች ባለመወጣት የሚጣለው የገንዘብ መቀጮ መጠንና ሥሌት እንደ ግዴታው አይነት የተለያየ ነው፡፡ (የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 86 — 91 ተመልከቱ)

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. በደረጃ ሀ፣ ለ እና ሐ ግብር ከፋዮች ግዴታ መካከል ያለው ተመሳሳይነት እና ልዩነት ምንድነው?
2. አንድ ታክስ ከፋይ በገቢ ግብር አዋጅና ገቢ ግብር ደንብ መሰረት ያለው መብት፤ በሌላ በኩል ግብር አስገቢው ባለስልጣን ያለበት ግዴታ ዋና ዋናዎቹን ጥቀሱ፡፡
3. አንድ የገቢ ታክስ ከፋይ የንግድ ሥራውን ማቋረጡን ለግብር አስገቢው ባለስልጣን ማሳወቅና አለማሳወቅ ጉዳትና ጥቅሙ ምንድነው?
4. በሐገራችን በመካሔድ ላይ ባለው የታክስ ሥረዓት ማሻሻያ ፕሮግራም ውስጥ አንዱ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ለታክስ ከፋይ የመለያ ቁጥር መስጠት እና ሁሉም ታክስ ከፋይ የመለያ ቁጥር እንዲይዝ ማድረግ ነው፡፡ ይህ ምን ጠቀሜታ አለው?

### 2.2.2. ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶች

በኢፌድሪ መንግስት ከሚጣሉ እና ከሚሰበሰቡ  የታክስ  አይነቶች ውስጥ ተጨማሪ እሴት ታክስ፤ ተርን ኦቨር ታክስ፤ ኤክሳይስ ታክስ፤ የጉምሩክ ቀረጥ እና ሱር ታክስ ቀጥተኛ ካልሆኑ የታክስ አይነቶች ጎራ የሚመደቡ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ተጨማሪ እሴት ታክስ፤ ተርን ኦቨር ታክስ እና ኤክሳይስ ታክስ ቀጥለው ይቀርባሉ፡፡ መጀመሪያ ተጨማሪ እሴት ታክስ፡፡

### 2.2.2.1. ተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT)

#### ሀ. ምንነት

ተጨማሪ እሴት ታክስ ከሽያጭ ታክስ ጎራ የሚመደብ የታክስ አይነት ነው፡፡ Carl S. Shoup ተጨማሪ እሴት ታክስ " ---- is a consumption/expenditure tax charged on the services by importers, manufactures and traders at each stage of the production and distribution process" በማለት ይፈታዋል፡፡ ከዚህም መረዳት እንደሚቻለው ተጨማሪ እሴት ታክስ፡-

- **የፍጆታ ታክስ ነው፡፡**  ተጨማሪ እሴት ታክስ  አንድ ሰው በሚያገኘው ገቢ ላይ የሚጣል ሳይሆን በእቃ ሽያጭ እና አገልግሎት ላይ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ተጨማሪ እሴት ታክስ በሸማቹ የፍጆታ ወጪ ላይ የሚጣል ታክስ ነው፡፡ ተጨማሪ እሴት ታክስ ቀጥተኛ ካልሆኑ የታክስ አይነቶች የሚመደብ በመሆኑ ታክሱን የመክፈል  የመጨረሻ ሸክም የሚያርፈው በሸማቹ ላይ ነው፡፡
- **ተጨማሪ ዋጋ፡-** ተጨማሪ እሴት ታክስ የሚጣለው በሚሸጠው የዕቃ ወይም በሚሰጠው አገልግሎት አጠቃላይ ዋጋ ላይ ሳይሆን በንግድ ልውውጥ ሒደት በሚደረገው ተጨማሪ ዋጋ ላይ ነው፡፡
- **በእያንዳንዱ ደረጃ፡-** ተጨማሪ እሴት የመክፈል ሸክም በአንድ ደረጃ ብቻ የተገደበ ሳይሆን በተለያዩ ደረጃዎች የተከፋፈለ ነው፡፡ ማለትም እቃዎችን ወደ ሐገር ውስጥ ሲገቡ፤ ሲመረቱ እና ሲሸጡ ተጨማሪ እሴት ታክስ ሊጣል ይችላል፡፡ ግዴታውም ከአስመጭው እና አምራቹ ጀምሮ እስከ ችርቻሮ ሻጩ የሚሄድ ነው ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ተጨማሪ እሴት ታክስ በተለያዩ ደረጃዎች የሚሰበሰብ ታክስ በመሆኑ መሰረተ ሰፊ ታክስ  ነው፡፡

እነዚህን ነጥቦች የበለጠ ግልጽ ለማድረግ የሚከተለውን ምሳሌ መመለከቱ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ አንድ እቃ አምራች በብር 200,000 የጥሬ ዕቃ ግዥ ቢፈጽምና ዕቃውን ለጅምላ ሻጥ በብር 250,000 ቢሸጥ፤ ጅምላ ሻጩ ደግሞ እቃውን ለችርቻሮ ሻጭ በብር 280,000 ቢሸጥ፤ እንዲሁም ችርቻሮ ሻጩ እቃውን ለሸማቹ በብር 300,000 ቢሸጥ እና የታክስ ማስከፈያው መጠን 15% ቢሆን የተጨማሪ እሴት ታክስ ስሌቱ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

- ጥሬ ዕቃ አቅራቢው እቃውን ሲሸጥ የሚሰበስበው ተጨማሪ እሴት ታክስ 200,000 X15/100 = 30,000 ይህ ማለት ጥሬ ዕቃ ሻጩ ዕቃውን ለአምራቹ ሲሸጥ 30,000 ተጨማሪ እሴት ታክስ ሰብስቦ ለመንግስት ገቢ ያደረጋል ማለት ነው፡፡
- አምራቹ ዕቃውን ለጅምላ ሻጭ ሲሸጥ የሚሰበስበው ተጨማሪ እሴት ታክስ ደግሞ 250000 X15/100 = 37,500 ሲሆን ለታክስ አስገቢው ባለስልጣን የሚከፍለው ታክስ 37,500–30,000 = 7,500 ወይም በዚህ ደረጃ እሴቱ 250000–200000= 50000 X15/100 = 7,500 ይሆናል ማለት ነው፡፡
- ጅምላ ሻጩ እቃውን ለችርቻሮ ሻጩ ሲሸጥ የሚሰበስበው ተጨማሪ እሴት ታክስ ደግሞ 280000 X15/100 = 42000 ሲሆን ለታክስ አስገቢው ባለስልጣን የሚከፍለው ግን 42000–37,500 = 4,500 ወይም 280000–250000=30000 X15/100 = 4,500 ይሆናል ማለት ነው፡፡
- ችርቻሮ ሻጩ ደግሞ ለሸማቹ እቃውን በብር 300000 ሲሸጥ ተጨማሪ እሴት ታክስ 300000 X15/100 =45000 ሲሆን ችርቻሮ ሻጩ ለታክስ አስገቢው ባለስልጣን የሚከፍለው ግን 45000–42000 = 3,000 ብር ወይም 300000–280000=20000 X15/100= 3,000 ይሆናል ማለት ነው፡፡

ከላይ በተጠቀሰው መሰረት መንግስት፡

- ከጥሬ ዕቃ አቅራቢ ብር 30,000
- ከአምራቹ ብር 7,500
- ከጅምላ ሻጩ ብር 4,500
- ከችርቻሮ ሻጩ ብር 3,000

በአጠቃላይ ብር 45,000 ተጨማሪ እሴት ታክስ ይሰበስባል ማለት ነው፡፡ የታክሱን አጠቃላይ መጠን እቃው ለሸማቹ የተሸጠበትን ዋጋ በአስራ አምስት ፐርሰንት በማብዛት ማወቅ ይችላል፡፡ (30000 X15/100 = 45,000)

ተጨማሪ እሴት ታክስ በአንድ ደረጃ ብቻ የሚከፈል ሳይሆን በእያንዳንዱ ደረጃ የሚከፈል ታክስ መሆኑን ከዚህ ምሳሌ በቀላሉ መረዳት ይቻላል፡፡ ታክሱም በእያንዳንዱ ደረጃ ማለትም ከጥሬ እቃ አቅራቢ ጀምሮ እስከ ችርቻሮ ሻጩ የተከፋፈለ መሆኑን እንዲሁም በእያንዳንዱ ደረጃ ታክሱ የሚሰላው በእቃው አጠቃላይ ዋጋ ላይ ሳይሆን በተጨማሪ እሴቱ ወይም ዋጋ ላይ ብቻ መሆኑንም መረዳት ይቻላል፡፡

ተጨማሪ እሴት ታክስ በብዙ ሐገሮች ተግባራዊ መሆን ከጀመረ ውሎ አድሯል፡፡ በእኛ ሀገር ግን ተግባራዊ መሆን የጀመረውም በቅርብ ጊዜ ነው፡፡ (1994) ተጨማሪ እሴት ታክስ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 98 መሰረት በማደረግ በፌዴራል መንግሥት የሚጣል እና የሚሰበሰብ ታክስ ነው፡፡ ከ1994 በፊት በአዋጅ ቁጥር 68/85 (እንደተሻሻለው) የሚጣልና የሚሰበሰብ የሽያጭ ታክስ ነበር፡፡ ይህ ሽያጭ ታክስ በተጨማሪ እሴት ታክስ ተተክቷል፡፡ ስለዚህ ተጨማሪ እሴት ታክስ ለሐገራችን ኢኮኖሚ አዲስ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ተጨማሪ እሴት ታክስ የሚመለከቱ ሁለት ሕጎች አሉ፡፡ እነሱም፡- የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 እና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 79/1995 ናቸው፡፡

ሽያጭ ታክስን በተጨማሪ እሴት ታክስ መተካት ያስፈለገበት ምክንያት በአዋጁ መግቢያ ላይ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ አንዱ ምክንያት የሽያጭ ታክስ የሽያጭ እንቅስቃሴ በተከናወነ ቁጥር በሚፈጠረው ተጨማሪ እሴት ላይ ታክስ መሰብሰብ ስለማያስችል ነው፡፡ ሽያጭ ታክስ የሚሰበሰበው ብዙን ጊዜ በጅምላ ሽያጭ ወይም በችርቻሮ ሽያጭ ደረጃ ነው፡፡ ታክሱም የሚጣለው በዕቃው አጠቃላይ ዋጋ ላይ ነው፡፡ የሽያጭ ታክስ ከአምራቹ እስከ ችርቻሮ ሻጩ ድረስ በሚካሔደው የንግድ ልውውጥ ውስጥ በአንድ ደረጃ ብቻ የሚጣል በመሆኑ በየደረጃው በሚፈጠረው ተጨማሪ እሴት (ዋጋ) ላይ ታክስ መሰብሰብ አያስችልም፡፡ ተጨማሪ እሴት ታክስ ግን የመክፈል ሐላፊነት በተለያዩ ደረጃዎች የተከፋፈለ በመሆኑ የሽያጭ እንቅስቃሴ በተከናወነ

ቁጥር የሚፈጠረው ተጨማሪ እሴት (ዋጋ) ታክስን ለመሰብሰብ የሚያስችል ነው፡፡ ይህ ምን ማለት እንደሆነ ከላይ የቀረበውን ምሳሌ ተመልከቱ፡፡

ሁለተኛው ምክንያት አስተዳደራዊ አመቺነት ነው፡፡ ተጨማሪ እሴት ታክስ መክፈል ግዴታ በተለያዩ ታክስ ከፋዮች መካከል የተከፋፈለ በመሆኑ ታክሱን ላለመክፈል የሚደረገው ጥረት አነስተኛ ነው፡፡ (Lesser tax invasion) በሌላ አገላለፅ የተጨማሪ እሴት ታክስ አሰባሰብ ሥረዓት ታክስ ከፋዩ ታክሱን ላለመክፈል የሚደረገውን ተግባር ለመቆጣጠር በቀላሉ የሚያስችል ነው፡፡

ሶስተኛው ምክንያት ተጨማሪ እሴት ታክስ ቁጠባንና ኢንቨስትመትን የሚያበረታታ መሆኑ ነው፡፡ ለዚህ መሰረቱ ተጨማሪ እሴት ታክስ በካፒታል እቃዎች ላይ የሚጣል ታክስ ስላልሆነ ነው፡፡ ተጨማሪ እሴት ታክስ የሚጣለው በፍጆታ እቃዎችና አገልግሎቶች ላይ ነው፡፡ የካፒታል እቃዎችን ከተጨማሪ እሴት ታክስ ውጪ ማድረጉ ቁጠባንና ኢንቪስትመትን ያበረታታል፡፡

### ለ. የተጨማሪ እሴት ታክስ ቅድመ ሁኔታዎች

በሀገራችን ዕቃ አቅርቦት (Supply of Goods) ወይም አገልግሎት መስጠት (Rendition of service) በተጨማሪ እሴት ታክስ ለመታቀፉ መሟለት ያለባቸው ሁኔታዎች፡-

1. የዕቃ አቅርቦት እና/ወይም አገልግሎት ተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈል ግዴታ ባለበት ሰው መከናወን አለበት፡፡ ተጨማሪ እሴት ታክስ መክፈል ግዴታ በሌለበት ነጋዴ የተከናወነ የእቃ አቅርቦት በተጨማሪ እሴት ታክስ አይሸፈንም፡፡ ለተጨማሪ እሴት ታክስ አላማ ታክሱን መክፈል ግዴታ ያለባቸው፡
    - የተመዘገበ ወይም መመዝገብ ያለበት ሰው
    - ታክስ የሚከፍልባቸው ዕቃዎች ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገባ ሰው እነዚህን ዕቃዎች ወደ አገር ውስጥ ማስገባት በተመለከተ

- በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ሳይመዘገብ በኢትዮጵያ ውስጥ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ለተመዘገበ ታክስ ከፋይ (ደንበኛ) የአገልግሎት መስጠት ሥራ የሚያከናውኑ ናቸው፡፡

2. የዕቃ አቅርቦት እና/ወይም አገልግሎት በኢትዮጵያ ውስጥ የተከናወነ መሆን አለበት፡፡ ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ከኢትዮጵያ ጋር ግንኙነት ያለው ሥራ መሆን አለበት፡፡ ከኢትዮጵያ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው ሥራ ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ተደርጎ አይቆጠርም፡፡

3. አቅረቦቱ ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴን ለማከናወን በታክስ ከፋዩ መከናወን አለባቸው፡፡

4. አቅርቦቱ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ ነፃ ያልተደረጉ የዕቃ አቅርቦት እና/ ወይም አገልግሎት ወይም zero rated መሆን የለባቸውም፡፡

### ሐ. ምዝገባ

የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ሁለት የምዝገባ አይነት ይደነግጋል፡፡ አንደኛው በአዋጁ አንቀጽ 16 ስር የተመለከተው ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት አንድ ሰው በማናቸውም ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ከብር አምስት መቶ ሺ በላይ ከሆነ ወይም በማናቸውም የአስራ ሁለት ወራት ጊዜ መጀመሪያ ከዚህ አስራ ሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ታክስ ከፋዩ የሚያከናውነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ከብር አምስት መቶ ሺ በላይ ይሆናል ብሎ ለመገመት የሚያችል ተጨባጭ ምክንያት ያለ እንደሆነ የመመዝገብ ግዴታ አለበት፡፡ ይህም ለተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዝገብ ግዴታ በአመታዊ አጠቃላይ ወይም ጥቅል ገቢ (Gross income) ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

ሁለተኛው በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ምዝገባ ነው፡፡ ይህም ለተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዝገብ ግዴታ የሌለበት የንግድ ሥራ የሚያካሒድ ሰው ቢያንስ ሰባ አምስት ፐርሰንት የእቃ ማቅረብ እና አገልግሎት የመስጠት ሥራ የሚያከናውነው ለተመዘገቡ ሰዎች ከሆነ በፍላጎቱ የምዝገባ ማመልከቻውን ለባለስልጣኑ ማቅረብ ይችላል፡፡ (አዋጅ አንቀጽ 17)

በሌላው በኩል የተመዘገበ ሰው ምዝገባው ከሚፀናበት ቀን ጀምሮ ታክስ ከፋይ ሲሆን መመዝገብ ያለበት ሆኖ ያልተመዘገበ ሰው ደግሞ ለምዝገባ ማመልከቻ የማቅረብ ግዴታ ከሚጀምርበት ቀጥሎ ያለው የሒሳብ ጊዜ ከሚጀምርበት አንስቶ ታክስ ከፋይ እንደሚሆን በአዋጅ ተደንግጓል፡፡ (አንቀጽ 3)

### መ. እቃ አቅርቦት እና አገልግሎት መስጠት

ከላይ ጠቀስ እንደተደረገው ተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ሁለት ነገሮችን የሚመለከት ሊሆን ይችላል፡፡ እነሱም ዕቃ አቅርቦት (Supply of Goods) ወይም አገልግሎት መስጠትን (Rendition of service) ናቸው፡፡

በአዋጅ መሠረት ሽያጭ የዕቃ አቅርቦት ነው፡፡ እንደሚታወቀው ሽያጭ ከዕቃ መሸጥና የመግዛት ውል ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ሽያጭ የተለመደ የዕቃ አቅርቦት አይነት ነው፡፡ በአዋጁ መሰረት በዕቃ አቅርቦት ሽያጭን ብቻ የሚመለከት አይደለም፡፡ በዕቃው የመጠቀም ወይም የመጠቀም መብትን የሚያቋቁሙ ስምምነቶች ወይም ውሎችም እንደ ዕቃ አቅርቦት የሚወሰዱ ናቸው፡፡ እነዚህም ውስጥ የኪራይ ውል፣የዱቤ ውል፣የጭነት ውል፣የቻርተር ስምምነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ በዕቃው መጠቀም ወይም መጠቀም መብትም ከሾፌሮች፣ ለፓይለት፣ አጋዥ ሰራተኞች ጋር ወይም ብቻውን ሊሆን ይቻላል፡፡ በተጨማሪም የእንፋሎት ወይም የኤሌክትሪክ ኃይል፣ የጋዝ ወይም የውሃ አቅርቦት እንደ ዕቃ አቅርቦት የሚቆጠሩ ናቸው፡፡

አገልግሎት ማቅረብ ማለት ደግሞ ዕቃ ወይም ገንዘብ ያልሆነ ማናቸውም አቅርቦት ሲሆን ማናቸውንም መብት መስጠት፣ ማስተላለፍ፤ ማቋረጥ ወይም መልቀቅ የሚመለከት ነው፡፡ በተጨማሪም አንድን ተግባር ለመፈፀም የሚያስችሉ ነገሮችን ማመቻቸት አገልግሎት ማቅረብ ነው፡፡ ታክሱን የሚከፍለውም አቅርቦቱን የሚሰጠው የተመዘገበ ሰው ነው፡፡ (አዋጁ አንቀጽ 4)

### ሰ. ታክስ ስለመጣል እና ከታክስ ነጻ ስለሆኑ ግብይቶች

የእቃ አቅርቦትን ታክስ የሚጣልባቸውና ከታክስ ነጻ የሆኑ ብሎ መከፋፈል ይቻላል፡፡ ታክስ የሚጣልባቸው ግብይቶችን በሁለት መክፈል ይቻላል፡፡ አንደኛው አስራ አምስት ፐርሰንት ታክስ የሚጣልባቸው አቅርቦቶች (standard rated supplies) ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት አቅርቦቱ አስራ አምስት ፐርሰንት ታክስ የሚከፈልበት ከሆነ አቅራቢው ግዢ ሲያከናውን አስራ አምስት

ፐርሰንት ተጨማሪ እሴት ታክስ (input VAT) የሚከፍል ሲሆን ታክስ የሚጣልባቸውን እቃ በሚሸጥበት ወይም አቅርቦት በሚያከናውንበት ግዜ ደግሞ አስራ አምስት ፐርሰንት ታክስ (out put VAT) ይሰበስባል ማለት ነው፡፡ ለመንግስት የሚከፍለው ታክስ በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት ነው፡፡ ማለትም out put VAT ሲቀነስ input VAT ይሆናል ማለት ነው፡፡ ይሄን ቀደም ሲል ከቀረበው ምሳሌ መረዳት ይቻላል፡፡ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ መሰረት አስራ አምስት ፐርሰንት ተጨማሪ እሴትታክስ የሚከፈልባቸው አቅርቦቶች፡-

**በተመዘገቡ ሰዎች የሚከናወን ታክስ የሚከፈልበት ግብይት፡-** በመሰረቱ ተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገቡ ሰዎች በሚያከናውኑት ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ዋጋ ላይ 15% የማስከፈያ ልክ የሚጣል ነው፡፡ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ማለት በህጉ ከታክሱ ነፃ ከተደረጉ አቅርቦቶች በስተቀር ታክስ የሚከፈልበትን የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ በማከናወን ሂደት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚቀርብ ዕቃ ወይም አገልግሎት ነው፡፡በአንቀፅ 7(3) ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ደግሞ ምን ማለት እንደሆነ በአንቀጽ 6 ተደንግጓል፡፡

**ከታክስ ነፃ ከተደረጉ ዕቃዎች በስተቀር ወደ አገር የሚገቡ ዕቃዎች፡-** ከታክስ ነፃ ከተደረጉ ዕቃዎች በስተቀር ወደ አገር በሚገቡ ሌሎች ዕቃዎች ላይ ተጨማሪ እሴት ታክስ ይጣላል፡፡ ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የሚጣለው የተጨማሪ እሴት ታክስ መጣኔም ወይም እሴት በዕቃዎቹ ላይ የሚከፈለውን ቀረጥና ታክስ ሲደመር በጉምሩክ ህግ መሠረት የሚወሰነው የዕቃዎች ዋጋ ነው፡፡ እሴቱ ተጨማሪ እሴት ታክስንና ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የሚከፈለውን የገቢ ግብር አይጨምርም፡፡ (አንቀጽ 15 ተመልከቱ) ወደአገር ውስጥ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፍለው አስመጪው ነው፡፡ አስመጪውም ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገበ ሊሆን ይችላል፡፡

**ወደ አገር የሚገቡ አገልግሎቶች፡-** በአዋጅ መሠረት በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ እና ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገበ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ለተመዘገበ ሰው (ደንበኛ) አገልግሎት ከሰጠ በሰጠው አገልግሎት ላይ ተጨማሪ እሴት ታክስ ይጣላል (አንቀጽ 23)፡፡ የሚከፈለውንም ታክስ አገልግሎት ተቀባይ ከሚከፍለው ገንዘብ ላይ ቀንሶ ማስቀረት አለበት፡፡ ቀንሶ ያስቀረውን ታክስ ለግብር አስገቢው ባለስልጣን ገቢ ማድረግ አለበት፡

ሁለተኛው ዜሮ በመቶ የማስከፈያ ልክ ታክስ የሚከፈልባቸው (zero-rated supplies) ናቸው፡፡ ዜሮ በመቶ የማስከፈያ ልክ ታክስ የሚከፈልባቸው ግብይቶች የምንላቸው አቅራቢው ግዢ ሲያከናውን አስራ አምስት ፐርሰንት ተጨማሪ እሴት ታክስ (input VAT) የሚከፍል ሲሆን እቃውን በሚሸጥበት ወይም አቅርቦት በሚያከናውንበት ጊዜ የማስከፈያው መጠን ዜሮ ፐርሰንት ታክስ (out put VAT) ይሆናል ማለት ነው፡፡ ይህም እቃው በሚሸጥበት ወይም አቅርቦቱ በሚከናወንበት ጊዜ የሚሰበሰበው ተጨማሪ እሴት ታክስ አይኖርም ማለት ነው፡፡ እቃ ሻጩ በእቃው በግዢ ወቅት የከፈለውን ተጨማሪ እሴት ታክስ (out put VAT) ከታክስ ባለስልጣኑ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ይህ ተመላሽ ታክስ ይባላል፡፡ ዜሮ ፐርሰንት ታክስ የሆኑ ግብይቶችን የሚያከናውን ነጋዴ ተመላሽ ታክስ ለመጠየቅ ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

በአዋጁ መሰረት ዜሮ ፐርሰንት ተጨማሪ እሴት ታክስ የሚመለከታቸው ግብይቶች ውስጥ ወደ ውጭ የሚላኩ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች፣ በሚኒስተሮች ምክር ቤት ደንብ በሚወሰነው መሰረት፣ዓለም አቀፍ የዕቃዎች ወይም የሰዎች ማጓጓዣ ተግባር ወይም ከዚሁ ጋር በቀጥታ የተገኛኙ አግለግሎቶች፣ እንዲሁም በዓለም አቀፍ በረራ ወቅት ለፍጆታ የሚውሉ የቅባት ዘይቶች እና ሌሎች አላቂ የቴክኒክ ዕቃዎች እና ለኢትየጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚቀርብ ወርቅ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

**ሪ. ከታክስ ነፃ የሆኑ ግብይቶች**

ከታክስ ነጻ በሆኑ ግብይቶች ላይ አስራ አምስት ፐርሰንትም ሆነ ዜሮ ፐርሰንት ተጨማሪ እሴት ታክስ አይጣልባቸውም፡፡ አቅራቢው እቃውን ሲሸጥ ምንም አይነት ታክስ አይሰበስብም፡፡ እቃውን ሲገዛ የከፈለው ታክስ ቢኖር ከታክስ ባለስልጣን የሚጠይቀው ተመላሽም አይኖርም፡፡ እቃው ሲገዛ የተከፈለው ተጨማሪ ታክስ ለአቅራቢው እንደ ግዢ ወጪ ነው የሚወሰደው፡፡ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ የሆኑ እቃዎች እና አገልግሎቶች ብቻ የሚያቀርብ ሰው ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ አይችልም፡፡ በአዋጁ መሰረት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ የሆኑ ግብይቶች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ. በንግድ መልክ ለማረፊያነት የሚከራዩ ክፍሎች (አንቀጽ 8 (1) (ሀ))

ለ. ወደ ውጪ ከሚላኩት እቃዎች በስተቀር ዓይነታቸው ቀጥሎ የተመለከቱት የዕቃዎች ወይም የአገልግሎቶች አቅርቦት እንዲሁም ገቢ ዕቃዎች ከተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ ነፃ ናቸው፡፡

- ያገለገሉ መኖሪያ ቤት ሽያጭ እና የመኖሪያ ቤት ኪራይ
- የትራንስፖርት አገልግሎቶች
- የፋይናስ አገልግሎቶች
- የሕክምና አገልግሎቶች እና በሐኪም የሚታዘዙ መድኃኒቶች
- ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚቀርብ ወርቅ ወደ አገር ማስገባት
- በትምህርት ተቋማት የሚሰጡ የማስተማር አገልግሎቶች እንዲሁም በሕፃናት የሚሰጡ አገልግሎቶች
- በሃይማኖት ድርጅቶች የሚሠጡ የእምነት ወይም ከአምለኮት ጋር የሚገናኙ አገልግሎትች
- ለሰብአዊ ዕርዳታ የሚውሉ ዕቃዎች
- የኤሌክትሪክ፣ የኬሮሲን እና ውሃ አቅርቦት
- ወደ አገር የሚገቡ በአገር ውስጥ የሚሸጡ መጽሐፎች
- ማንኛውንም የስራ እንቅስቃሴ ለማከናወን ለሚሰጥ ፈቃድ ለመንግስት የሚፈፀም ክፍያ፡፡

እነዚህ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ የሆኑ ግብይቶችን በተመለከተ ዝርዝር ሁኔታዎች በሚኒስትሮች ምክር ቤት የተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 79/1995 ተደንግጓል፡፡

ለማጠቃለል አስራ አምስት ፐርሰት ተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ዜሮ በመቶ ታክስ ማስከፈያ መጠንና ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ የሆኑ ግብይቶችን የበለጠ ለመረዳት የሚከተለውን ምሳሌ

መመልከቱ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ ቀደም ብለን የጠቀስነውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ አንድ ለተጨማሪ እሴት የተመዘገበ የንግድ ሥራ ድርጅት በብር 200,000 የጥሬ ዕቃ ግዥ ቢፈጽምና ዕቃውን በብር 250,000 ቢሸጥ ተጨማሪ እሴት ታክስ ስሌት እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

**የታክስ ማስከፈያው 15% ከሆነ**

- ጥሬ ዕቃውን ሲገዛ የሚከፍለው ተጨማሪ እሴት ታክስ 200,000 X15/100 = 30,000 ይህ ማለት ጥሬ ዕቃ ሻጩ ዕቃውን ለድርጅቱ ሲሸጥ 30,000 ተጨማሪ እሴት ታክስ ሰብስቦ ለመንግስት ገቢ ያደረጋል ማለት ነው፡፡
- ድርጅቱ ዕቃውን ሲሸጥ የሚሰበስበው ተጨማሪ እሴት ታክስ ደግሞ 250,000 X15/100 = 37,500 ለታክስ አስገቢው ባለስልጣን የሚከፍለው ታክስ 37,500–30,000 = 7,500 ወይም 250,000—-200,000 = 50,000 X15/100 = 7,500

**ታክስ ማስከፈያው ዜሮ ፐርሰንት ከሆነ**

- ጥሬ ዕቃውን ሲገዛ የሚከፍለው ተጨማሪ እሴት ታክስ 200,000 X15/100 = 30,000
- ድርጅቱ እቃውን የሚሸጠው በብር 250,000 ነው፡፡ ማስከፈያው ዜሮ ፐርሰንት ስለሆነ ድርጅቱ የሚሰበስበው ተጨማሪ እሴት ታክስ የለም፡፡ ድርጅቱ በጥሬ እቃ ግዢ ወቅት የከፈለውን ተጨማሪ እሴት ታክስ ማለትም ብር 30,000 ማሟላት የሚጠበቅበትን ነገሮች ካሟላ ከግብር አስገቢው ባለስልጣን ሊጠይቅ ይችላል፡፡

**ዕቃው ከታክስ ነፃ ከሆነ**

- ድርጅቱ ጥሬ እቃውን ሲገዛ የሚከፍለው ተጨማሪ እሴት ታክስ 200,000 X15/100 = 30,000
- ድርጅቱ እቃውን ሲሸጥ የሚሰበስበው ተጨማሪ እሴት ታክስ የለም፡፡ ጥሬ እቃውን ሲገዛ የከፈለው ታክስ የወጪው አካል ይሆናል፡፡
- ከታክስ ባለስልጣኑም የሚጠይቀው ተመላሽ ታክስ አይኖርም፡፡

## ሸ. ግዴታዎች

የተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይ ግዴታዎች፡-

- ***ማስታወቂያ ማቅረብ፡-*** ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ሰው ታክሱን በትክክል የማስላት፣ በወቅቱ የመክፈል እና በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የታክስ ማስታወቂያውን ለባለስልጣኑ ማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡ (አንቀጽ 28)
- ***ደረሰኝ መስጠት፡-*** ተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበና ታክስ የሚከፍልበት ግብይት የሚካሂድ ሰው ዕቃዎቹን ለሚያቀርብለት ሰው ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡ ደረሰኙም የገቢዎች ሚኒስትር በሚወሰነው አይነት የሚዘጋጅ ነው፡፡
- ***የሂሳብ ሰነዶች መያዝ፡-*** ተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ሰው የተቀበላቸውን የታክስ ደረሰኞች ዋነኛ ቅጂ፣ የሰጣቸውን ማንኛውንም የታክስ ደረሰኞች ቅጂ ፣ ወደአገር ያስገባቸውን ወይም ወደውጭ የላካቸውን ዕቃዎች የሚያሳይ የጉምሩክ ሰነድ የሂሳብ መዝገቦች እና ሌሎች የገቢዎች ሚኒስትር በሚያወጣው መመሪያ የተዘረዘሩ የሂሳብ ሰነዶችን ለአስር ዓመታት በኢትዮጵያ ውስጥ ማስቀመጥ አለበት፡፡ (አንቀጽ 37)
- ለውጦችን ማስታወቅ (አንቀጽ 38)

**ቀ. የፍትሐብሔር ሐላፊነት የሚያስከትሉ ግዴታዎች**

የፍትሐብሔር ሐላፊነት የሚያስከትሉ የተጨማሪ እሴት ታክስ ግዴታዎች፡-

- ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ እያለበት አለመመዝገብ፣
- ሀሰተኛ የሆነ የታክስ ደረሰኝ አዘጋጅቶ መጠቀም፣
- የታክስ ደረሰኝ አለመስጠት፣
- ለተጨማሪ ታክስ የተመዘገበ ሳይሆን የታክስ ደረሰኝ መስጠት፣
- የሂሳብ ሰነዶችን አለመያዝ

- የታክስ ማስታወቂያን በጊዜው አለማቅረብ
- ታክስን አዘግይቶ መክፈል ናቸው፡፡

አንድ ተጨማሪ እሴት ከፋይ አዋጁን በመተላለፍ ከላይ የተጠቀሱትን ጥፋቶች ከፈፀመ የሚቀጣው የገንዘብ መቀጮ መጠን በአዋጁ ተመልክቷል፡፡ (አንቀጽ 45፣46፣እና 47 ተመልከቱ)

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. የሽያጭ ታክስ ጎጂ ጎኑ ምንድነው? ተጨማሪ እሴት ታክስ ምን ጎጂ ጎን አለበት ብላችሁ ታስባላችሁ?
2. ተጨማሪ እሴት ታክስ ከኢንቨስትመትን አንጻር ያለው ጠቀሜታ እንዴት ይገለጻል?
3. ተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይ ለመሆን መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ምንድናቸው?
4. በተጨማሪ እሴት ታክስ እና የሽያጭ ታክስ መካከል ያለው አንድነትና ልዩነት ምንድነው?
5. ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ መሆንና ዜሮ በመቶ ማስከፈያ መጠን መካካል ያለው ልዩነት ምንድነው? ዜሮ በመቶ ተጨማሪ እሴት ታክስ ማስከፈያ መጠን መደንገጉ ያለው ጠቀሜታ ላይ ተወያዩ፡፡
6. በፌዴራል መንግስት የሚጣለውና የሚሰበሰበው ተጨማሪ እሴት ታክስ በክልሎች ሽያጭ ታክስ ብቸኛ ሥልጣን ላይ ያለው እንድምታ ምንድነው?

### 2.2.2.2. ተርን ኦቨር ታክስ

**ሀ. ምንነት**

ተርን ኦቨር ታክስ ከሽያጭ ታክስ ጎራ የሚመደብ ሌላው የታክስ አይነት ነው፡፡ በሐገራችን ተርን ኦቨር ታክስ በህጉ ነጻ ካልተደረጉ በስተቀር ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገቡ ሰዎች በሐገር ውስጥ በሚሸጧቸው ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ላይ የሚጣል ታክስ ነው፡፡ ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው፡-

- ተርን ኦቨር ታክስ ስሌት መሰረት ጠቅላላ የሽያጭ ገቢ ነው፡፡ (It is an indirect tax imposed not on the value added but on the total turnover or sales of goods or services.)
- ተርን ኦቨር ታክስ የሚጣለው ከታክስ ነጻ እንዲሆኑ ያልተደረጉ እቃ አቅርቦት እና አገልግሎት ላይ ነው፡፡ ስለዚህ ተርን ኦቨር ታክስ የፍጆታ ታክስ ነው፡፡
- ተርን ኦቨር ታክስ የሚከፈለው ለተጨማሪ እሴት ታክስ ባልተመዘገበ ሰው ነው፡፡ ስለዚህ ለተጨማሪ እሴት ያልተመዘገበ ሰው ማለትም አመታዊ የሽያጩ ገቢው ከብር 500000 በታች የሆነ ሰው ተርን ኦቨር ታክስ ከፋይ ነው ማለት ነው፡፡

ተርን ኦቨር ታክስ በአዋጅ ቁጥር 308/1995 የሚጣልና የሚሰበሰብ ሲሆን የሚጣለውና የሚሰበሰበው በፌዴራል መንግስት ነው፡፡ ተርን ኦቨር ታክስ መጣልና መሰበሰብ ያስፈለገበት አንዱ ምክንያት የመንግስት ገቢ ምንጭ መሰረት ለማስፋት ነው፡፡ ሌላው በንግድ ሥራ ላይ በተሰማሩ ሰዎች መካከል ፍትሐዊነት እንዲሰፍን ለማድረግ ነው፡፡ ተርን ኦቨር ታክስ ያልተጣለ ቢሆን ኖሮ ታክስ ለመክፈል የሚገደዱት አመታዊ ግብይታቸው ከብር አምስት መቶ ሺ ብር በላይ የሆኑ ሰዎች ብቻ ይሆኑ ነበር፡፡ ይህ ፍትሐዊ ካለመሆኑም በላይ የታክስ ሥርዓቱን ጎዶሎ ያደርገዋል፡፡ ባጭሩ ተርን ኦቨር ታክስ የመንግስትን ገቢ ምንጭ ለማስፋት፣ የታክስ ሥረዓቱን ሽፋን የተሟላ ለማድረግ እና በንግድ ግንኙነቱ ፍትሐዊነት እንዲሰፍን በማቀድ የተጣለ ታክስ ነው ለማለት ይቻላል፡፡

### ለ. ከፋዮች

ከላይ እንደተመለከተው የተርን ኦቨር ታክስ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገቡ እና በአገር ውስጥ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን የሚሸጡ ሰዎችን የሚመለከት ነው፡፡ ስለዚህ በአገር ውስጥ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን የሚሸጥ ማንኛውም ሰው በሽያጭ ላይ ሊከፈል

የሚገባውን ታክስ ከገዥው ሰብስቦ ለታክስ ባለስልጣን ገቢ ማድረግ አለበት፡፡ ስለዚህ የተርን ኦቨር ታክስ ከፋይ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገበ እና በአገር ውስጥ ዕቃዎችን የሚሸጥ ወይም አገልግሎቶችን የሚያቀርብ ሻጭ ወይም አቅራቢ ነው፡፡

### ሐ. ማስከፈያ መጠን እና የስሌቱ መሰረት

አዋጁ ሁለት አይነት የታክስ ማስከፈያ መጠን ይደነግጓል፡፡ አንደኛው ማናቸውንም በአገር ውስጥ የሚሸጡ ዕቃዎች፣ የስራ ተቋራጮች፣ የእህል ወፍጮ ቤቶች፣የትራክተሮች እና ኮምቦይንሀርቨሰተሮች በአገር ውስጥ በሚሰጡት አገልግሎቶች የሚመለከት ነው፡፡ የታክስ ማስከፈያው መጠንም ሁለት በመቶ ነው፡፡ ሁለተኛው ሌሎችን የሚመለከት ሲሆን የታክስ ማስከፈያው መጠንም አሥር በመቶ ነው፡፡ አስር በመቶ ተርን ኦቨር ታክስ ማስከፈያ ሌሎች አገልግሎቶች ውስጥ የምክር አገልግሎት፤ ህትመት፤ ስልጠናን መጥቀስ ይቻላል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው የተርን ኦቨር ታክስ የሚሰለው በዕቃው ወይም አገልግሎት ጠቅላላ የሽያጭ ገቢ ላይ ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ቆዳ ፋብሪካ ለጫማ የሚሆን ቆዳ በብር 100 ቢገዛ እና ለጫማ ፋብሪካ ደግሞ በብር 150 ቢሸጥ፤ ጫማ ፋብሪካው ደግሞ ለጅምላ ሻጭ በብር 200 ቢሸጥ፤ ጅምላ ሻጩ ደግሞ ለችርቻሮ ሻጩ በብር 250 ቢሸጥ፤ችርቻሮ ሻጩ ደግሞ ለተጠቃሚው በብር 300 ቢሸጥ የተርን ኦቨር ታክሱ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

- የቆዳ ፋብሪካ ተርን ኦቨር ታክስ 2/100 X100 = 2ብር
- የጫማ ፋብሪካ ተርን ኦቨር ታክስ 2/100 X150 = 3ብር
- ጅምላ ሻጭ ተርን ኦቨር ታክስ 2/100 X200 = 4ብር
- ችርቻሮ ሻጭ ተርን ኦቨር ታክስ 2/100 X250 = 5ብር
- ሸማች ተርን ኦቨር ታክስ 2/100 X300 = 6ብር

አጠቃላይ ተርን ኦቨር ታክስ 20ብር ይሆናል ማለት ነው፡፡ ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው አንድ ዕቃ ከአንድ ጊዜ በላይ ታክስ የሚጣልበት መሆኑን ነው፡፡

### መ. ነፃ የሆኑ ግብይቶች

በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ግብይቶች ከታክስ ነፃ ናቸው፡፡

- ቢያንስ ሁለት ዓመት ያገለገለ መኖሪያ ቤት ሽያጭ እና የመኖሪያ ቤት ኪራይ
- የፋይናስ አገልግሎቶች
- በሃይማኖት ድርጅቶች የሚሰጡ የእምነት ወይም ከአምልኮት ጋር የሚገኛኙ አገልግሎቶች
- የሕክምና አገልግሎቶች እና በሐኪም የሚታዘዙ መድኃኒቶች
- በትምህርት ተቋማት የሚሰጡ የማሰተማር አገልግሎቶች እንዲሁም ለሕፃናት የሚሰጡ አገልግሎቶች
- ለሰብዓዊ ዕርዳታ የሚውሉ ዕቃዎች አገልግሎቶች
- የኤሌክትርክ የኬሮሲን እና ውሃ አቅርቦት
- የትራንስፖርት አገልግሎቶች
- ማንኛውም የሥራ እንቅስቃሴ ለማከናወን ለሚሰጥ ፈቃድ ለመንግስት የሚፈጸም ክፍያ
- ከስልሳ በመቶ በላይ ሠራተኞቹ አካል ጉዳተኛች የሆኑበት አካል ጉዳተኞችን ቀጥሮ የሚያሰራ ድርጅት የሚያቀርባቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች፡፡
- መፃሕፍት

### ሰ. ግዴታዎች እና ግዴታዎችን አለመወጣት የሚያስከትለው ሐላፊነት

የተርን ኦቨር ታክስ ከፋይ የተለያዩ ግዴታዎች አለበት፡፡ አንዱ ግዴታ ታክሱን ማስታወቅና ታክሱን መክፈል ነው፡፡ የተርን ኦቨር ታክስ ከፋይ የታክሱን ስሌት በትክክል በማከናወን የታክሱን ማስታወቂያ በሕጉ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ለታክሱ ባለስልጣን በማቅረብ ታክሱን የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡ የሒሳብ ጊዜውም እንደ ግብር ከፋዮቹ ደረጃ ይለያያል፡፡ (አንቀጽ 10

(2)) ታክሱ የማስታወቂያ ማቅረቢያ ጊዜውም እያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ በተጠናቀቀ በአንድ ወር መክፈል አለበት፡፡ ስለዚህ ተርን ኦቨር ታክስ ታክስ ከፋዩ ራሱ ታክሱን በማሳወቅ የሚከፈል ነው፡፡

ሁለተኛው የተርን ኦቨር ታክስ ከፋዩ ግዴታ ሒሳብ መዝገብ መያዝ ነው፡፡ ቀደም ሲል በገቢ ግብር አዋጅ ውስጥ የሂሳብ መዝገብ መያዝ ግዴታ ያለባቸው ታክስ ከፋዮች ተመልክተናል፡፡ በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 48 መሠረት የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ የተጣለባቸው ታክስ ከፋዮች ለተርን ኦቨር ታክስ አወሳሰን እንዲያገለግል በገቢ ግብር አዋጅ የታዘዘውን የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ አለባቸው፡፡ በዚህ መሰረት በገቢ ግብር አዋጅ መሰረት የደረጃ ‘ሀ’ ግብር ከፋዮች ተብለው የሚታወቁ እና ለተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዘገብ ግዴታ የሌለባቸው ታክስ ከፋዮች እንዲሁም የደረጃ ለ ግብር ከፋዮች የሆኑ የተርን ኦቨር ታክስ ከፋዮች የሒሳብ መዝገብ መያዝ ግዴታ አለባቸው፡፡ የደረጃ ሐ ግብር ከፋዮች ግን የሒሳብ መዝገብ መያዝ ግዴታ የለባቸውም፡፡ ሌላው የተርን ኦቨር ታክስ ከፋይ ግዴታ ለውጦችን ማስታወቅ ነው፡፡

**ረ. አወሳሰን**

ተርን ኦቨር ታክስ በመረጃ ወይም በቁርጥ ሊወሰን ይችላል፡፡ ከላይ እንደተመለከተው አንድ የተርን ኦቨር ታክስ  ታክስ ከፋዩ ራሱ ታክሱን በማሳወቅ የሚከፈል የታክስ አይነት ነው፡፡

በተርን ኦቨር ታክስ አወሳሰን ሲባል ሕጉ የተወሰኑ የተርን ኦቨር ታክስ ከፋዮች የሒሳብ መዝገብ እንዲይዙ ግዴታ ይጥላል፡፡ የታክስ ባለስልጣኑም የታክስ ከፋዩ ያሳወቀው ታክስ ትክክል ለመሆኑ ለማረጋገጥ የታክስ ከፋዩን ሒሳብ መዛግብትና ሌሎች ሰነዶችን የመመርመር ሥልጣን አለው፡፡ የታክስ ባለስልጣኑ በምርምራው ታክስ ከፋዩ ሊከፍል የሚገባውን ታክስ አሳንሶ ያስታወቀ መሆኑን ከደረሰበት ተጨማሪ የታክስ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

በመርህ ደረጃ የሒሳብ መዝብ መያዝ ግዴታ ያለባቸውን ታክስ ከፋዮች ታክስ የሚወስነው የሒሳብ መዛግብትና ሌሎች ደጋፊ ሰነዶችን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ይህም የሚሆነው መዛግብቶቹና ደጋፊ ሰነዶቹ በታክስ ባለስልጣኑ ዘንድ ተቀባይነት ካገኙና ታክስ ከፋዩም እንዲያቀርባቸው ሲጠየቅ ካቀረባቸው ነው፡፡ ነገር ግን መዛግብቶቹ እና ደጋፊ ሰነዶቹ በማንኛውም ምክንያት ተቀባይነት ካጡ ወይም ታክስ ከፋዩ እንዲቀርባቸው ሲጠየቅ

ካላቀረባቸው ወይም የሒሳብ መዛግብትና ደጋፊ ሰነዶቹ ከሌሉ የታክስ ባለስልጣኑ ታክሱን ባለው መረጃ ወይም የዕቃውን ወይም የአገልግሎቱን የአገር ውስጥ ገበያ ዋጋ፣ ዋጋው የማይታወቅ ከሆነ የተመሳሳዩን የገበያ ዋጋ መሰረት በማድረግ ለመወሰን ይችላል፡፡ (አንቀጽ 11 (2))

በሌላ በኩል በገቢ ግብር አዋጅ መሰረት የሂሳብ መዝገብ የማይዙ የደረጃ 'ሐ' ግብር ከፋዮች የተርን ኦቨር ታክስ በቁርጥ የሚወሰን ነው፡፡ የስሌቱ መሰረትም ለገቢ ግብር መሰረት የሆነው ጠቅላላ ገቢ ነው፡፡ (አንቀጽ 11 (3))

የተርን ኦቨር ታክስ ሕግን መተላለፍ የፍትሐብሔር ተጠያቂነት ሊያስከትል ይችላል፡፡ የተርን ኦቨር ታክስ ከፋይ የሆነ ሰው በአዋጅ የተጣለበትን ግዴታ ካልተወጣ አስተዳደራዊ መቀጮ ሊጣልበት ይችላል፡፡ አስተዳደራዊ መቀጮ ሊያስጥሉ የሚችሉ ጥፋቶች ውስጥ፡-

- የታክስ ማስታወቂያ በጊዜ አለማቅረብ፣
- ታክሱን አዘግይቶ መክፈል
- መዝገብ አለመያዝ  የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

አንድ ተርን ኦቨር ታክስ ከፋይ ታክስ ማስታወቂያ በጊዜ ያላቀረበ እና ታክሱን መክፈል ባለበት ጊዜ ውስጥ ካለከፈለ የሚጣልበት የገንዘብ መቀጮ መጠን በአዋጁ ተመልክቷል፡፡ (አንቀፅ 23 እና 24)

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. ተርን ኦቨር ታክስን መጣል ያስፈለገበት ምክንያት ምንድነው?
2. በተርን ኦቨር ታክስ እና በተጨማሪ እሴት ታክስ መካካል ያለው ልዩነትና አንድነት ምንድነው?

### 2.2.2.3. ኤክሳይዝ ታክስ

***ሀ. ምንነት***

ኤክሳይዝ ታክስ በተወሰኑና በተመረጡ ዕቃዎች ላይ የሚጣል የታክስ አይነት ነው፡፡ እንደ ሌሎች የታክስ አይነቶች ሁሉ የኤክሳይዝ ታክስ የሚጣልበት ዋና አላማ የመንግሥትን ገቢ ለማሳደግ  ነው፡፡ ለዚህ አላማ ሲባል በቅንጦት ዕቃዎች እና መሠረታዊ  በመሆናቸው  ምክንያት

የገበያ ፍላጎታቸው በማይቀንስ ዕቃዎች ላይ ኤክሳይዝ ታክስ ይጣላል። ይሄም ኤክሳይዝ ታክስ በተለያዩ ሁኔታ ውስጥ የገበያ ፍላጎታቸው ብዙም የማይለዋወጥ ዕቃዎች የሚመለከት ነው። በተጨማሪም ኤክሳይዝ ታክስ እንደ ማስተካካያ ታክስ (corrective tax) እንዲያገለግል የሚጣል ታክስ ነው። ለዚህም ኤክሳይዝ ታክስ ጎጂ በሆኑ ዕቃዎች ላይ ይጣላል። ለህብረተሰቡ ጤና እና ማህበራዊ እሴት ላይ ችግር የሚፈጥሩ ዕቃዎች ላይ ኤክሳይዝ ታክስ መጣሉ የዕቃዎቹ አጠቃቀም እንዲቀንስ ያደርጋል የሚል ግምት አለ።

በአሁኑ ጊዜ ኤክሳይዝ ታክስ የሚጣለው እና የሚሰበሰበው በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 307/95 መሰረት ነው።

## ለ. ታክስ ከፋይ፤ ታክስ የሚጣልባቸው ዕቃዎች፣ ማስከፈያ ልክ፣ ስሌቱ መሠረት እና አከፋፈል

ኤክሳይዝ ታክስ ከውጭ ወደሀገር ውስጥ በሚገቡ ዕቃዎች ወይም ሀገር ውስጥ በሚመረቱ ዕቃዎች ላይ ሊጣል ይችላል። ስለዚህ ኤክሳይዝ ታክስ ከፋይ የሚሆነው ሀገር ውስጥ በሚመረቱ ዕቃዎችን በተመለከቱ የዕቃ አምራች ሲሆን ከውጪ ወደ ሀገር ውስጥ በሚገባ ዕቃዎች በተመለከተ ደግሞ አስመጪው ነው። ከውጭ ወደሀገር ውስጥ ሲገቡ ወይም ሀገር ውስጥ ሲመረቱ ኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባችው የሚገባ ዕቃዎች ዝርዝር እና የማስከፈያው ልክ ከአዋጅ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ተዘርዝረዋል። በአጠቃላይ በአዋጁ ኤክሳይዝ ታክስ የሚጣልባቸው ዕቃዎች ወይም ምርቶች በአጠቃላይ አሥራ ዘጠኝ ናቸው። እነሱም፡-

- ማናቸውም ዓይነት ስኳር በአንኳር መልክ) ሞላሰስን ሳይጨምር
- መጠጦች ((ማናቸውም ለስላሳ መጠጦች (ከፍሬ ጭማቂዎችና እነዚህን ከመሳሰሉ በስተቀር)፣መልክ የተዘጋጁ ለስላሳ መጠጦች፤ በፋብሪካ የሚመረቱ የታሸገ ውሃ፤ ማናቸውም አልኮል ያለባቸው መጠጦች፤ ማናቸውም ቢራና እስታወት፤ ማናቸውም የወይን ጠጅ መጠጦች፤ዊስኪ፤ሌሎች አልኮል ያለባቸው መጠጦች)
- ማናቸውም ዓይነት ንፁሕ አልኮል
- ትምባሆ የትምባሆ ውጤቶች (የትምባሆ ቅጠል፤ ሲጋሬት፣ ሲጋራ፣ ሲጋሪሎስ፣ ፒፓ ትምባሆ፣ሱረትና ሌሎች የትምባሆ ውጤቶች)
- ጨው

- ነዳጅ- ሱፐርቤንዚን፣ ተራ ቤንዚን፣ ፔትሮል፣ ጋዞሊንና ሌሎች የሞተር ስፒሪት
- ሽቶዎች እና ቶይለት ወተርስ
- ጨርቃ ጨርቅ እና ለጨርቃ ጨርቅ የተሰሩ ዕቃዎች (ከተፈጥሮ ሐር፣ ከናይል ከሱፍ ወይም ከማናቸውም ሌሎች ተመሳሳይ ነገሮች በሹራብ መልክ ቢሆን የተሰሩ ጨርቃ ጨርቆች (በሙሉ ሆነ በከፊል የተሰራ አመድማ፣ ነጭ ቀለም የተነከረ ወይም የታተመ፣ በማናቸውም ቁመት ወይም ወርድ የተሰራ ጨርቃ ጨርቅ (ከወባ መከላከያ አጎበር እና ከአቡጀዲ በስተቀር) እንዲሁም የብርድልብሶች፣አንሶላዎች፣የአልጋ ሽፋኖች፣ፎጣዎች፣ጠረጴዛ ልብሶች፣እነዚህንም የመሳሰሉ ጨርቃ ጨርቆች፤ከጨርቃ ጨርቅ የተሰሩ ወይም የተዘጋጁ ልብሶች)
- ከወርቅ፣ከብርና ከሌሎች ከነገሮች የተሰሩ ጌጣጌጦች
- ለመኖሪያ ቤት አገልግሎት የሚሆኑ ሳህን ማጠቢያ መኪናዎች
- ለመኖሪያ ቤት አገልግሎት የሚሆኑ የልብስ ማጠቢያ መኪናዎች
- የቪዲዮ ዴክ
- የቴሌቭዥን እና የቪዲዮ ካሜራዎች
- ተቀባይ ቴሌቪዥን፣ ከግራማፎን፣ ከራዲዮ ወይም ከድምፅ መቅረጫና መስሚያ መሣሪያዎች ጋር ተጣመሩ ቢሆንም ባይሆንም
- ለመንገኞች መጓጓዣ የሚሆኑ ተሽከርካሪዎች (አውቶሞብሎች) "እስቴሽንዋገን"የአገልግሎት መኪናዎች ላንድሮቨሮች፣ ጂፖች፣ፒክአፖች እና እነዚህንምየ መሳሰሉ ተሽከርካሪዎች፣ ባለሞተር ካራቫኖች ጭምር የተገጣጠሙ ወይም ያልተገጣጠሙ በመጀመሪያ ሲመጡ ሊኖራቸው ከሚገባው መሳሪያ ጋር
- የወለል ምንጣፎች
- የአስቤስቶስና የአስቤስቶስ ውጤቶች
- የጠረጴዛ፣ የግድግዳና የእጅ ሰዓቶች
- አሻንጉልቶችና መጫወቻዎች

ወደሀገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎችን በተመለከተ የታክስ ሥሌቱ መሰረት የዕቃዎች ዋጋ፣ የመድህን አረቦን እና የማጓጓዣ ወጪ (ሲ .አይ.ኤፍ) ነው። አስመጪውም ታክሱን ዕቃዎቹን ከጉምሩክ ክልል በሚያወጣበት ጊዜ መክፈል አለበት። ነገር ግን ታክስ ከፋዩ ባለስልጣን

በሚፈቅደው የዕቃ መጋዘን ውስጥ ካስቀመጠ ዕቃዎቹ ከመጋዘን እንደወጡ ወዲያውኑ ታክሱን ይከፍላል፡፡

በአገር ውስጥ በተመረተ ዕቃ ላይ የሚጣለውን የኤክሳይዝ ታክስ ስሌቱ መሰረት ለማምረት የወጣው ወጪ ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው ጨው ለማምረት 6000 (ስድስት ሺ) ብር ቢያወጣ የጨው ምርት ማስከፈያ ልክ ሰላሳ ፐርሰነት በመሆኑ አምራቹ 1800 (አንድ ሺ ስምንት መቶ ብር) ብር ኤክሳይዝ ታክስ ይከፍላል ማለት ነው፡፡ አምራቹም ዕቃዎቹ ከተመረቱበት ቀን ጀምሮ በሰላሳ ቀን ውስጥ ታክሱን የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡ ስለዚህ በአገር ውስጥ በተመረተ ዕቃ ላይ የሚጣለውን የኤክሳይዝ ታክስ መጠን ለመወሰን ዕቃውን ለማምረት የወጣው ወጪ መታወቅ ይኖርበታል፡፡

## ሐ. ግዴታዎች እና ግዴታዎችን አለመወጣት የሚያስከትለው የፍትሐብሔር ሃላፊነት

አንዱ የኤክሳይዝ ታክስ ከፋይ ግዴታ አግባብ ባለው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓትና የታክስ ባለስልጣኑ በሚፈቅደው ዓይነት የሂሳብ መዛግብትንና ደጋፊ ሰነዶችን መያዝ ነው፡፡ በተጨማሪም ኤክሳይዝ ታክስ ከፋይ የታክስ ባስልጣን በሚሰጠው ቅጽ ላይ ታክሱን በሚገባ ለመሰበሰብ አስፈላጊ የሚሆነውን መረጃ የሚያሳይ መግለጫ ሞልቶ ለታክስ ባለስልጣኑ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡ (አንቀፅ 8)

እንዲሁም ታክስ ከፋዩ የታክስ ባለስልጣን ለሚያደረገው ማጣራት ሥራ በተመለከተ ባለስልጣኑ የሚጠይቀውን የመፈፀም ግዴታ አለበት፡፡ እንዲሁም የታክስ ባለስልጣን ወኪል በሥራ ቦታው በመገኘት ስለታክስ አሰበሰብ ለሚያደገርገው ቁጥጥር አስፈላጊ የሆነውን ሁሉ አሟልቶ ማቅረብ አለበት፡፡

ታክስ ከፋይ የሥራውን ዓይነትና የሥራውን አድራሻ እንዲሁም ሥራውን ሲጀምር ወይም ሲቋረጥ ሁኔታውን ለባለስልጣኑ ወዲያውኑ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

ሌላው የኤክሳይዝ ታክስ ከፋይ ግዴታ ለውጦችን ማሳወቅ ነው። እንደ ሌሎች ታክሶች ሁሉ የኤክሳይዝ ታክስ ከፋይ ስሙን፣ አድራሻውን፣ የንግድ ሥራውን ቦታ፣ አደረጃጀቱ፣ ወይም ታክስ የሚከፈልበትን ዋነኛ ንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ወይም የሚያከናውናቸው ተግባራት ዓይነት፣ ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የሚያከናውንበት አድራሻ ወይም ስም የቀየረ እንደሆነ ይህንኑ ለታክሱ ባለስልጣን በአምስት ቀናት ጊዜ ውስጥ ማሳወቅ አለበት።

በአጭሩ ከላይ የተጠቀሱት ግዴታዎች ኤክሳይዝ ታክስ ከፋይ በሚያቀርበው መግለጫ ወይም ታክስ ማስታወቂያ መሰረት የሚከፈል ታክስ ከመሆኑ ጋር የተገናኙ ናቸው። ለዚህም ታክስ ከፋዩ ተገቢ የሆነ መረጃ ለታክስ ባለስልጣኑ መስጠት ይኖርበታል። እንዲሁም ታክስ ከፋይ ራሱ የታክሱን መጠን በማስላት መክፈል ይጠበቅበታል። በሌላ በኩል የታክስ አስገቢው ባለስልጣን የቀረበውን መረጃ ትክክለኝነት የማጣራትና የማረጋገጥ ሥልጣን አለው። ታክስ ከፋይ መክፈል ካለበት ታክስ ያነሰ እንደሆነ የታክስ ባለስልጣኑ ተጨማሪ ታክስ ይወስናል። የታክስ ውሳኔውም ለታክስ ከፋይ መድረስ አለበት። ታክስ ከፋዩም ታክሱን የታክስ ውሳኔው በደረሰው 30 ቀን ውስጥ መክፈል አለበት።

ከላይ ከተጠቀሱት ግዴታዎች ውስጥ የታክስ ማስታወቂያን በጊዜው አለማቅረብ እና ታክስን አዘግይቶ መክፈልም የፍትሐብሔር ሐላፊነት ሊያስከትሉ እንደሚችሉ በሕጉ ተደንግጓል።

## 2.3. የቴምብር ቀረጥ

የቴምብር ቀረጥ በሰነዶች ላይ የሚጣል ነው። የቴምብር ቀረጥ የሚጣለውና የሚሰበሰበው በቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር 110/90 እና በቴምብር ቀረጥ ደንብ ቁጥር 221/1954 ነው። ሆኖም ግን የቴምብር ቀረጥ ደንብ ቁጥር 221/1954 ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት የሚኖራቸው የቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር 110/90 እስካልተቃረኑ ድረስ ነው።

### ሀ. የሚከፈልባቸው ሰነዶች፣ አተማመን፣ ከፋይ እና ቀረጥ የሚከፈልበት ጊዜ

የቴምብር ቀረጥ የሚከፈልባቸው ሰነዶች፣ የቀረጡ አተማመን፣ ቀረጡን የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰው እና ቀረጡ የሚከፈልበት ጊዜ በአዋጅ ተደንግጓል።

የቴምብር ቀረጥ ማስከፈያ ልክ በአዋጅ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተዘረዘረ ሲሆን የቀረጡ አተማመን ሁለት ዓይነት ስልትን የተከተለ ነው፡፡ አንዱ በቁርጥ የሚወሰን ሲሆን ሁለተኛው ዋጋን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ቀረጡ በቁርጥ የሚከፈለው በሰነዱ መሰረት ተፈፃሚ የሚሆነው መብት ወይም ግዴት ሊተመን የማይችል ሲሆን ነው፡፡ በሌላ በኩል ተፈፃሚ የሚሆነው መብት ወይም ግዴታ በገንዘብ ሊተመን የሚችል ከሆነ ቀረጡ በዋጋው መቶኛ የሚሰላ ነው፡፡

ቁረጡን የመክፈል ግዴታን በተመለከተ በህጉ በሌላ አኳኋን ካልተገለፀ በስተቀር በአንድ ሰነድ ተጠቃሚ የሆነ ሰው ሰነዱ ላይ የሚተመነውን የቴምብር ቀረጥ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

በአዋጅ የቴምብር ቀረጥ ከሚከፈልባቸው ሰነዶች ውስጥ አንድ የንግድ ማህበር፣ የህብረት ሥራ ማህበር ወይም የማንኛውም አይነት ማህበር መመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ ሲሆን የማስከፈያው ልክ በቁርጥ ነው፡፡ ቀረጡም የሚከፈለው ከምዝገባ በፊት ወይም በምዝገባ ጊዜ ነው፡፡

ግልግል የቴምብር ቀረጥ የሚከፈልበት ሁለተኛው የሰነድ አይነት ነው፡፡ ግልግል (award) ማለት ስለግልግል፣ ስለዕረቅ፣ስለስምነት ወይም ስለሌላ ተመሳሳይ ጉዳይ በሁለት ተዋዋይ ወገኖች በተደረገ ስምምነት መሰረት በፍርድ ቤት ሳይሆን በገላጋዮች አልቆ በጽሑፍ በተሰጠ ውሳኔ ማለት ነው፡፡ የቀረጡ አተማመን ሥልትም በዋጋው መሠረት ነው፡፡ ጉዳያቸውን በግልግል የሚያስወስኑ ወገኖች ለቴምብር ቀረጥ አከፋፈል በጋራና በተናጥል ተጠያቂ ናቸው፡፡ ቀረጡም የሚከፈለው ውሳኔው ከመሰጠቱ በፊት ወይም በሚሰጥበት ጊዜ ነው፡፡

የቴምብር ቀረጥ የሚከፈልበት ሶስተኛው ሰነድ አይነት ማገቻ (bond) ነው፡፡ ማገቻ ማለት ምን ማለት እንደሆነ በአዋጅ ተደንግጓል፡፡ (አንቀጽ 2 (2)) ቀረጡም ልክ በዋጋው የሚሰላ ነው፡፡ ቀረጡን የመክፈል ግዴታ በሰነዱ ተጠቃሚ የሆነ ሰው ነው፡፡

አራተኛው የዕቃ ማከማቻ ማረጋገጫ ሰነድ ነው፡፡ የዕቃ ማከማቻ ማረጋገጫ ሰነድ ላይ የሚከፈለው የቀረጥ ልክ በዋጋው ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ቀረጡን የመክፈል ግዴታ በሰነዱ ተጠቃሚ የሆነ ሰው ነው፡፡ ቀረጡም የሚከፈለው ማረጋገጫው በሚሰጥበት ጊዜ ነው፡፡

አምስተኛው ውሎች፣ ስምምነቶችና መግለጫዎቻቸው ሲሆን የሚከፈለው ቀረጥ ልክ በዋጋው ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ቀረጡን የመክፈል ግዴታ የተበዳሪው ነው፡፡ ቀረጡም በሰነዱ ላይ ከመፈረሙ በፊት ወይም በሚፈርምበት ጊዜ መክፈል አለበት፡፡

ስድስተኛው ውሎች፣ስምምነቶችና መግለጫዎቻቸው ላይ የሚከፈለው ቀረጥ ሲሆን ልኩም በቁርጥ የተወሰነ ነው፡፡ ቀረጡን የመክፈል ግዴታ በሰነዱ ተጠቃሚ የሆነ ሰው ሲሆን ቀረጡም በውሉ ወይም በስምምነት ሰነዶች ላይ ከመፈረማቸው በፊት ወይም በሚፈረምበት ጊዜ የሚከፈል ነው፡፡

ሰባተኛው ሕብረት ስምምነት ነው፡፡ በአከፋፈሉ የተወሰደው ስሌት በቁርጥ ሲሆን ለሚከፈለውን ቀረጥ አሰሪውና ሰራተኞቹ በጋራና በተናጠል ተጠያቂ ናቸው፡፡ ቀረጡ የሚከፈለው ስምምነቱ ሲመዘገብ ወይም ሲሻሻል ነው፡፡

ስምንተኛው የቅጥር ውል ስምምነት ነው፡፡ የቅጥር የውል ስምምነት ላይ የሚከፈለው ቀረጥ ልክ የአንድ ወር ደመወዝ አንደ መቶኛ ነው፡፡ ቀረጡን የመክፈል ግዴታ የአሰሪው ነው፡፡

ዘጠነኛው ኪራይ፣የተከራይ አከራይና መሰል መብት ማስተላለፊያ ሰነድ ሲሆን ለአከፋፈሉ መሰረት የተደረገው ዋጋው ሲሆን በውሉ ውስጥ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር ቀረጡን የመከፈል ግዴታ ያለበት ተከራይ ነው፡፡

አስረኛው ሰነድ ማረጋገጫ (notaries acts) ነው፡፡ ቀረጡ የተሰላው በቁርጥ ሲሆን ቀረጡም የሚከፈለው ማረጋገጫው በሚሰጥበት ጊዜ ነው፡፡

አስራ አንደኛው የውክልና ሥልጣን ሰነድ ነው፡፡ቀረጡ በቁርጥ የተወሰነ ሲሆን የማስከፈያ ልኩም ሰለሳ አምስት ብር ነው፡፡

የመጨረሻው የንብረት ባለቤትነት ስም ማስመዝገቢያ ሰነድ ነው፡፡ ቀረጡ በዋጋው ሁለት መቶኛ ሲሆን ሌላ ስምምነት ከሌለ በስተቀር ቀረጡን የመክፈል ግዴታ የንብረቱ ባለቤትነት የሚመዘገብለት ሰው ነው፡፡ ቀረጡም የሚከፈለው የንብረት በለቤትነት ስም ማስመዝገቢያ ሰነድ ላይ የማስመዝገቡ ተግባር ከመፈፀሙ በፊት ወይም በሚፈፀምበት ጊዜ ነው፡፡

ሆኖም ግን የሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ የሚተመነው በንብረቱ ሰነድ ውስጥ በተወሰነው የንብረቱ ዋጋ ላይ ሆኖ ዋጋዉ አገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን ተቀባይነት ያገኘ እንደሆነ ነው፡፡ በንብረቱ ሰነድ ላይ የተመለከተው ዋጋ ባለስልጣኑ ያልተቀበለው እንደሆነ ተገቢውን የቴምብር ቀረጥ የሚከፈልበት የንብረቱ ዋጋ በባለስልጣኑ ይወሰናል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ሰነዶች ላይ የሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ ከአምሳ ብር በታች ከሆነ ክፍያው ተገቢውን ዋጋ የያዘውን ቴምብር በመለጠፍ ይፈፀማል፡፡ ከአምሳ ብር በላይ ከሆነ ግን የፌዴራል መንግሥት የገቢዎች ቦርድ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ቴምብር ከመለጠፍ በሌላ መንገድ ቀረጡ እንዲከፈል ሊደረግ ይችላል፡፡

## ሰ. የቴምብር ቀረጥ ሕግን መተላለፍ የሚያስከትለው ውጤት

የቴምብር ቀረጥ ሕግን መተላለፍ የፍትሐብሔር ወይም የወንጀል ውጤት ሊኖረው ይችላል፡፡ (የወንጀል ውጤቱን በኋላ የምንመለስበት ይሆናል፡፡) የቴምብር ቀረጥ ሕግን መተላለፍ በፍትሐብሔር ረገድ ያለው ውጤት የቴምብር ቀረጥ የሚጣልባቸው ሰነዶች ከላቸው ተቀባይነት ጋር የተያይዘ ነው፡፡

በዚህ መሰረት የቴምብር ቀረጥ የሚከፈልባቸው ሰነዶች ሕጉ በሚያዘው መሠረት ትክክለኛ የቴምብር ቀረጥ ካልተከፈለባቸው በስተቀር በውል ወይም በህግ ማስረጃ የመቀበል ሥልጣን ባለው ሰው ወይም የመንግስት መሥሪያ ቤት ዘንድ በማስረጃነት ተቀባይነት አይኖራቸውም፡፡ ምልክት አይደረግባቸውም ወይም ማረጋገጫ አይሰጣቸውም፡፡ ሆኖም ግን ይህ በወንጀል ፍ/ቤት በሚታይ ክርክር በማስረጃነት የሚቀርቡ ሰነዶችን አይመለከትም፡፡ የቴምብር ቀረጥ ያልተከፈለባቸው ሰነዶች በፍትሐብሔር ጉዳይና በወንጀል ጉዳይ የተለያየ ውጤት እንዳላቸው ልብ ሊባል ይገባል፡፡ በሌላ በኩል በማስረጃነት ተቀባይነት ያላገኙ ሰነዶች ሊከፈልባቸው የሚገባው ቀረጥ በሁለት እጥፍ ተከፍሎባቸው በመረጃነት ሊቀርቡ እንደሚችሉ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

### ሐ. የመሰብሰብ ሥልጣንና የይግባኝ ሥርዓት

የቴምብር ቀረጥ የመሰብሰብና አዋጁን የማስፈፀም ሥልጣን የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን ነው፡፡ የአገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን ቀረጥ ከፋዮች ስለቀረጡ አወሳሰን የሚረዱ ሰነዶችና ውሳኔዎችን እንዲያቀርቡ ማድረግና የመመረመር ሥልጣን አለው፡፡ እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው እራሱ ቀርቦ እንዲያስመረምር ወይም እንዲያስረዳ ለማዘዝ ይቻላል፡፡ በዚህ ሁኔታ ቀረጥ ከፋይ ለመፈፀም ፈቃደኛ ሳይሆን ከቀረ ቀረጡን በግምት ለመወሰንና ለመሰብሰብ ሥልጣን አለው፡፡

ባለስልጣኑ በወሰነው የቴምብር ቀረጥ ሂሳብ የማይስማማ ቀረጥ ከፋይ ባለስልጣኑ ውሳኔውን በጽሁፍ ካስታወቀበት ቀን አንስቶ ከ21 ቀኖች በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ለማቅረብ ይቻላል፡፡

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. የቴምብር ቀረጥ ዋና አላማ ምንድነው?
2. ውልን በተመለከተ የቴምብር ቀረጥ አለመክፈል የሚኖረው ውጤት ምንድነው?
3. የቴምብር ቀረጥ በክልሎች እንዴት ይጣላል? እንዴትስ ይሰበሰባል? የሕግ መሰረቱስ ምንድነው?
4. ግዮን ሆቴል ዋና ቦታ መግቢያ ቲኬት በሚያስከፍለው ላይ የቴምብር ቀረጥ እንዲከፍል በመጠየቁ ምክንያት ይግባኙን ለከፍተኛ ፍ/ቤት (በፍትሐ ብሔር መ.ቁ.51/79) አቅርቦ ተቀባይነት በማጣቱ ይግባኙን ለጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ በነበረው ይግባኝ ላይ መልስ ሰጪ የነበረው የአገር ውስጥ ገቢ አስተዳደር በቀረበው ይግባኝ ላይ ሁለት መከራከሪ ነጥቦችን አቅርቧል፡፡ አንደኛው ከፍተኛው ፍ/ቤት በሚሰጠው ውሳኔ በቴምብር ቀረጥ ድንጋጌ ለግብር ከፋዩ ሆነ ለግብር አስገቢው ባለስልጣን ለጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ መብት ስላልሰጠ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ይግባኙን ለማየት ሥልጣን የለውም፡፡ ሁለተኛው ክርክር ግብር አስገቢው ባለስልጣን በሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ የሚቻለው በተወሰነው የቀረጥ ሒሳብ ወይም መጠን ላይ ነው የሚል ነው፡፡ እነዚህ

የመከራከሪያ ነጥቦች እንዴት ይታያሉ? ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኙን የማየት ሥልጣን አለው የሚባል ከሆነ የይግባኝ ማቅረቢያው ጊዜ 21 ቀን ነው ወይስ በመደበኛው የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥረዓት ህግ የተደነገገው 60 ቀን ነው?

## 2.4. የታክስ ወንጀሎች

የታክስ ህግን መተላለፍ የፍትሐብሔር ሐላፊነት ብቻ ሳይሆን የወንጀል ተጠያቂነትን እንዲሚያስከትል የገቢ ግብር፣ ተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ተርን ኦቨር ታክስ፤ ኤክሳይዝ ታክስ እና የቴምብር ቀረጥ በሚጥሉ ህጎች ውስጥ ተደንግጓል፡፡ የወንጀል ተጠያቂነት ሊያስከተሉ የሚችሉና እንደ ታክስ ወንጀል የሚቆጠሩ ድርጊቶች እንደ ታክሶች አይነት መጠነኛ ልዩነቶች ቢኖራቸውም አብዛኞቹ ተመሳሳይ ናቸው፡፡ የታክስ ወንጀሎች በግብር ከፋይ እና በሌሎች ሰዎች ሊፈጸሙ ይችላሉ፡፡ ታክስ ከፋዩን የሚመለከቱ የታክስ ወንጀሎች ውስጥ ጥቂቶቹ፡፡-

**ሕግን በመጣስ ታክስን አለመክፈል ወይም አለማሳወቅ፡-** አንድ ታክስ ከፋይ በሕጉ በተደነገገው ጊዜ እና አኳኃን የሚፈለግበት ታክስ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡ ታክሱንም በትክክልና በሐቀኝነት ለግብር አስገቢው ባለስልጣን ማሳወቅ አለበት፡፡ እነዚህን ግዴታዎች አለመወጣት ወይም ገቢን አሳንሶ ማሳወቅ የወንጀል ተጠያቂነትን ያስከትላሉ፡፡

**የሀሰት ወይም አሳሳች መረጃን ማቅረብ፡-** ታክስ ከፋይ ለግብር አስገቢው ባለስልጣን ትክክለኛ መረጃ የማቅረብ ወይም የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ለግብር አሰገቢው ባለስልጣን ሰራተኛ አንዱን ነጥብ በተመለከተ የሀሰት ወይም አሳሳች መረጃ ያቀረበ ወይም ሊቀርብ ከሚገባው መግለጫ ውስጥ መግለጫውን አሳሳች ሊያደርግ በሚችል አኳኃን መካተት የሚገባቸውን ነጥቦች የስቀረ እንደሆነ በወንጀል ይጠየቃል፡፡

**የታክስ ባለስልጣን ሥራ ማሰናከል፡-** የታክስ አስገቢው ባለስልጣን የታክስ ከፋዩን የስራ እንቅስቃሴዎች የሚመለከቱ ሰነዶችን፣ ሪፖርቶችን ወይም ሌሎች ማናቸውንም መረጃዎች የመመርመር ሥልጣን አለው፡፡ ለዚህ ሥራ ታክስ ከፋዩ በግብር አስገቢው ባለስልጣን ፈቃደኛ ሆኖ አለመገኘት በወንጀል ያስቀጣል፡፡ የግብር አስገቢው ባለስልጣን ተገቢውን ተግባሩን ለማከናወን ታክስ ከፋዩን ለጥያቄ እንዲቀርብ ሊያዘው ይችላል፡፡ ታክስ ከፋዩ ለዚህ ፋቃደኛ ሆኖ መገኘት አለበት፡፡ በተጨማሪም የግብር አስገቢው ባለስልጣን ሰራተኛ ወደ ታክስ ከፋዩ የንግድ

ቦታ በመግባት አስፈላጊውን ምርመራ ለማከናወን መብት አለው፡፡ ታክስ ከፋዩ ይህን መብት በመገደብ በሥራው ላይ መሰናክል መፍጠር የለበትም፡፡ ይህን አድርጎ ቢገኝ ታክስ ከፋዩን በወንጀል ያስቀጣዋል፡፡

**ለውጥን ያለማስታወቅ፡-** ለውጥን ያለማሳወቅም በወንጀል ያስጠይቃል፡፡

**ከአንድ በላይ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር መያዝ፡-** አንድ ታክስ ከፋይ አንድ የግብር መክፈያ መለያ ቁጥር ብቻ መያዝ ይጠበቅበታል፡፡ ከአንድ በላይ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር መያዝ በወንጀል ያስጠይቃል፡፡

**የማይገባው ተመላሽ ታክስ መጠየቅ፡-** ተጨማሪ እሴትን በተመለከተ መንግስት ለማጭበርበር በማሰብ የማይገባውን ተመላሽ ታክስ መጠየቅ በወንጀል ያስጠይቃል፡፡

**የቴምብር ቀረጥ በተመለከተ፡-** የቴምብር ቀረጥ ሕግን መተላለፍ የወንጀል ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡ አንድ ሰው ቀረጥ ሊከፈልበት የሚገባውን ሰነድ ተገቢውን ቴምብር ሳይለጠፍበት ያስፈፀመ ወይም ከምስክርነት በስተቀር የፈረመ እንደሆነ እንዲሁም ተገቢውን ቀረጥ እንዳይከፍል ለማድረግ ለማሰብ የአንድን ሰነድ እውነተኛ ሁኔታ የደበቀ እንደሆነ በወንጀል ይጠየቃል፡፡ በተጨማሪ አንድ ቴምብር ወይም ቴምብር የተለጠፈበት ወረቀት ለመሸጥ ሳይፈቀድለት የሸጠ ወይም ለመሸጥ ያቀረበ እንደሆነ በወንጀል ሊጠየቅ ይችላል፡፡

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ለታክስ ወንጀሎች መንሴኤ ናችው የምትሉትን ዘርዝሩ፡፡ የታክስ ህጉ ራሱ ለታክስ ወንጀሎች አስተዋጾ ሊኖረው ይችላል? እንዴት?
2. በታክስ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች የልማት እና የእድገት ጠንቅ ናቸው፡፡ እንዴት? ወንጀሎችን ለመከላከል ሊወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎች ምንድናቸው? በዚህ ረገድ ከእናተ ሰልጣኞች ምን ይጠበቃል?

## 2.5. የታክስ ይርጋ

ቀደም ሲል እንዳየነው የገቢ ግብር፣ተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ተርን ኦቨር ታክስ እና ኤክሳይዝ ታክስ ታክስ ከፋዩ በሚያቀርበው ማስታወቂያና ሌሎች መረጃዎች መሰረት ሊወሰኑ ይችላሉ። ሆኖም ግን ታክስ ከፋዩ በሚያቀርበው የታክስ ማስታወቂያ ወይም መረጃ መሰረት የሚከፈለው ታክስ የመጨረሻ አይደለም። ታክስ አስገቢው ባለስልጣን በታክስ ከፋዩ ራሱ ተሰልቶ የቀረበውን ወይም የተከፈለውን ታክስ የማጣራት ሥልጣን አለው። በማጣራቱም ሒደት ታክሱ ስህተት ወይም ያልተካተተ ገቢ ያለ መሆኑ የተረጋገጠ ከሆነ ባለስልጣኑ ያቀረበውን ታክስ ወይም ማስታወቂያ አስተካክሎ ታክሱን የመወሰን ሥልጣን አለው። የተስተካከለው ወይም የተሻሻለው የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያው ለታክስ ከፋዩ ሊደርሰው ይገባል። ታክስ አስገቢው ባለስልጣን ታክስ ከፋዩ ያቀረበውን የታክስ ማስታወቂያ ወይም የከፈለውን ታክስ እንደገና በማጣራት ውሳኔ መስጠት የሚችለው በምን ጊዜ ውስጥ ነው?

ከላይ የተጠቀሱትን የታክስ አይነቶች የሚጥሉ አዋጆች ውስጥ በግልፅ እንደተመለከተው አንድ ታክስ ከፋይ በሕጉ በተደነገገው ጊዜ ውስጥ እና ሕጉ በሚያዘው አኳኃን የታክስ ማስታውቂያን ያቀረበ ሆኖ ማስታወቂያውን ያቀረበው ግን ታክሱን ለማስታወቅ ከተወሰነው ጊዜ በኃላ ከሆነ ግብር አስገቢው ባለስልጣን የቀረበውን ማስታወቂያ አስተካክሎ ታክሱን መወሰን የሚችለው በአምስት አመት ጊዜ ውስጥ ነው። ይህ አምስት አመት ጊዜ ገደብ መቆጠር የሚጀምረው ታክስ ከፋዩ በሕጉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥና አኳኃን ታክስ ማስታወቂያውን ያቀረበ ከሆነ የታክስ ማስታወቂያው መቅረብ ካለበት የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ሲሆን ታክስ ከፋዩ የታክስ ማስታወቂያውን ማቅረብ ከነበረበት ጊዜ በኂላ ያቀረበ ከሆነ ደግሞ የግብር አስገቢው ባለስልጣን የታክስ ማስታወቂያውን ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ ይሆናል።

በሌላ በኩል ታክስ ከፋዩ ታክሱን ያላሳወቀ ወይም የተጭበረበረ የታክስ ማስታወቂያ ያቀረበ ከሆነ የግብር አስገቢው ባለስልጣን በማናቸውም ሌላ ህግ የተደነገገው ይርጋ ሳያግደው ግብሩን በማናቸውም ጊዜ መወሰን ይችላል። ስለዚህ በሕጉ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ታክሱን ያላሳወቀ፣የገቢውን ሙሉና ትክክለኛ መግለጫ ያላቀረበ ወይም የሐሰት መግለጫ ለግብሩ ባለስልጣን ያቀረበ ግብር ከፋይ ያለምንም የጊዜ ገደብ በማናቸውም ጊዜ ተጨማሪ የግብር ውሳኔ ሊተላለፍበት ይችላል። በሌላ አባባል በሕጉ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ታክሱን ያላሳወቀ፣የገቢውን ሙሉና ትክክለኛ መግለጫ ያላቀረበ ወይም የሐሰት መግለጫ ለግብሩ

ባለስልጣን ያቀረበ ግብር ከፋይ በህጉ የተቀመጠውን የአምስት አመት ይርጋ ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም ማለት ነው፡፡ ይልቁንም ይህ አይነቱ ታክስ ከፋይ ታክሱን ባለማሳወቁ ወይም የሐሰት መግለጫ በማቅረቡ ወይም ታክሱን ለማስለት የሚያስችል መረጃ ለማቅረብ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ቅጣት ይጠብቀዋል፡፡

ቀደም ሲል ሲሰራባቸው በነበሩት ሕጎች ታክስን ለማየት ሥልጣን ባላቸው አካላት ዘንድ የታክስ ይርጋን በተመለከተ የተለያዩ ውሳኔዎች ሲሰጡ ቆይተዋል፡፡ የተለያዩ ውሳኔዎች መሰጠት ምክንያት የነበረው ይርጋን በተመለከተ የተደነገጉ ድንጋጌዎች ለትርጉም የተጋለጡ መሆናቸውን ነበር፡፡ ይህ ችግር አሁን መፍትሔ ያገኘ ይመስላል፡፡

ለማጠቃለል በአምስት አመት ይርጋ ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው ታክሱን በማሳወቅ ግዴታውን የተወጣ ታክስ ከፋይ ብቻ ነው፡፡ ታክሱን ያላሳወቀ ወይም የተጭበረበረ የታክስ መስታወቂያ ያቀረበ ታክስ ከፋይ በተመለከተ የታክስ ግዴታውን በይርጋ አይታገድም፡፡

**የመወያያ ጥያቄ**

በተወሰነ ጉዳይ ካልሆነ የታክስ ግዴታን በይርጋ ቀሪ እንዳይሆን ከማድረጉ በስተጀርባ ያለው ምክንያት ምንድነው?

## ክፍል ሶስት

## የታክስ ይግባኝ ሥርዓት እና አሰባሰብ አፈፃፀም

*መግቢያ*

የታክስ ህግ በታክስ ከፋዮች ላይ የተለያዩ ግዴታዎችን ይጥላል፡፡ አንዱ ግዴታም ሕጉ ባስቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ታክሱን መክፈል ነው፡፡ የታክስ በመወሰን እና በመሰብሰብ ረገድም ግብር አስገቢው ባለስልጣን ሰፊ የሆነ ሥልጣን አለው፡፡ በሌላ በኩል ታክስ ከፋዮች የታክስ ባለሥልጣኑ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካላቸው ቅሬታቸውን አቅርበው የሚያስሙበትና ፍትህ የሚያገኙበት ሥረዓትም ተዘርግቷል፡፡ እንዲሁም አንድ ታክስ ከፋይ መክፈል ያለበትን ታክስ በሕጉ በተቀመጠው ጊዜ ገደብ ውስጥ በመክፈል ግዴታውን ካልተወጣ ግብር አስገቢው ባለስልጣን ታክሱን እንዴት አድረጎ እንደሚሰበስብ በሕጉ ተመልክቷል፡፡ በዚህ ክፍል የምንመለከተው እነዚህን ሁለት ነጥቦች ይሆናል፡፡

ይህን ክፍል ሲያጠናቅቁ ሰልጣኞች፡-

- ስለ ግብር አጣሪ ኮሚቴ እና የግብር ይግባኝ ጉባኤ አወቃቀርና ሥልጣን በቂ ግንዛቤ ይጨብጣሉ፡፡
- ስለገቢ ግብር፣ተጨማሪ እሴት ታክስ፣ተርን ኦቨር ታክስ እና ኤክሳይዝ ታክስ የይግባኝ ሥረዓት በቂ ግንዛቤ ይኖራቸዋል፡፡
- የግብር ይግባኝ ጉባኤ ከፍ/ቤቶች ጋር ስላለው ግንኙነት ያብራራሉ፡፡
- ታክስን በተመለከተ የፍ/ቤቶች ሥልጣን ወሰን ጠንቅቀው ይረዳሉ፡፡
- ታክስ የታክስ ከፋዩን ሀብት በመያዝ የሚሰበሰቡትን ሁኔታ ይረዳሉ፡፡

**ይግባኝ ሥርዓት**

የገቢ ግብር፣ ተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ተርን ኦቨር ታክስ እና ኤክሳይዝ ታክስ የይግባኝ አቀራረብ ሥረዓት ተመሳሳይ መሆኑን ታክሶችን ከሚጥሉ ህጎች መረዳት ይቻላል፡፡ በታክስ ባለስልጣኑ የሚሰጡ የታክስ ውሳኔዎች ሁሌም የመጨረሻ እንዳልሆኑ በህጎቹ ተመልክቷል፡፡ ባለስልጣኑ በሰጠው ውሳኔ ቅሬታ የተሰማው ታክስ ከፋይ ቅሬታውን እንደሁኔታው ለአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ወይም ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ማቅረብ ይችላል፡፡

**3.1.1. አቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ**

የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ አባላት በታክስ ባለስልጣኑ ኃላፊ አቅራቢነት እንደ አግባብነቱ በገቢዎች ሚኒስትር ወይም አግባብ ባለው የክልል ባለስልጣን የሚሰየሙ ናቸው፡፡

የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ በግብር ከፋዮች መቀጫ እንዲነሳ፣ ወለድ ቀሪ እንዲደረግ ወይም የግብር ግዴታ እንዲሻሻል የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን መመረመርና የውሳኔ የመስጠት ሥልጣን አለው፡፡ ለዚህም ማናቸውንም የጽሑፍ ማስረጃዎች ወይም መረጃዎች የመሰብሰብ እንዲሁም ለማጣራት ማንኛውንም ሰው መጥራትና መጠየቅ ይችላል፡፡ በተጨማሪም ኮሚቴው የግብር አስገቢው ባለስልጣን የሰጠው የግብር ውሳኔ ትክክለኛ የተሟላ እና ታክሱን የሚጥለውን አዋጅ ጠብቆ የተሰጠ መሆኑን የማረጋገጥ ሥልጣን አለው፡፡

እንዲሁም ምስክር ወረቀት በመከልከል ወይም ንግድ ፈቃድ በመሰረዙ ግብር አስገቢው ባለስልጣን በሰጣቸው ምክንያቶች ቅር የተሰኘ ግብር ከፋይ ቅሬታውን ለአጣሪ ኮሚቴ ማቅረብ ይችላል፡፡(የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 41(2))

አጣሪው ኮሚቴ ከግብር ከፋዮች የሚቀርበውን አቤቱታ ሊያይ የሚችለው ግብር ከፋዩ የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ በደረሰዉ በአስር ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ካቀረበ ነው፡፡

የአጣሪው ኮሚቴ ውሳኔ ተፈፃሚነት የሚኖረው የውሳኔ ሃሳቡ በግብር አስገቢው ባለስልጣን ኃላፊ ከፀደቀ ነው፡፡ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ኃላፊ ኮሚቴው ባቀረበው ሃሳብ ካልተስማማ ምክንያቱን በመግለጽ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ለኮሚቴው ሊመልሰው ይችላል፡፡

በመጨረሻም መቀጮውን ማንሳትን በተመለከተ ኮሚቴው የገቢዎች ሚኒስትር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በግብር ከፋዩ ላይ የተጣለው አስተዳደራዊ መቀጮ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲነሳ ማድረግ ይቻላል፡፡

### 3.1.2. ግብር ይግባኝ ጉባኤ

በግብር አስገቢው ባለስልጣን የግብር ውሳኔ ላይ ይግባኝ የሚቀርበው ለግብር ይግባኝ ጉባኤ ነው፡፡ ግብር አስገቢው ባለሥልጣን የሚሰጠው የግብር ውሳኔ ማለት የሚፈለገውን ፍሬ ግብር ብቻ ሳይሆን ግብር ከፋዩ ወይም ግብርን ከተከፋይ ሒሳብ ቀንሶ ገቢ የማድረግ ግዴታ ያለበት ሰው ግዴታውን ባለመወጣቱ የሚጣለውን አስተዳደራዊ መቀጮንም የሚጨምር ነው፡፡

የግብር ይግባኝ ጉባኤዎች እንደ አስፈላጊነታቸው በፌዴራል ደረጃ የፌዴራል የግብር ይግባኝ ጉባኤ፣ በእያንዳንዱ የክልል ዋና ከተማ የክልል የግብር ይግባኝ ጉባኤ፣ በእያንዳንዱ የዞን ዋና ከተማ የዞን የግብር ይግባኝ ጉባዔና በእያንዳንዱ የወረዳ አስተዳደር ከተማ የወረዳ የግብር ይግባኝ ጉባኤ እንደሚቋቋሙ ተደንግጓል፡፡ የፌዴራል የግብር ይግባኝ ጉባኤ ተጠሪነቱ ለፍትህ ሚኒስትር ሲሆን ሌሎቹ በየደረጃው ላሉት የስራ አስፈፃሚ አካላት ነው፡፡

ግብር አስገቢው ባለስልጣን በሚሰጠው የግብር ውሳኔ ቅር የተሰኘ ግብር ክፋይ ለግብር ይግባኝ ጉባኤ ይግባኝ ለማቅረብ በሕጉ የተዘረዘሩትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት ይጠበቅበታል፡፡ እነዚህም ቅድመ ሁኔታዎች ሁለት ናቸው፡፡ አንደኛው አካራካሪ የሆነውን የግብር መጠን አምሳ በመቶ ለግብር አስገቢው ባለስልጣን ማስያዝ ነው፡፡ ሁለተኛው የይግባኝ ማቅረብያ ጊዜን የሚመለከት ሲሆን ግብር ከፋዩ የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ ከደረሰው ወይም በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ውሳኔ በተሰጠ በሰላሳ ቀን ውስጥ ይግባኙን ማቅረብ አለበት፡፡ እነዚህን ሁኔታዎች ያላሟላ ይግባኝ በይግባኝ ጉባኤ ተቀባይነት የለውም፡፡ ይግባኙ የቀረበበት ቀን የሚባለውም ይግባኙ በቀጥታ ለይግባኝ ጉባኤው የቀረበ ከሆነ ይግባኝ በመዝገብ ቤት የተመዘገበበት ቀን ሲሆን ይግባኝ በሪኮማንዴ የተላከ ከሆነ ደግሞ በፖስታ ቤት ተመዘገበበት ቀን ይሆናል፡፡

የታክስ ባለሥልጣን በሚሰጠው የታክስ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ሊያቀርብ የሚችለው ታክስ ከፋዩ ወይም ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ታክስ ቀንሶ ገቢ የማድረግ ሐላፊነት ያለበት ሰው ሊሆን ይችላል፡፡ የታክስ ባለስልጣኑ ለግብር ይግባኝ ጉባኤ ይግባኝ የሚልበት ሁኔታ አይኖርም፡፡

ታክስ ከፋዩ የሚያቀርበው የይግባኝ ማመልከቻም የይግባኝ ፍሬ ነገር እና የይግባኝ ምክንያቶች የግብር ከፋዩን ስም፣ አድራሻ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ ኣባሪ ሰነዶችና ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን መያዣ የተከፈለበት ደረሰኝ ፎቶ ኮፒ የያዘ መሆን አለበት፡፡ ከእነዚህ ውስጥ አንዱ ቢጎድል የይግባኝ ጉባኤው ይግባኝ ባይ የተባለውን ጉድለት እንዲያሟላ ይጠይቀዋል፡፡ ይግባኝ ባይ በአምስት ቀኖች ውስጥ የተባለውን ጉድለት ማስተካከል አለበት፡፡ ያላስተካከለ እንደሆነ የቀረበው የይግባኝ ማመልከቻ ወዲያውኑ ውድቅ ይሆናል፡፡

የይግባኝ መስማት ሒደትም በተመለከተ ታክስ ከፋዩ የሚያቀርበው ይግባኝ ከማሰማቱ በፊት የይግባኙ ማመልከቻ ግልባጭ ለግብር አስገቢው ባለስልጣን ደርሶ መልስ እንድሰጥበት መደረግ አለበት፡፡ ይግባኝ ባይ በሁለት የቀጠሮ ጊዜ ሳይገኝ የቀረ እንደሆነ ወይም ይግባኙን ካቀረበ በኃላ የመልስ መልስ ሳያቀርብ ቢቀር ወይም የግብር አስገቢው ባለስልጣን የይግባኝ ማመልከቻ ከደረሰው በኃላ በሁለት የቀጠሮ ጊዜዎች ሳይገኝ የቀረ እንደሆነ ወይም ለይግባኙ መልስ ሳይሰጥ ቢቀር ተከራካሪው ወገን በሌለበት ውሳኔ ይሰጣል፡፡

ግብር ይግባኝ ጉባኤ የግብር አስገቢው ባለስልጣን ውሳኔ የውሳኔው ይዘት ምን መያዝ እንዳለበት በሕጉ ተመልክቷል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤም የግብር ውሳኔ የማፅናት፣ የመቀነስ ወይም የመሰረዝ ሥልጣን አለው፡፡ ጉባኤው የፍሬ ነገር እና የሕግ ስህተት የማረም ሥልጣን አለው ማለት ነው፡፡

### 3.1.3. ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት

የይግባኝ ጉባኤ የሰጠው ውሰኔ በሕግ ረገድ ስህተት አለበት የሚል ወገን ይግባኙን ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት የማቅረብ መብት አለው፡፡ ሆኖም ግን ይግባኝ ባዩ ይግባኙን ለማቅረብ ሁለት ግዴታዎች ሟሟላት ይጠበቅበታል፡፡ አንደኛው ጉባኤው ውሳኔ በተሰጠ ሰላሳ ቀን ውስጥ ይግባኙን ማቅረብ ነው፡፡ ሁለተኛው ይግባኝ ጉባኤው የተወሰነበትን ሙሉ ግብር መክፈል ነው፡፡ ይግባኝ የቀረበለት ፍ/ቤቱም ያለው ሥልጣን በሕግ ረገድ የተወሰነውን ክርክር ብቻ ተመልክቶ ውሳኔ ከሰጠ በኃላ ጉዳዩን ወደ ጉባኤው መመለስ ነው፡፡

ፍ/ቤቱም በሚሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ተከራካሪ ወገን አሁንም በደረጃው ቀጥሎ ለሚገኘው ፍ/ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት ተሰጥቶታል፡፡ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የመጀመሪያው

ፍ/ቤት በይግባኝ ያየውን ጉዳይ ብቻ የሚያይ ነው፡፡ ይግባኝ ባዩም ውሳኔው በተሰጠ ሰላሳ ቀን ውስጥ ይግባኙን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ነጥብ ከሌሎች የይግባኝ ሥርዓቶች በተለየ ሁኔታ ወደ መደበኛ ፍ/ቤቶች ይግባኝ የቀረበ እንደሆነ ጉዳዩ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ቀርቦ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ አፈፃፀሙ የማይታገድ መሆኑ ነው፡፡ በጉባኤው ውሳኔ መሰረት ታክሱ የሚከፈል ይሆናል፡፡ ለዚህ ሕጉ ታክስ ከፋዩ የሰጠው ብቸኛ መፍትሔ ቢኖር የታክሱ ውሳኔ በመጨረሻው ይግባኝ ፍ/ቤት የተሻሻለ ወይም የተለወጠ እንደሆነ ከሚገባው በላይ የተከፈለው እንዲመለስለት ማድረግ ነው፡፡

ሌላው መታየት ያለበት ነጥብ ደግሞ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ሥልጣን ወሰን ነው፡፡ ከግብር ይግባኝ ጉባኤ ላይ የሚቀርበውን ይግባኝ የሚያይ ፍ/ቤት ሥልጣኑ የተገደበ ነው፡፡ የፍ/ቤቱ ሥልጣን በሕግ ረገድ ተፈፅሟል የተባለውን ስህተት በማቃናት ጉዳዩን ወደ ጉባኤው መላክ እንጂ በታክስ አወሳሰን የግምት ሥራ ውስጥ መግባት እንደሌለበት በአዋጆቹ ተመልክቷል፡፡ ጥያቄው ታዲያ በሕግና በፍሬ ነገር ሥራ መሀል ያለውን የልዩነት መስመር እንዴት ማስመር ይቻላል የሚለው ነው፡፡

ታክስን በተመለከተ ለፍ/ቤት ከሚቀርቡት ይግባኞች መረዳት እንደሚቻለው በይግባኝ ቅሬታነት አዘውትረው የሚቀርቡት ታክስ የተጠየኩት በማይመለከተኝ ሥራ ነው፤ የተተመነብኝን ገቢ ሰርቼ ያላገኘሁት ነው፣ ያቀረብኩት የሂሳብ መዝገብ በአግባብ የተያዘ ሆኖ ሳለ የታክስ ባለስልጣኑ ባለመቀበል ታክሱን በግምት ወሰነብኝ፣ ሊቀነሱ የሚገባቸው ሂሳቦች አልተቀነሱልኝም፣ ታክሱ በይርጋ ታግዶ ሳለ መጠየቁ ያለአግባብ ነው፣ ቁርጥ ግብር ከፋይ ስለሆንኩ የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ የለብኝም፣ ታክስ የተጠየኩበትን ሥራ አልሰራሁም ወይ ሥራውን አቋርጫለሁ፤ የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ በአግባቡ እንዲደረሰኝ አልተደረገም፣ የተጣለብኝ መቀጫ አይመለከተኝም፣... ወዘተ የሚሉ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ የትኛው የሕግ የትኛው ደግሞ የፍሬ ነገር ጥያቄ ነው የሚለውን መመለስ አስቸጋሪና አንዳንዴም የሚያወዛግብ ሥራ ነው፡፡

ቀደም ሲል በነበሩት ህጎች መሰረት ከተሰጡት ውሳኔዎች መረዳት እንደሚቻለው በአንዳንድ ፍ/ቤቶች የፍሬ ነገር (fact) እንጂ የሕግ ስህተት አይደሉም ተብለው የተጣሉ ጉዳዮች በሌሎቹ ክርክር ሲካሔድባቸው ይታያሉ፡፡

በሚቀርበው የታክስ ይግባኝ ክርክር ውስጥ የትኛው የሕግ ወይም ደግሞ የፍሬ ነገር ጥያቄ ነው ለሚለው ወሰን ማበጀት አዳጋች ቢሆንም የፍሬ ነገር ክርክር የአንድ ነገር መኖርና አለመኖር ጋር የተያያዘ ሲሆን የህግ ክርክር ደግሞ በሕግ ድንጋጌዎች አፈጻጸምና ትርጉም ጋር የተያያዘ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ግራ ቀኙን የሚያከራክረው ነጥብ የአንድ ነገር መኖር ወይም አለመኖር ከሆነ የዚህ አይነቱ የፍሬ ነገር ተከራካሪ ወገኖች በሚያቀርቡት የማስረጃ ክብደት የሚወሰን ይሆናል፡፡

ታክስ ከፋዩ ነጋዴ መሆን አለመሆኑ፣ ታክስ ከፋዩ ትክክለኛ ስራ ፍቃድ ያለው መሆን አለመሆኑ፣ ታክስ ከፋዩ በተወሰነ ጊዜ የንግድ ሥራ ማከናወን አለማከናወኑ፣ታክሱን ማሳወቅ አለማሳወቁ፣ ታክሱን በጊዜ መክፈል አለመክፈሉ፣ የሒሳብ መዝገብ መያዝ አለመያዙ እና የመሳሰሉት የፍሬ ነገር ክርክሮች ናቸው ለማለት ይቻላል፡፡ እነዚህን ጭብጦች በማስረጃ ሊነጥሩ የሚችሉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ አንድ ታክስ ከፋይ የንግድ ሥራ ማከናወኑን የታክስ ባለስልጣኑ የተባለው ሰው ገቢ በሚያስገኝ ሥራ ላይ መሰማራቱን ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡ ይህ የሕግ ትርጉም አይጠይቅም፡፡ በሌላ በኩል ገቢው የተገኘው ከመቀጠር ነው ወይስ ከንግድ የሚለው የሕግ ክርክር የሚያስነሳ ነው፡፡ ስለዚህ የግብር ከፋዮች መብት ላለማጣበብ እያንዳንዱን ጉዳይ በጥልቀት መመርመር አስፈላጊ ይሆናል፡፡

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ሥልጣን ምንድነው? አንድ ታክስ ከፋዩ የተጣለበትን መቀጮ ወይም ወለድ ላይ ቅሬታ ካለው ቅሬታውን ለአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ሳያቀርብ ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ማቅረብ ይችላል?
2. አብዛኞዎቹ ግብር ከፋዮች ግብሩን ለማዘግየት ባላቸው ዓላማ ምክንያት ያለበቂ ምክንያት ለአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ አቤቱታ ስለሚያቀርቡ አቤቱታ

አጣሪ ኮሚቴ ቢቀር ወይም የኮሚቴው ሥልጣን ቢገደብ የሚል ጥያቄ ለግብር አስገቢው ባለስልጣን ጥያቄ እያቀረቡ ነው፡፡ ለአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ መኖር ጥቅሙና ጉዳቱ ምንድነው? ለሚነሳው ችግርስ መፍተሔው ምንድነው ትላላችሁ?

3. የግብር ይግባኝ ጉባኤ በሚሰጠውን ውሳኔ ላይ የሚቀርበውን ይግባኝ ማየት ሥልጣን ያለው የትኛው ፍ/ቤት ነው?
4. አንዳንድ ሰዎች አንድ ታክስ የተወሰነበት ታክስ ከፋይ የተወሰነበትን ታክስ ሙሉ በሙሉ ለግብር አስገቢው ባለስልጣን እንዲያሲዝ ማድረግ ይግባኝ መብትን እንደ መከልከል ይቆጠራል ይላሉ፡፡ ይሔ እንዴት ይታያል?
5. የግብር ይግባኝ ጉባኤ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ የተሰማው ተከራካሪ ወገን ውሳኔው በተሰጠ 30 ቀን ውስጥ ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይግባኝ ለማለት እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ የግብር ይግባኝ ጉባኤ ውሳኔ ከተሰጠ በኃላ ውሳኔውን ግልባጭ ለመስጠት ጊዜ እንደሚጠይቅ ይታወቃል፡፡ ስለዚህ በጊዜ ይግባኙ ተገልብጦ ያልተሰጠው ታክስ ከፋይ ለምን በዚህ ጊዜ ገደብ ተጎጂ ይሆናል? የአንድ ወሩ ጊዜ ቢያልፍ ይግባኝ ባይ ያለው መፍትሔ ምንድነው?
6. የይግባኝ ጊዜ አቆጣጠርን በተመለከተ የግብር ማስታወቂያ የተሰጠበት ቀን ከሰላሳ ቀን ውስጥ ገብቶ ይታሰባል ወይስ አይታስብም? በዘህ ነጥብ ላይ ግብር ሰሚ ጉባኤ ሆነ ፍ/ቤቶች ዘንድ ተመሳሳይ አቋም እንደሌለ በእነዚህ አካላት ከተሰጡ ውሳኔዎች መረዳት ይቻላል፡፡ ውሳኔዎቹ ቀደም ሲል በነበረው የገቢ ግብር አዋጅን መሰረት የተሰጡ ናቸው፡፡ ሆኖም ግን የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜን በተመለከተ ሁለቱ ህጎች ተመሳሳይ ስለሆኑ ውሳኔዎቹ ማየቱ አሁንም አግባብነት ይኖረዋል፡፡ ከተሰጡት ውሳኔዎች ውስጥ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ ባይ፡-የዞን ፋይናስ ጽ/ቤት (የቦሌ ክ/ከተማ) ገቢዎች መምሪያ እና መልስ ሰጭ ሐይለማርያም ወርቁ መካከል በነበረው ክርክር ላይ የተሰጠውን ውሳኔ እንመልከት፡፡ ጉዳዩም ባጭሩ የግብር ውሳኔ ማስታወቂያው ለመልስ ሰጪ ሰኔ 15 ቀን 1990 ደረሰው፡፡ መልስ ሰጪ ይግባኙ ደግሞ ሐምሌ 15 ቀን 1990 ለግብር

ይግባኝ ጉባኤ አቀረበ፡፡ ግብር ይግባኝ ጉባኤውም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ይግባኙ የቀረበው የይግባኝ ማቅረቢያው ጊዜ ካለፈ በኋላ በመሆኑ ሊስተናገድ አይችልም በማለት ይግባኙን ሰርዛአል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት ከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ የጉባኤውን ውሳኔ በመሻር ይግባኙ ይታይ በማለት ወስኖአል፡፡

ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በአብላጫ ድምጽ የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር በግብር ይግባኝ ጉባኤ ውሳኔ መሰረት እንዲፈጸም አዟል፡፡ ውሳኔውም..... ለይግባኝ መቅረቢያ የተወሰነው 30(ሰላሳ) ቀን ፣ቆጠር የሚጀምረው የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ(ጀምሮ) ነው፡፡ ይህ ማለት የግብር ውሳኔ ማስታወቂያው ተሰጠበት ቀንም ከሰላሳው (30) ቀን ውስጥ ገብቶ ይታሰባል ማለት ነው፡፡ ሕጉ ይህን ያህል ግልጽ ከሆነ ስላለው አፈፃፀም በተመለከተ በፍትሐብሔር ህጉ የተደነገገው የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር ወደሚመለከተው ድንጋጌ የምንሄድበት ምክንያት የለም፡፡ በግብር ሕጉ መሰረት ጊዜው ሲሰላ ከ30(ሰላሳ) ቀን በላይ አልፎአል፡፡ በመሆኑም የይግባኝ ጊዜው አላለፈም በማለት ከመልስ ሰጭው የቀረበውን ክርክር አልተቀበልነውም፡ :......ስለዚህ ይግባኝ የተባለበትን ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ-ሥ/ ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት በመሻር የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ መሰረት ይፈጸም.... የሚል ነው፡፡

ሐሳብ የተለዩት ዳኛ ደግሞ....... የግብር ሕጉ ይግባኝ ላማቅረብ 30 ቀን ፈቅዷል፡፡ ይኸው የ30 ቀን ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው የግብር ማስታወቂያ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ እንደሆነ ህጉ ያዛል፡፡ ሆኖም ይ የህግ አቀራረጽ የተለመደውን የሕግ አተረጓጎም ባልተከተለ ሁኔታ ይተረጉማል የሚል እምነት የለኝም፡፡ ማስታወቂያው የተሰጠበት ቀን በይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ውስጥ የሚጠቃለል ከሆነ ለይግባኝ መቅረቢያ ጊዜ 30 ቀን ተሰጠ ማለት የሚቻለወም አይመስለኝም፡፡ ማስታወቂያው በማናቸውም የስራ ሰዓት የሚሰጥ በመሆኑ ቅሬታ ያለው ሰው በ30 ቀን ውስጥ ይግባኝ እንዲያቀርብ

የፈቀደ ሕግ መልሶ መብቱን ሊያጣብብ በሚችል መልኩ የአቆጣጠር ሥረዓት የሚያስቀምጥ አልመሰለኝም፡፡ በሌሎች ሕጎች ያለው የቀን አቆጣጠር ሥርዓት በግብር ሕግ አይሰራም ለማለት የሚያስችል በቂና አሳማኝ ምክንያት የለም፡፡ በዚህ ምክንያት የግብር ማስታወቂያ የተሰጠበት ቀን ከሰላሳው ቀን ውስጥ መታሰበ ይገባል በማለት በአብዛኛው ድምፅ በተሰጠው የህግ ትርጉም ባለመስማማት ይግባኝ የተባለበት ውሳኔ መሻር አልነበረበትም የሚል የሀሳብ ልዩነት አቅርቤአለሁ........በማለት ልዩነታቸውን አስፍረዋል፡፡

ሀ. ይህ ውሳኔ እንዴት ይታያል? ሚዛን የሚደፋው የትኛው መስመር ነው?

ለ. በሌሎች ሕጎች ያለው የቀን አቆጣጠር ሥርዓት ለግብር ህግ ተፈጻሚነት አላው?

7. ይግባኝ ባይ፡-ብርሃኑ መሐሪ እና መልስ ሰጭ የዞን 2 ፋይናንስ ጽ/ቤት መካከል የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁጥር 1683/93 ውሳኔ ሰጥቷአል፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በግብር ይግባኝ ጉባኤ ሲሆን፤ የይግባኝ ባይ ክርክርም የንግድ ፈቃድ አውጥቼ ከምሰራው የንግድ ሥራ ውጪ ያለአግባብ የተጠየቅሁት ግብር ሊሰረዝልኝ ይገባል፤ግብር የተጠየኩበትን ሥራዎች አልሰራሁም የሚል ነው፡፡ ጉባኤው ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ፣... የይግባኝ ባይ የንግድ እንቅስቃሴ በመልስ ሽጭ መስሪያ ቤት እንስፔክተሮች ታይቶና ተረጋግጦ የቀን ገቢው ተጠንቶ ግብርና ታክሱ የተወሰኑ በመሆኑ ክርክሩ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ባይ ይግባኙን ለከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ በከፍተኛ ፍ/ቤት ላይ የመልስ ሰጭ ክርክር ግብርና ታክሱ የተወሰነው በመስሪያ ቤቱ ኢንስፔክተሮች በተደረገው ምርምራ ተረጋግጦ ነው፡፡ እንዲሁም በይግባኝ የቀረበው ክርክር የአነሰ በዛ እንጂ የሕግ ክርክር የሚያስነሳ ባለሞሆኑ ፍ/ቤቱ ከመሰረቱ ሊመረምረው አይችልም የሚል ነው፡፡

ይግባኝ የቀረበለት የከፍተኛው ፍ/ቤት ለይግባኙ መነሻ የሆነው ነጥብ የሕግ ሳይሆን፣ በማስረጃ የሚረጋገጥ የእውነታ ጭብጥ የሚያስነሳ ሆኖ አግኝቼዋለሁ የሚል ምክንያት በመስጠት ይግባኙን ሳይቀበል ቀርቷል፡፡

ሀ. የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ እንዴት ትመዝኑታላቸሁ?

ለ. ማስረጃን በተመለከተ የሚቀርበው ክርክር ከግብር ሕጉ አኳያ ሲታይ የህግ ክርክር ነው ወይስ አይደለም?

8. ግብር የሚከፈልበት ገቢ ሲታሰብ ከጠቅላላው የግብር ከፋዩ ገቢ ላይ ሊቀነሱ የሚገባቸው ወጪዎች ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ክርክሮች ከግብር ሕጉ አንጻር የህግ ክርክር ሊሆን ይችላሉ? ለምን?

**የታክስ አሰባሰብ አፈፃፀም**

ታክስ በሕግ የሚጣል ግዴታ መሆኑን፤እንዲሁም ታክስ የመጣሉ ሥልጣን የሕግ አውጭው አካል ብቻ እንደሆነ ቀደም ሲል ተመልክቷል፡፡ ሕግ አውጪው አካል ባለው ሥልጣን ታክስን መጣል ብቻ ሳይሆን የተጣለው ታክሱን ማን መሰብሰብ እንዳለበት እና እንዴት መሰብሰብ እንዳለበት መደንገግ ይጠበቅበታል፡፡ ሕግ አውጪው አካል የተጣለው ታክስ የሚሰበስብበትን ሥረዓት የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በሚያወጣው ህግ ውስጥ ማካተት ወይም አሰባሰቡን የሚመለከቱ ስነ ስርዓታዊ ህጎች ወይም ደንቦችን ማውጣት ይኖርበታል፡፡ ለዚህ አላማ የሚወጡ ህጎችም የሚጣለውን ታክስ መሰብሰብ የሚያስችሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

በመሰረቱ ታክስ የሚጣለው እና የሚሰበሰበው ከአጠቃላይ ጥቅም በመሆኑ አንድ ታክስ ከፋይ ሕጉ በሚያዘው መሰረት ታክሱን በመክፈል የዜግነት ግዴታውን መወጣት ይጠበቅበታል፡፡ ሆኖም ግን ሁሉም ይሔን ተገንዝቦ የታክስ ግዴታውን ይወጣል ማለት አይቻልም፡፡ ስለዚህ ሕጉ በሚያዘው መሰረት ግዴታቸውን በማይወጡ ታክስ ከፋዮች ላይ የሚፈለገውን ታክስ በሕግ በማስገደድ መሰብሰብ የግድ ይላል፡፡

በሐገራችን የገቢ ታክስ፣ተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ተርን ኦቨር ታክስ እና ኤክሳይዝ ታክስ በሚጥሉ አዋጆች ውስጥ አንድ ታክስ ከፋይ የታክስ ግዴታውን ባልተወጣ ጊዜ ታክስ አስገቢው

ባለስልጣን ታክሱን እንዴት በሕጉ አግባብ አስገድዶ መሰብሰብ እንዳለበት ተደንግጓል። መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎችን ተመልክተዋል።

### ሀ. የመጨረሻና ተፈጻሚነት ያለው የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ

ቀደም ሲል እንደተመለከተው የታክስ ባለስልጣኑ ታክሱን በሚወስንበት ጊዜ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያውን ለታክስ ከፋዩ ማድረስ ወይም መስጠት ይኖርበታል። የታክስ ውሳኔው ማስታወቂያው የደረሰው ታክስ ከፋይም በህጉ የተለያዩ አማራጮች የተቀመጡለት በመሆኑ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያው ሁል ጊዜ የመጨረሻና ተፈፃሚነት ያለው ላይሆን ይችላል። የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ የመጨረሻና ተፈፃሚነት ያለው ሊሆን የሚችለው፡-

- ታክስ ከፋዩ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ከመድረሱ ባሉት ሰላሳ ቀናት ውስጥ የሚፈለግበትን ታክስ ካልከፈለ ወይም
- አቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ውሳኔ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሰላሳ ቀናት ውሰጥ የሚፈለግበትን ታክስ ካልከፈለ ወይም
- ለግብር ይግባኝ ጉባዔ ይግባኝ ካላቀረበ ወይም
- ለግብር ይግባኝ ጉባዔ በሰጠው ውሳኔ ላይ ሕጉ በሚያዘው የጊዜ ገደብ ውስጥ ይግባኝ ካላቀረበ ወይም
- ይግባኝ ፍ/ቤቱም የመጨረሻው ውሳኔ ከሰጠ ነው።

በዚህ ሁኔታ የመጨረሻና ተፈፃሚነት ያለው የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ መሠረት የሚፈለግበትን ታክስ ያልከፈለ ታክስ ከፋይ ጥፋተኛ ነው። ታክስ አስገቢው ባለስልጣን ጥፋተኛ ከሆነው ታክስ ከፋይ ላይ የሚፈለገውን ታክስ አስገድዶ የመሰብሰብ ሥልጣን አለው። ይህን ሥልጣኑን ተጠቅሞ ታክሱን አስገድዶ ለመሰብሰብ የሚችለው የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያው የመጨረሻና ተፈፃሚነት ያለው ሲሆን ነው። ታክሱም የሚሰበሰበው የታክስ ከፋዩን ሀብት በመያዝ ነው።

### ለ. የታክስ ከፋዩን ሀብት መያዝ

የታክስ አስገቢውን ባለስልጣን ሥልጣን ታክስን በመወሰን ብቻ የተገደበ አይደለም። ሥልጣኑ ታክስን ከመወሰን አንስቶ በታክስ ውሳኔን እስከ ማስፈፀም የሚሔድ ነው። በዚሁ መሰረት የታክስ አስገቢው ባለስልጣን ጥፋተኛ በሆነው ታክስ ከፋዩ ላይ የሚፈለገውን ታክስ እና

ታክሱን ለመሰብሰብ የወጣውን ወጪ የታክስ ከፋዩን ሀብት (property) በመያዝ የማስፈፀም ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

ቀደም ሲል ሲሰራባቸው በነበሩት ህጎች አንድ ታክስ ከፋይ እንደ ታክስ ውሳኔው ካልፈጸመ ታክስ አስገቢው መስሪያ ቤት ፍርድ ቤት ሔዶ የአፈፃፀም መዝገብ መክፈት ይኖርበታል፡፡ ታክስ አስገቢው መስሪያ ቤት በራሱ ታክሱን አስገድዶ የመሰብሰብ ሥልጣን አልነበረውም ማለት ነው፡፡ በወቅቱ ሥራ ላይ የነበረው ሕግም የሚያዘው ይሄንኑ ነበር፡፡ የአሁኑ ህግ የሚያዘው ግን ቀደም ሲል ከነበረው የተለየ ነው፡፡ አሁን ሥራ ላይ ባለው ህግ ታክስ አስገቢው ባለስልጣን በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ የሚፈልገውን ታክስ ለመሰበሰብ ፍ/ቤት ሔዶ የሚከፈተው የአፈጻጸም መዝገብ የለም፡፡ የታክስ ውሳኔውን የሚያስፈፅመው ራሱ ነው፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው ታክስ አስገቢው ባለስልጣን የታክስ ውሳኔውን የሚያስፈፅመው የታክስ ከፋዩን ሀብት በመያዝ ነው፡፡ ለታክስ አፈፃፀም አላማ 'መያዝ' ማለት በማናቸውም መንገድ መያዝን እንዲሁም የታክስ ከፋዩ የሆነ ገንዘብ ወይም ንብረት በእጁ ከሚገኝ ሰው ታክስ መሰብሰብን እንደሚጨምር በህጉ ተመልክቷል፡፡ በዚህ መሠረት ታክስ አስገቢው ባለስልጣን ታክሱን ለመሰብሰብ የታክስ ከፋዩ በባንክ ቤት ያለውን ጥሬ ገንዘብ ወይም ከመቀጠር የሚያገኘው ገቢ ወይም የታክስ ከፋዩ የሚንቀሳቀስ ንብረት እንዲያዝ ማድረግ ይቻላል፡፡

ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘው ታክስ ከፋዩ ከመቀጠር የሚያገኘው ገቢ ያለው ከሆነ ታክስ አስገቢው ባለስልጣን ከተቀጣሪው ደመወዝ የመክፈል ኃላፊነት ላለበት ኃላፊ ማስታወቂያ በመስጠት እንዲያዝ ማድረግ ይቻላል፡፡ ባልተከፈለ የታክስ ምክንያት ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ለመያዝ የታክስ አስገቢው ባለስልጣን በመጀመሪያ መፈፀም ያለበት ግዴታ አለ፡፡ ይሔም ግዴታ ደመወዙን የመያዝ ሀሳብ እንዳለው አስቀድሞ ለታክስ ባለዕዳው በፅሑፍ ማስታወቅ ነው፡፡ ታክስ አስገቢው ባለስልጣን ይህን ማስታወቂያ ደመወዝ ከመያዙ ከሰላሳ ቀን በፊት ለታክስ ባለዕዳው እንዲደርሰው የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

የታክስ ባለዕዳውን ደመወዝ መያዝ ውጤትም በታክስ ዕዳ ምክንያት ደመወዝ እንዲያዝ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ የታክስ ዕዳ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ወይም የታክሱ ዕዳ በይርጋ ምክንያት ሊጠየቅ የማይቻል እስከሚሆንበት ጊዜ ድረስ የሚቀጥል ነው፡፡

በሌላ በኩል በታክስ ዕዳ ምክንያት የማይያዙ ገቢዎች በአዋጆች ተጠቅሰዋል፡፡ እነሱም፡- በሰንጠረዥ ‘ሀ’ ከግብር ነፃ ከተደረገው የገቢ መጠን ሳያልፍ ሰራተኛው የሚያገኘው ደመወዝ ወይም ማናቸውም በተወሰነ ጊዜ የሚገኝ ሌላ ገቢ እና በማናቸውም የኢትዮጵያ ሕግ እንዳይከበሩ የተደረጉ ገቢዎች ናቸው፡፡

ታክስ አስገቢው ባለስልጣን የታክስ ከፋዩን ንብረት ወይም ንብረቶች ለታክስ ዕዳ መክፈያ ለማዋል ንብረቱን ወይም ንብረቶቹን በመያዝ በሐራጅ ወይም በባለስልጣኑ በፈቀደ በማናቸውም ሌላ ዘዴ ለመሸጥ ይችላል፡፡  ሐራጁም የሚደረገው ንብረቱ ከተያዘበት ቀን አንስቶ ከሚቆጠር አስር ቀናት ጊዜ በኋላ መሆን አለበት፡፡ ሆኖም ግን ንብረቱ የሚበላሽ ከሆነ የንብረቱን ባህሪ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተገቢ መስሎ በታየው ጊዜ ሊሸጠው ይችላል፡፡ እንዲሁም የታክስ አስገቢው ባለስልጣን በታክስ ዕዳ ምክንያት ንብረቱን የመያዝ ሀሳብ እንዳለው አስቀድሞ ለታክስ ባለዕዳው በጽሑፍ ማስታወቅ አለበት፡፡ የጽሑፍ ማስታወቂያውም ንብረቱ ከመያዙ ከ30 ቀን በፊት ለታክስ ከፋዩ ሊደርሰው ይገባል፡፡

ሆኖም ግን የታክስ አስገቢው ባለስልጣ የታክሱን አሰባሰብ የሚያዳናቅፍ ሁኔታ መኖሩን የተረዳ እንደሆነ የሰላሳ ቀን የጊዜ ገደብ ሳይጠበቅ ታክሱ ወዲያውኑ እንዲከፈል ለማደረግ ጥያቄ ካቀረበና ታክስ ከፋዩ ለመክፈል ፈቃደኛ ካለሆነ ንብረትን በመያዝ ታክስ የመሰብሰብ አፈፃፀም ሕጋዊ ይሆናል፡፡

የንብረት መያዝ ውጤትም በሕጉ ተመልክቷል፡፡ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የተከበረ ወይም በአፈፃፀም ላይ ያለ ወይም በዋስትና የተያዘ ካለሆነ በስተቀር ማናቸውም በታክስ ምክንያት የተያዘ ንብረት በእጅ የሚገኝ ወይም ለታክስ ከፋዩ ማናቸውም ግዴታ ያለበት ሰው የታክስ አስገቢው ባለስልጣን ሲጠይቀው የያዘውን ሀብት የማስረከብ ወይም ያለበትን ግዴታ የመፈጸም ሐላፊነት አለበት፡፡ ንብረቱን ለማሰረከብ ፈቃደኛ ሳይሆን ከቀረ ግን በተያዘው ንብረት መጠን

በግል ተጠያቂ ይሆናል፡፡ የተጠያቂነቱ ግን ከሚፈለገው የታክስ ዕዳ መጠን ማለፍ የለበትም፡፡ በተጨማሪም ንብረቱን ለማስረከብ ፈቃደኛ ያልሆነው ያለበቂ ምክንያት ከሆነ የታክስ ዕዳ መጠን አምሳ ፐርሰንት በተጨማሪ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

በሌላ በኩል በይዞት ሥር ያለውን ንብረት አስረከበ ወይም ከታክስ ከፋዩ የሚፈለገውን ገንዘብ ለታክስ አስገቢው ባለስልጣን በተጠየቀው መሰረት ገቢ ያደረገ ሰው ካስረከበው ንብረት ወይም ገቢ ካደረገው ገንዘብ ጋር በተያያዘ የግብር ግዴታውን ባልተወጣው ታክስ ካፋይ ወይም ማናቸውም ሌላ ሰው ከሚፈለግበት ዕዳ ወይም ካለበት ግዴታ ነፃ እንደሚሆን ተመልክቷል፡፡

ዋስትና የተሰጣቸው የሌሎች አበዳሪዎች የቅድሚያ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ታክስ ተከፋይ ከሚሆንበት ቀን አንስቶ ተከፍሎ እስከአለቀበት ጊዜ ድረስ ታክስ የመክፈል ግዴታ ባለበት ሰው ሀብት ላይ የታክስ አስገቢው ባለስልጣን ከማናቸውም ሌሎች ዕዳዎች የቀደምትነት መብት አለው፡፡

የማይንቀሳቀስ ንብረትን በተመለከተ የታክስ አስገቢው ባለስልጣን የታክስ ዕዳ የሚፈለግበትን ሰው ሀብት በዋስትና ተይዞ እንዲቆይ ንብረቱን ለመዘገበው አካል የጽሑፍ ተዕዛዝ የሚሰጥ መሆኑን ለታክስ ከፋዩ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፡፡ ታክስ ከፋዩም ማስጠንቀቅያው በደረሰው 30 ቀን ውስጥ ታክሱን ያልከፈለ እንደሆነ ታክስ አስገቢው ባለስልጣን ለመዘገበው ባለስልጣን የታክስ ከፋዩ ሀብት ባልተከፈለው የታክስ ዕዳ መጠን በዋስትና ተይዞ እንዲቆይ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡ በዚህ መሰረት ትዕዛዝ ሲሰጥ መዝጋቢው ባለስልጣን ማናቸውንም ክፍያ ሳይጠይቅ ንብረቱን በዋስትና እንዲያዝ (mortgage) የደረሰውን ትዕዛዝ እንደማናቸውም በሀብቱ ላይ እንዳለ የመያዣ ሰነድ ይመዘግባል፡፡ የዋስትናው ምዝገባ የሚፈለገውን ታክስ ለማስከፈል በማናቸውም መልክ በሕግ እንደተሰጠ መያዣ (legal mortgage) ወይም እንደማናቸውም ሌላ ዕዳ ወይም ክፍያ ሆኖ ይቆጠራል፡፡

በመጨረሻም በታክስ ዕዳ ምክንያት የተያዘ ንብረት የተሸጠ እንደሆነ ከሽያጩ ከተገኘው ገንዘብ ውስጥ ታክስ ከፋዩ ከሚፈለግበት ዕዳ በላይ የሆነው ገንዘብ ለንብረቱ ባለቤት ይመለሳል፡፡

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በኢትዮጵያ ሕግ እንዳይከበሩ የተደረጉ ገቢዎች ካሉ ጥቀሱ፡፡
2. የታክስ አስገቢው ባለስልጣን ራሱ የሰጠውን ውሳኔ ራሱ የታክስ ከፋዩን ንብረት በመያዝ በሐራጅ እንዲሸጥ ማድረጉ ፍታዊ አይደለም ብለው ትችት የሚሰነዝሩ ሰዎች አሉ፡፡ በዚህ ረገድ እናተ ምን ትላለችው? ከሐገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አነፃር የታክስ ውሳኔ የማስፈፃም ሥልጣን ለራሱ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን መሰጠቱ ለምን አስፈለገ ብላቸው ታስባላቸው?
3. የታክስ አሰባሰብን የሚያደናቅፍ ሁኔታ ሳይኖር የታክስ አስገቢው ባለስልጣን በሕጉ የተቀመጠውን የጊዜ ገደብ ሳይጠብቅ የታክስ ከፋዩን ንብረት ቢይዝ ታክስ ከፋዩ ያለው መፍትሔ ምንድነው?
4. በሐራጅ ሒደት ሕገ ወጥ ተግባሮች ቢፈጽሙ የታክስ ከፋዩ መፍትሔ ምንድነው? ሐራጁ እንዲታገድለት ለፍርድ ቤት ቢያመለክት ፍርድ ቤቱ አቤቱታውን መቀበል ይቻላል? ይችላል ከተባለ የሕግ መሰረቱስ?
5. የታክስ አስገቢው ባለስልጣን የታክስ ባለዕዳውን ንብረት በሐራጁ መሰረት የሚገዛ ሰው ቢጠፋ ወይም ገዢ ባይቀረብ ያለው መፍትሔ ምንድነው? በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ውስጥ ያሉ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት አላቸው?
6. ሠራተኛ ደመወዝ እና ከግብር እዳ የትኛው ቅድሚያ አለው?
7. ታክስ መክፈል የዜግነት ግዴታ ነው፡፡ ይህ ከሐገራችን ታክስ ከፋዮች አንጻር እንዴት ይታያል? ለምሳሌ በሐገራችን የሚሰበሰበው ጠቅላላ ገቢ ውስጥ በታክስ መልክ ፈሰስ እየተደረገ ያለው ከአስራ ሁለት በመቶ አይበልጥም፡፡ ለዚህ ዋነኛው ችግር ምንድነው ትላላችው? ለዚህ ችግር መፍትሔው ምንድነው?

## ዋቢ ጽሑፎች

**ሕጎች**

- የኢፌድሪ ሕገመንግስት
- የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994
- የሚኒስተሮች ምክር ቤት የፋይናስ ደንብ ቁጥር 17/1989
- የሚኒስትሮች ምክር ቤት የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/2002
- የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994
- የቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር 110/1990
- የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 280/1994
- የኢንቨስትመንት ማበረታቻ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 7/1988
- የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 307/1995
- የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 308/1995
- የሚኒስትሮች ምክር ቤት የተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 79/1995
- የማዕድን ሥራዎች ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 52/1985
- የማዕድን ሥራዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 182/1986
- የ1948 የተሻሻለው ህገመንግስት
- የንግድ ህግ
- የፍትሐብሄር ሕግ
- የኢፌድሪ የወንጀል ሕግ

**ሌሎች**

- Bekele Haile Selassie, " Ethiopia–The Constitutional Law of Taxation and Its Implications for Federal and State Relations," A thesis Submitted in partial Fulfillment of the Requirements for the Degree of the Master of Law at the University of Wisconsin (unpublished) 1999
- Bekele Haile Selassie :-Ethiopia:- A Precarious Ethno- Federal Constitutional Order" A Dissertation for the Doctor of Juridical Science (S.J.D) University of Wisconsin Law School (unpublished) 2002.

- Solomon Negussie:- Fiscal Federalism in the Ethiopian Ethnic-Based Federal System" PHD thesis (2005)
- Alemayehu Tegene:- The Structure of Allocation of Taxation Power in FDRE. Term paper submitted for Fiscal Federalism course. (2002) AAU.
- Selected Materials and Cases on Tax Law. Compiled by Federal Supreme Court Judicial Training Program (2002).
- Discussion of the House of People Representative as regards the amendment of Art 98 of the FDRE Constitution, Megabit 30,1989 E.C
- Discussion of the joint session of the House of Federation and the House of Peoples Representatives as regards the amendment of Article 98 ot the FDRE Constitution, Miazia 2, 1989 E.C.
- Discussion of the House of Federation as Regards the amendment of the Articles 98 of the FDRE Constitution Miaza 1, 1989 E.C. On its 2nd ordinary session.
- Teferi Bekele;- Ordinary Business Deductions under the Ethiopian Income Tax Law: Law and Practice A thesis submitted in partial Fulfillment of the Requirements for the Degree of Bachelor of Laws at the Faculty of Law, Addis Ababa University (2007) (unpublished)
- Gebrie Worku, Tax Accounting in Ethiopia Context 2nd edition 2008
- Misrak Tesfaye, Ethiopian Tax Accounting: Theory and Practice, 2008.
- Bahtia.H.L. Public finance,5th edition, vices publishing House, 1976
- Basu Durge Das, Commentary on the Constitution of India Vol.4, 4th edition S.C. Saracen and Sons (PVT) Ltd, 196
- Musgrave, Richard D. and Musgrave, Peggy B., Public Finance 3rd edition, Grew Hill Company, 1980.
- Gupta, Alka , Public Finance and Tax Planning, First edition Anmol Publications PVT.LTD, New Delhi
- Cooke, J.E ed. Federalist Middleton, Connecticut: Wesleyan University Press, 1961.
- The Basic Law of the Federal Republic of German Constitution
- The Constitution of India

- Black's Law Dictionary (2004)
- የፍ/ቤት ውሳኔዎች
- የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራስያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የማስፈጸም አቅም ግንባታ ስትራቴጂና ፕሮግራሞች የማስታወቂያ ሚኒስቴር የፕሬስ ኦዶዩቪዥዋል መምሪያ (የካቲት 1994) አ.አ.
- ከገቢ ግብር አዋጅ ከተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ እና ከተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ማብራሪያ በሚያስፈልጋቸው አንቀጾች ላይ የተዘጋጀ ማብራሪያ (የገቢ ሚኒስቴር)